የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

ቀን /Date መስከረም 28 2013
ቁጥር/Ref. ሣ.ከ.ት.ሚ/1.18/3763/13

ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች
ባሉበት

ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡-መመሪያ ስለመላክ

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የትምህርትና ስልጠና ስራን ለመምራት የወጣ መመሪያ 56 ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር የተላከ መሆኑ ታውቆ መመሪያውን ለተቋማቱ ማህበረሰብ አባላትና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማስተዋወቅና በተደራጀ አግባብ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር በተቋሙ ከፍተኛ አመራር የቅርብ ክትል እየተደረገ እንዲተገበር አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፡-
- ለከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ
- ለከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል

  አዲስ አበባ

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት

  ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር

www.moshe.gov.et
+251-1-833 27 89
info@ethernet.edu.et
www.facebook.com/SHE.Ethio
23976 ኮድ/CODE 1000

Scanned with CamScanner

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

ቀን /Date ወሰከሞ 2 8 2013

ቁጥር/Ref. ሳገዴ/1.18/3763/13

ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች
<u>ባሉበት</u>

ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርና ስልጠና ኢንስቲትዩት
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:-<u>መመሪያ ስለመላክ</u>

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የትምህርትና ስልጠና ስራን ለመምራት የወጣ መመሪያ 56 ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር የተላከ መሆኑ ታውቆ መመሪያውን ለተቋማቱ ማህበረሰብ አባላትና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማስተዋወቅና በተደራጀ አግባቡ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር በተቋሙ ከፍተኛ አመራር የቅርብ ክትል እየተደረገ እንዲተገበር አሳስባለሁ::

ከሰላምታ ጋር

ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኑ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

<u>ግልባጭ</u>:-

- ለከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ
- ለከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል

  <u>አዲስ አበባ</u>

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት

  <u>ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር</u>



Scanned with CamScanner

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

# በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ውስጥ የመማር ማስተማር ስራን ለመምራት የወጣ መመሪያ

# Directive on Reopening of Higher Education and Training Institutions Amid Covid-19 Epidemic

Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

## መመሪያ ቁጥር 31/2013

### በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ውስጥ የመማር ማስተማር ስራውን ለመምራት የወጣ መመሪያ

አስተማማኝ የሆነ የኮቪድ-19 ክትባት ወይም ህክምና እስከሚገኝ ድረስ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ተዘግተው የነበሩ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በመከፈት የተቋረጠውን ትምህርትና ስልጠና እንደገና ማስቀጠል በማስፈለጉ፤

የኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጤና ሚኒስቴር ባቀረበው ምክረ ሃሳብ መነሻ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በቂ ዝግጅት አድርገው ተገቢ ጥንቃቄዎች በመውሰድ፣ ከልከላዎችንና ግዴታዎችን በማክበር እንዲከፈቱ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ተቋማቱ እንዲከፈቱ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ሁሉም የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተቋማቱ መልሰው ሲከፈቱ የሚኖሩ ለውጦችን ተገንዝበው የአሰራር ማስተካከያ እንዲያደርጉ ወጥ መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 86/5 እና በአዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀጽ 43/3 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1. አጭር ርእስ**

ይህ መመሪያ ''በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የመማር ማስተማር ስራን ለመምራት የወጣ መመሪያ 31/2013'' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

በሌሎች ጸንተው ባሉ የትምህርትና ስልጠና ህጎች ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንዳሉ ሆነው የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "የትምህርትና ሥልጠና ተቋም" ማለት የመንግሥት ወይም የግል ወይም መንግስታዊ ያልሆነ የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ነው፡

2) "የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ" ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 28 ና 34 ከተገለጸው በተጨማሪ ተማሪዎችን እንዲሁም በግቢ ውስጥ የሚገኝን ከተቋሙ ጋር ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው ይጨምራል፡፡

## Directive No. 31 / 2020

### A Directive prepared to direct the teaching and learning efforts in educational and training institutions during the CVD-19 epidemic.

Due to the need to reopen the closed educational and training facilities with the necessary care until a reliable CVD-19 vaccine or treatment is available;

Given the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (FDRE) has issued a directive to ensure the opening of the institutions in accordance with the guidelines set by the Ministry of Health;

Given the need for a uniform guideline for all education and training institutions and relevant stakeholders to be aware of the changes that will occur when the institutions are reopened and to make the necessary adjustments;

The Ministry of Science and Higher Education has issued this directive in accordance with the Proclamation No. 1152/2019 and 954/2016.

### Part One

### General Provisions

**1. Short Title**

This guideline may be referred to as "Directives for directing the teaching and learning efforts in education and training institutions during the Covide-19 epidemic 31/ 2020.

**2. Definitions**

Unless otherwise indicated, the terms of this directive shall be understood as described here, with prejudice to all applicable education and training laws:

1) "Education and training institution" is a public or private or NGO educational and training institution;

2) In addition to what is stated in Articles 28 and 34 of the Higher Education Proclamation No. 1152/2019, "Education and Training Institution Community" includes students as well as anyone in the campus who is somehow connected with the institution;



Scanned with CamScanner

3) "የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ማኅበረሰብ አባል" ማለት መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የአስተዳደር ሠራተኞች ወይም በግቢ ውስጥ የግንባታና ልዩ ልዩ ፕሮጀክት ሥራ የሚሰሩ፣ በቋሚነት የምግብ አቅርቦት ከውጪ የሚያቀርቡ፣ በግቢ ውስጥ ባሉ ሱቆች፣ ሱፐርማርኬቶች፣ ምግብ ቤቶች እና መሰል አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሰዎችን ያካትታል፤

4) "ተማሪ" ማለት በትምህርትና ስልጠና ተቋማት በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርትና ስልጠና መርኃ ግብሮች ተመዝግቦ በመማር ወይም አጭር ሥልጠና በመውሰድ ላይ ያለ ሰው ነው::

5) "ዕጩ ተመራቂ" ማለት ለመመረቅ የሚያስችሉ ሁሉንም ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ የምረቃ ሥነ-ሥርዓት እስከሚከናወንና የትምህርት ማስረጃው ተሰጥቶት ከተቋሙ ለመውጣት የሚጠባበቅ ተማሪ ነው::

6) "ሥነ ምግባር' ማለት ማንኛውም በተቋሙ ወይም በተቋሙ ማኅበረሰብ አባላት ወይም ከተቋሙ ውጭ ባለ ማኅበረሰብ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ የሚችል ባህሪይ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ሊገለጽ የሚችል ነው::

7) "የዲሲፕሊን ጥፋት" ማለት በዚህ መመሪያ ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተከለከለ ድርጊት መፈፀም፣ መተባበር ወይም ሲፈጸም እያዩ በቸልተኝነት ማለፍ ነው::

8) "የዲሲፕሊን መመሪያ" ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 1152/2011 አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የወጣ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የዲስፕሊን መመሪያ ነው:

9) "አነስተኛ የዲሲፕሊን ጥፋቶች" የሚባሉት ለዲስፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በዚህ መመሪያ መሠረት ኃላፊነት በተሰጠው አካል የምክር፣ የቃል ወይም የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው::

10) "ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች" የሚባሉት ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና እንደአስፈላጊነቱ ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያስቀጡ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው::

11) "መካከለኛ የዲሲፕሊን ጥፋቶች" ከአንድ ወሰነ ትምህርት እስከ ሁለት ዓመት የሚያስቀጡ (ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ) የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው::

12) "ከፍተኛ የዲሲፕሊን ጥፋቶች" የሚባሉት ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጡ (ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ) የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው::

13) "በጣም ከፍተኛ የዲሲፕሊን ጥፋቶች" የሚባሉት ከትምህርትና ስልጠና ተቋም መርኃ-ግብር ሙሉ በሙሉ መሰናበትን የሚያስከትሉ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው::

14) "ኮቪድ-19 ወረርሽኝ" ማለት በዓለም የጤና ድርጅት በዚህ ስም የሚጠራው ተላላፊ በሽታ ነው::

15) "ማስክ" ማለት ኮቪድ-19 ወረርሽኝን በትክክል ለመከላከል የሚያስችል በፋብሪካ የሚመረት ወይም በቤት ውስጥ የሚዘጋጅ አፍና አፍንጫን በአግባቡ ለመሸፈን የሚያገለግል ጭምብል ነው::

3) "Community Member of Education and Training Institutions" means teachers, students, administrative staff or people who work on construction and various projects on campus, provide regular food services from outside, provide in-campus store shops, supermarkets, restaurants and similar services;

4) "Student" means a person who is enrolled in formal and informal education and training programs in educational and training institutions or is undergoing short training;

5) "Graduating Candidate" means a student who has met all the requirements for graduation and is expected to leave the institution after graduation;

6) "Ethics" means any behavior that may have a positive or negative effect on any member of the institution, community or anyone outside the institution;

7) "Disciplinary Offense" means committing or cooperating or negligently acting in accordance with this Directive or other applicable laws.

8) "Discipline Guide" means a disciplinary guideline issued by the Ministry of Science and Higher Education in accordance with Article 86 Sub-Article 5 of the Higher Education Proclamation 1152/2019.

9) "Minor Disciplinary Offenses" are disciplinary offenses that provide counseling, oral or written notice to the responsible body in accordance with this Directive without having to report it to the Disciplinary Committee;

10) "Simple Disciplinary Offenses" are disciplinary offenses that range from written warnings to severe written warnings and social services as needed;

11) "Intermediate Discipline Offenses" are disciplinary offenses punishable by one-year to two-year suspension from school;

12) "Major Disciplinary Offenses" are disciplinary offenses punishable by two to three-year suspension from school;

13) "Serious Disciplinary Offenses" are disciplinary offenses that are punishable by complete dismissal from the programs of the Education and Training Institution;

14) "Cowid-19 epidemic" is a contagious disease so labeled by the World Health Organization;

15) A "mask" is a factory or home-made mouth and nose cover used to effectively prevent the spread of COVID-19.



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

16) "አካላዊ መራራቅ" ማለት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከሰው ወደ ሰው የሚኖረውን ስርጭት ለመቀነስ ወይንም ለመግታት በሁለት ወይንም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የተቀመጠውን 2 ሜትር ርቀት መጠበቅ ነው፤

17) "ስብሰባ" ማለት አራትና ከዚያ በላይ ሆኖ በአንድ ቦታ በአካል መገኘት ነው:: ነገር ግን በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማስቀጠል የመነጋገር፣ ሥልጠና የመስጠት፣ የመወያየት፣ ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ ተግባራትን አያካትትም::

18) "ለይቶ ማቆያ" ማለት የዶርም አገልግሎት ለሚሰጣቸው ተማሪዎች ለኮቪድ-19 በሽታ የተጋለጡ፣ የተጠረጠሩ ወይንም ተመርምረው በበሽታው መያዛቸው ሲረጋገጥ በተቋሙ ግቢ ውስጥ የሚቆዩበት ስፍራ ነው፤

19) "የኮቪድ-19 ምልክቶች" ማለት በኮቪድ-19 የተያዘ ሰው ላይ ሊስተዋሉ የሚችሉ እንደ ትኩሳት፣ የራስ ምታት፣ የሳል፣ ጣዕምና ሽታን መለየት አለመቻል፣ የጉሮሮ አካባቢ ቁስለቶችና የመሳሰሉ ምልክቶች ናቸው፤

20) "ኮቪድ 19 ፖዘቲቭ" ማለት ተመርምሮ ቫይረሱ የተገኘበት ሰው ማለት ነው፤

21) "ቀላል የኮቪድ-19 ታካሚ" ማለት በኮቪድ-19 የተያዘ ሆኖ የሳንባ ምች በሽታን ወይም ሌሎች የኮቪድ-19 ከፍተኛ ህመም ምልክቶችን የማያሳይ ታካሚ ነው፤

22) "ፀረ-ተህዋሲያን ውህድ" ማለት ከኮሮና ቫይረስ ጋር ንክኪ ይኖርቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ እቃዎችን ለማጽዳት የሚውል ከአልኮል ወይም ከሎሪን የተዘጋጀ ውህድ ማለት ነው፤

23) "ራስን ማግለል" ማለት የኮቪድ-19 ንክኪ ያለው ወይም ተጠርጣሪ የሆነ ሰው የወረርሸኙን ስርጭት ለመግታት ሲባል ከሌሎች ጋር ያለውን አካላዊ ግንኙነት በማቆም ራስን ለይቶ ማቆየት ነው::

24) "በጸረ-ተህዋሲያን ኬሚካሎች" ማለት ለኮቪድ-19 መከላከል ተብለው የተለዩ ስታንደርድ ይዘታቸውና መጠናቸው የታወቀ "sodium hypochlotite /calcium hypochlorite/ hypochlorous acid" ማለት ነው::

25) "የተቋም ኃላፊ ወይም ምክትል ሀላፊ " ማለት እንደቅደም ተከተሉ አንድን የትምህርትና ሥልጠና ተቋም በሀላፊነት ወይም በምክትል ሀላፊነት የሚመራ ግለሰብ ነው::

26) "ጥፋት" ማለት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተላልፎ መገኘት ማለት ነው::

27) "የጥፋት ምድብ" ማለት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ሲተላለፉ ከሚያስከትሉት የጉዳት ክብደት፣ በቀጣይት ከሚፈጥሩት አሉታዊ ተጽዕኖ፣ ድግግሞሽ እና የሚወሰነው የቅጣት ውሳኔ ማስተማሪያነት ደረጃን ታሳቢ በማድረግ አነስተኛ፣ ቀላል፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ ወይም በጣም ከፍተኛ ብሎ መመደብ ማለት ነው::

28) በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለጸው በሙሉ የሴትንም ፆታ ያካትታል።

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

16) "Physical Distance" means maintaining the distance between two or more people to reduce or stop the spread of the COVID-19 epidemic;

17) "Meeting" means the gathering of four or more persons in one place. However, it does not include the gatherings to conduct the teaching and learning process in educational and training institutions; it does not prohibit talking, training, discussion, and awareness raising activities for educational purposes;

18) "Isolation Center" means a place where dormitory students who are exposed, suspected or diagnosed with Covid-19 disease may stay on campus;

19) "Symptoms of COVID-19" are symptoms such as fever, headache, cough, inability to distinguish odors, sore throats, etc. caused by exposure to the Corona Virus;

20) "Covid-19 Positive" means a person who has been diagnosed with the corona virus;

21) "Simple COVID-19 Patient" means a COVID-19 patient who does not show any symptoms of pneumonia or other severe COVID-19 symptoms;

22) "Antimicrobial solution" means an alcohol or chlorine compound used to clean items that are thought to be in contact with corona virus;

23) "Self-Isolation" means to isolate oneself, if one is or suspects to be exposed to COVID-19, by stopping physical contact with others in order to prevent the spread of the virus;

24) "Head or Deputy Head of an Institution" means an individual who manages an educational or training institution in a leading or deputy position;

25) "Offense" means a violation of the provisions of this Directive;

26) "Category of Offense" means to classify offenses as minor, simple, medium, high or very high, taking into account the severity of the harm in accordance with the provisions of this Directive, its subsequent negative impact, frequency and the level of punishment to be determined;

27) The masculine gender used also includes the feminine gender.

### 3. Limitations

This guideline applies to education and training institutions throughout the country.

## ክፍል ሁለት
## የተከለከሉ ተግባራት እና የተጣሉ ግዴታዎች

### 4. የተከለከሉ ተግባራት

1) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም የፊት ለፊት ትምህርትና ስልጠና መስጠት መጀመር እንደሚችል ከሚመለከተው አካል ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ስለመሆኑ ተረጋግጠ ውሳኔ/ፈቃድ ሳይሰጥ እንዲሁም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስራውን በተመለከተ የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር ወይም ሳይከተል ትምህርት መስጠትና ስልጠና ማስጀመር የተከለከለ ነው፣
2) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል ኮቪድ-19 እንዳለበት እያወቀ ወይም ከለይቶ ማቆያ አምልጦ ወደ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ መግባት፣ ከተቋሙ ማኅበረሰብ ጋር መቀላቀል ወይም ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ በሚችልበት ሁኔታ ከሌሎች የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ማኅበረሰብ አባላት ጋር መገናኘት የተከለከለ ነው::
3) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል እንዲሁም ወደ ተቋሙ አገልግሎት ለመስጠትም ሆነ ለማግኘት የሚመጣ ሰዉ ለሰላምታም ይሁን ለማንኛውም ዓላማ በእጅ መጨባበጥ፣ ሆነ ብሎ የዕርስ በዕርስ አካላዊ ንክኪ ማድረግ የተከለከለ ነው::
4) የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግ፣ ቀሪ መሆኑ እስከሚወሰንበት እና ሥልጣን ባለው አካል በይፋ እስከሚገለጽበት ጊዜ ድረስ ከመኝታ እና ከመመገቢያ ሰዓት ውጪ በማንኛውም ቦታ ማንኛውም ሰው በትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ሳያደርግ መንቀሳቀስ በፍጹም የተከለከለ ነው፣
5) የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ ተገልጋዮች በሚቀመጡበት ጊዜም ይሁን በማንኛዉም አኳኋን አገልግሎቱን ሲያገኙ ቢያንስ ከአንድ ሜትር በታች እንዳይጠጋጉ እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርጉ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ወይም በአንድ ጠረጴዛ ከ3 ተገልጋዮች በላይ እንዲቀመጡ ማድረግ የተከለከለ ነው::
6) የተቀደደ፣ንጽህናዉ ያልተጠበቀ፣ በአግባቡ መሸፈን የማይችልና ተገቢ ባልሆነ መልኩ የተደረገ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግና መጠቀም የተከለከለ ነው::
7) ከተማሪዎች ምግብ ቤት እና ከሌሎች ግቢ ውስጥ ካሉ ምግብ ቤቶች የሚወጡ ትርፍራፊ ምግቦችን ለሌላ ለማንኛውም አካል አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው::
8) ማንኛውም ተማሪ ወይም ሰልጣኝ ተቋሙ ካለበት ከተማ ውጪ በግሉ ዕቅድ የተጓዘ እንደሆነ ቀድሞ የጉዞ ታሪኩን ተቋሙ ውስጥ ላለው ማዕከል ማስመዝገብ ያለበት ሲሆን ከጉዞ መልስ ራሱን በለይቶ ማቆያ ውስጥ ሳያቆይ ወይም ተመርምሮ በሽታው እንደሌለበት እስኪረጋገጥ ድረስ በቀጥታ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር መቀላቀል የተከለከለ ነው፡

## Part Two
## Prohibited Activities and Obligations

### 4. Prohibited Activities

1) It is prohibited to provide face-to-face education and training without permission from the relevant body and without complying with the general precautionary measures.
2) It is prohibited for any member of the Education and Training Institution community who is infected with the corona virus or suspects of being infected, to enter the Education and Training Institution, knowingly or unintentionally, to associate with the Institutional Community or to communicate with other members of the Education and Training Institution in a manner where the virus can be transmitted to other people.
3) It is forbidden for any member of the Education and Training Institution community and anyone who comes to the institution to shake hands for any reason or to make any physical or bodily contact with anyone.
4) No one shall be allowed to remove the mask from his or her nose and mouth, with the exception of sleeping and eating hours, until the decision is made to stop wearing masks by the relevant authority and is made public.
5) Service recipients should not be less than one meter away from the next person and must use masks while receiving services. If sitting at a table, no more than three persons should sit at the table.
6) It is forbidden to use worn out, torn, or unhygienic and improperly applied masks.
7) It is prohibited to supply to anyone leftover food from student cafeteria or other campus food services.
8) Any student or trainee who plans to travel outside of the local vicinity must report his travel plans to the institution and upon return must self-quarantine himself or get tested for COVID-19 prior to socially mingling with the community.



Scanned with CamScanner

9) ኮቪድ-19ን ለመከላከል የሚደረጉ የጥንቃቄ መልዕክቶችን ይዘው የተለጠፉት ማስታወቂያዎችን መቅደድ፣ ሌላ ማስታወቂያ ደርቦ መለጠፍ፣ ማበላሸት ወይም በሌላ ቁስ መጋረድ የተከለከለ ነው::

10) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በሀኪምና ባለሙያ የተረጋገጠ ምንም ዓይነት የኮቪድ-19 ምልክቶችና ስሜቶች ሳይኖሩት ሆነ ብሎ በሀሰት የኮቪድ-19 ታማሚ ነኝ በሚል በተቋሙ ላይ ስጋት ወይም ፍርሀት እንዲፈጠር ማድረግ የተከለከለ ነዉ::

11) ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በተቋሙ ላይ ወይም በሌላ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ አሉታዊ የስነ-ልቦና ይሁን የማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጫና ወይም ጉዳት የሚፈጥር ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ መረጃዎችና አስታያየቶችን በመረጃ መረብም ሆነ በማንኛዉም መልኩ ማሰራጨት የተከለከለ ነዉ::

12) ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል አላስፈላጊና በሳይንስ ያልተረጋገጡ የኮቪድ-19 መረጃዎችና አስታያየቶችን በመረጃ መረብም ሆነ በማንኛዉም መልኩ ማሰራጨት የተከለከለ ነዉ:

13) ማንኛዉም ሰዉ ወደ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሲገባ በር ላይ ባለዉ የሙቀት መለኪያ ሳይለካና ሳያረጋግጥ መግባት የተከለከለ ነዉ::

14) የተማሪዎች መዝናኛ፣ ስፖርታዊ ውድድርን በሚመለከት

ሀ. ማንኛውም የአካል ቅርርብንና ንኪኪን የሚፈልጉ የተማሪዎች የቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ያሉ መዝናኛዎች፣ የመዝናኛ መሳሪያዎችና ጨዋታዎች በማንኛውም ደረጃ የሚደረግ የቡድን ስፖርታዊ ውድድር ማድረግ የተከለከለ ነው::

ለ. ተማሪዎች በግል ካልሆነ በስተቀር የቡድን ስፖርት መስራት አይፈቀድም::

ሐ. በተቋሙ ግቢ ውስጥ የሚደረጉ የስነ-ጽሑፍ ምሽቶችና የተለያዩ የመዝናኛ መሰባሰቦች የተከለከሉ ናቸው::

መ. በግቢ ውስጥ ባሉ ላዉንጆችና መዝናኛ ቦታዎች የሚገኙ የቤት ውስጥ መዝናኛ ጨዋታዎችን ማድረግ የተከለከሉ ነው::

15) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በግልም ሆነ በቡድን በማንኛውም መልኩ የተቋሙን ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት የሚያውክ እንቅስቃሴና ተግባራትን ማቀድ፣ መፈጸም፣ ማስተባበር፣ መተባበር የተከለከለ ነው::

16) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በግልም ሆነ በቡድን ፖለቲካ፣ ኃይማኖት ወይም ብሔር ተኮር የግጭት መንስኤና አባባሽ የሆኑ፣ አለመግባበትና ጥርጣሬ የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎችና ተግባራትን መፈጸም የተከለከለ ነው::

9) It is prohibited to tear, erase, damage or cover any posted Covid-19 announcement or material on any notice board.

10) It is prohibited for any member of the Education and Training Institution community to cause fear or intimidation on institutional premises under false premises that he/she is infected by CVD-19 without certification by a medical professional.

11) Any member of the Education and Training Institution community is prohibited from disseminating disturbing information and/or comments related to CVD-19 on the Internet or on any other social media that may cause psychological, social or economic hardship or harm to the institution, individual or group.

12) It is prohibited for any member of the Education and Training Institution community to disseminate unnecessary and/or unsubstantiated COVID-19 related information and/or comments on the Internet or on social media.

13) It is forbidden for anyone to enter an educational and training facility without submitting to required temperature check at the entrance.

14) Regarding student recreation and sports:

a. Indoor and outdoor recreation, recreational equipment, games or sports that require physical closeness or contact are prohibited.

b. Students are not allowed to play group sports except individual activities that don't require any physical contact with others.

c. Entertainment and/or social gatherings (during the day or evening) are prohibited.

d. Indoor entertainment in campus lounges and recreation areas is prohibited.

15) It is prohibited for any member of the Education and Training Institution community to individually or collectively plan, carry out, coordinate or collaborate in activities that disrupt the peaceful teaching and learning process of the institution.

16) It is prohibited for any member of the education and training community to personally or collectively engage in activities that are politically, religiously or ethnically motivated, causing or encouraging conflicts, misunderstandings, and/or suspicions.



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Science and Higher Education

Scanned with CamScanner

## 5. የተጣሉ ግዴታዎች

1) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ኮቪድ-19ን በመከላከል ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚችልበትን አጠቃላይ ሁኔታ የሚደነግግና ከዚህ መመሪያ ጋር የተጣጣመ ማንዋል የማዘጋጀት፣ የማስተዋወቅና የማስፈጸም ግዴታ አለበት።

2) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ኮቪድ-19 ወረርሽኝን በመከላከል ትምህርትና ስልጠናን ለማስቀጠል በየደረጃው የሚያስተባብር ግብረ-ኃይል የማደራጀት፣ የግንኙነት መሥመር የማዘጋጀትና ለተጠቃሚዎች ምቹ በሆነ መንገድ የማስተዋወቅ ግዴታ አለበት።

3) ቢሮዎች፣ ለመማር ማስተማር የሚጠቀሙባቸው ክፍሎች፣ ቤተ-መጽሐፍትና ቤተሙከራዎች፣ የተማሪዎች ማደሪያ ክፍሎች በየቀኑ ከተቻለም ከዚያ በታች በሆነ ድግግሞሽ የሚጸዱና በቂ አየር የሚዘዋወርባቸው እንዲሆኑ የማድረግ ግዴታ አለበት።

4) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት በቂ ውሃ፣ ከእጅ ንክኪ ነጻ የሆኑ የእጅ መታጠቢያዎች፣ ልብስ ማጠቢያዎች፣ ልብስ ማስጫዎች፣ መጸዳጃ ቤቶች የተሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

5) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም በቂ የህክምና ባለሙያዎች ያሉትና በየደረጃው ህክምና እና መድኃኒት መስጠት የሚችል ክሊኒክ የማዘጋጀት ግዴታ አለበት።

6) የመኝታና የምግብ አገልግሎት የሚሰጡ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ተማሪዎችን መልሰው ከመቀበላቸው በፊት በየካምፓሱ እንደየሁኔታው የማቆያና የለይቶ ማቆያ (Quarantine and Isolation Center) እና አገልግሎት መስጫ ማዕከል ማዘጋጀት አለባቸው። ለዚህም ከጤና ተቋማትና ሌሎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት ይኖርባቸዋል።

7) የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የተቋሙ ተማሪዎች /ሠልጣኞች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ ይመከራል።

8) ኮቪድ-19ን ለመከላከል የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን ለሁሉም ተማሪዎች/ሰልጣኞች፣ መምህራንና አስተዳደር ሠራተኞች በቂ ግንዛቤ የመፍጠር፣ በግልጽ በሚታዩ ቦታዎች በቪድዮ ማሳየት፣ በጽሑፍ መለጠፍ አግባብ ባለው መንገድ መልዕክት የማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው።

9) በቂ፣ የግል መከላከያ ቁሳቁሶችን (PPE) የሚጠቀሙ እና ግንዛቤ ያላቸው የጽዳት ሠራተኞች እንዲኖሩ የማድረግና በአግባቡ እያጸዱ ስለመሆናቸው የመቆጣጠር ግዴታ አለባቸው።

10) ከኮቪድ-19 ልዩ ባህሪይ አንጻር ብቂ የግል መከላከያ (ማስክ፣ ጓንት፣ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት…ወዘተ) ለጽዳት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን (ሳሙና፣ ጸረ-ተህዋሲያን ኬሚካል/ቴክኖሎጂ…ወዘተ) ቀድሞ የማዘጋጀትና በማይበላሹበት ጊዜና ሁኔታ የማከማቸት) ግዴታ አለበት።

## 5. Obligations

1) All educational and training institutions are obligated to prepare, promote and implement a manual in accordance with this directive that stipulates the general conditions for the provision of education and training to protect members from the spread of COVID-19 epidemic.
2) Every education and training institution is required to create a task force at all levels to organize and coordinated efforts and communicate in a user-friendly manner in order to curtail the spread of CVD-19 epidemic.
3) Offices, classrooms, libraries, laboratories, and student dormitories shall be cleaned and ventilated at least on a daily basis.
4) Every education and training institution is required to ensure that sufficient water, touch-free hand washes, laundry, and toilets are provided prior to the commencement of the teaching and learning process.
5) All educational and training institutions are responsible for setting up a basic clinic that has adequate medical staff and can provide basic treatment and medication.
6) Education and training institutions that provide dormitory and food services must set up Quarantine and Isolation Center and Service Centers on every campus before accepting students. To this end, they need to work in collaboration with health offices and other relevant institutions.
7) Every educational and training institution is advised to widen opportunities for the students / trainees, teachers, employees and administrative staff to get masks with affordable price.
8) All education and training institutions have the duty to provide clear and adequate information and post notices in strategically important locations through written and video displays to inform their students / trainees, teachers and administrative staff in order to prevent COVID-19.
9) Education and Training Institutions have the duty to ensure that there are adequate, knowledgeable and efficient janitorial service providers and to monitor them properly.
10) Due to the special characteristics of Covid-19, Education and Training Institutions are required to prepare adequate personal protective equipment (masks, gloves, garbage cans, etc.) and cleaning materials (soap, antimicrobial chemicals, appropriate technology, etc.) and ensure that they are made readily available and safely stored.



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

11) በቂ የፍሳሽና የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓትና መሠረተ ልማት የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡፡

12) የሰው እንቅስቃሴ የሚበዛባቸው አካባቢዎች፣ በብዙ ሰው የሚነካኩ የጋራ መገልገያዎች፣ ጠረጴዛዎች፣ እጀታዎች፣ ቁሳቁሶች ...መሠል ቦታዎችና ዕቃዎች በየቀኑ በጸረ-ተህዋሲያን ኬሚካሎች ወይም 70 በመቶ አልኮል በሆነ የማስፀዳት ግዴታ አለበት፡፡

13) መማሪያ ክፍሎች፣ የተማሪዎች ማደሪያ፣ ቤተ-ሙከራና ወርከ ሾፖች፣ ቤተ መጽሐፍት፣ ምግብ ቤትና መሰል አገልግሎት መስጫ አካባቢዎች በቂ የአየር ዝውውር ያለባቸው እና በአግባቡ የሚጸዱ መሆን አለባቸው፡፡

14) የትምህርትና ስልጠና ተቋም የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫቶች የያዙት ቆሻሻ ከተደፋ በኋላ ወደ ነበሩበት ቦታ ወይም ከፍሎች ከመመለሳቸው በፊት በጸረ-ተህዋሲያን ማፅጃ ኬሚካል ወይም ቴክኖሎጂ የጸዱ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

15) የእጅ መታጠቢያዎችን ግቢ መግቢያ በር አካባቢ፣ በቢሮዎች፣ በቤተ-መጽሐፍት፣ ምግብ ቤቶች፣ መግቢያ በሮች አካባቢና ከፍተኛ የሰው እንቅስቃሴ በሚገኝባቸው ቦታዎች ላይ ከበቂ ውኃና ሳሙና ወይም ሳኒታይዘር ከተመደቡ ተቆጣጣሪዎች ጋር የማዘጋጀት ግዴታ አለበት፡፡

16) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባልና ማንኛውም ወደ ተቋሙ ግቢ የሚገባ ሰው የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስከ ማድረጉን የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

17) ማንኛውም በትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ የሚንቀሳቀስ ሰው የሚያደርገው የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ያልተቀደደ፣ ንጽህናው የተጠበቀና በአግባቡ መሸፈን የሚችል መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

18) በመማሪያ ክፍል ሁሉም ሰው የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ አድርጎ የተማሪዎች አቀማመጥ ከመጻፊያ ሰሌዳ እና ከፊት ረድፍ መካከል ቢያንስ ሁለት ሜትር ርቀት የሚኖረው ሆኖ በተማሪዎች መካከል ቢያንስ አንድ ሜትር ርቀት እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡

19) በቤተ-ሙከራና በቤተ መጽሐፍት በጠረጴዛ መካከል 1 ሜትር ርቀት መኖሩን እና ተማሪዎቹ ማስከ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

20) በመመገቢያ አዳራሾች ተማሪዎች እጅ ሲታጠቡ፣ሲሰለፉና ሲመገቡ ተገቢውን ርቀት መጠበቃቸውን ማረጋገጥና ክትትል ማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

21) አካላዊ ርቀትን የበለጠ ለመጠበቅ መመገቢያ ሰዓትን የማራዘም ፣ ተጨማሪ የማንበቢያ ክፍሎችን የማደራጀት፣ የገጽ ለገጽ ትምህርትና ስልጠና ሰዓትን የማሳጠር (40 ደቂቃዎች የማድረግ) ፣ ሁሉም ቤተ-መጽሐፍት፣ ቤተ-ሙከራ፣ ምግብ ቤቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን እና በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት መስጠት መቻላቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡

11) Institutions are responsible for the development of adequate drainage and solid waste disposal systems and infrastructure.

12) Areas where there is much human activity, commonly used utensils, tables, desks, door handles, and furniture must be sanitized daily with standard disinfectant /sodium hypochlotite / calcium hypochlorite/ hypochlorous acid or solution with 70% alcohol content.

13) Classrooms, dormitories, laboratories and workshops, libraries, cafeterias, etc. should be ventilated and cleaned.

14) It is mandatory to ensure that waste containers, once emptied, are cleaned with antimicrobial chemicals before they are returned to the rooms.

15) It is mandatory to provide hand-washing facilities with sufficient water, soaps and sanitizers near entrances to campuses, offices, libraries, cafeterias, and areas of high human traffic with constant supervision.

16) It is the duty of the Education and Training Institution to monitor and ensure that everyone entering the premises is wearing a mask appropriately.

17) All Education and Training Institutions are required to monitor and ensure that every person entering the premises is wearing a clean and untorn mask at all times.

18) As everyone in the calassroom wears mask, the distance between the wall and front row in the classroom should be at least two meters, and at least one meter between students.

19) Library, laboratory and other tables should be set at least one meter apart and students using these facilities should wear proper masks.

20) Ensuring and monitoring the proper distance of students while queuing, washing hands and eating in dining halls is strictly required.

21) In order to maintain a healthy physical distance, required actions include extension of dining time, arranging for additional reading rooms, shortening of face-to-face teaching and learning time (limiting it to 40 minutes), ensuring that all libraries, laboratories, and food service facilities are fully operational during service hours.

Ministry of Science and Higher Education, Federal Democratic Republic of Ethiopia



Scanned with CamScanner

22) ማንኛውም አካላዊ ቅርርብንና ንክኪን የሚፈጥሩ ስፖርታዊ ውድድሮችና ጫዋታዎች እንዳይካሄዱ የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

23) በመግቢያና መውጫ አካባቢ መጨናነቆች እንዳይፈጠሩ አማራጭ የግቢና የህንጻ መግቢያና መውጫ በሮችን ማዘጋጀት አለበት፡፡

24) የኮቪድ-19 ተጠርጣሪን የመለየትና የማከም ሥራዎችን በሚመለከት ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም፡-

ሀ. በሁሉም መግቢያዎች የሙቀት መለኪያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን የማሰባሰብና ከማስተባበሪያ ግብረ ኃይሉና ከማዕከሉ ጋር በመቀናጀት የክትትል ሥራ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

ለ. የማቆያና የለይቶ ማቆያ ማዕከል (Quarantine and Isolation centers) የማዘጋጀት ተጠርጣሪ ሲገኝም ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማት ጋር በመሆን የመከታተል፣ የተሟላ ባለሙያ ያለው ክሊኒክ የማዘጋጀት ግዴታ አለበት፡፡

ሐ. ማንኛውም የመተንፈሻ አካል ችግር የተከሰተበት የትምህርትና ስልጠና ማህበረሰብ አባል ወዲያው ተለይቶ ተገቢው ክትትል የሚደረግበት ስርዓት የመዘርጋትና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

መ. ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማት እና ኮቪድ-19 መከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ከሚሰሩ አካላት ጋር ፈጣንና መደበኛ የግንኙነት ስርዓት የመፍጠርና ሁል ጊዜ አገልግሎት ላይ ያለ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

ሠ. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ማኅበረሰብ አባል የሆነ ግለሰብ ኮቪድ-19 ያለበት መሆኑ ሲጠረጠር ወይም በምርመራ ሲረጋገጥ እና ቀላል ህመም ሁኔታ ካሳየ በቤት ውስጥ ወይንም በተዘጋጁት ለይቶ ማቆያዎች እንዲቆይ የማድረግና ከሚመለከታው የጤና ተቋማት ጋር በመቀናጀት የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡

ረ. ከኮቪድ-19 ተጠርጣሪ ወይም ታማሚ ጋር ንኪኪ ያላቸው ሆነው የተለዩ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች በቤታቸው እንዲቆዩ የማድረግና ተማሪዎችን በግቢው ውስጥ ወደተዘጋጀው ለይቶ ማቆያ የማስገባትና ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማት ጋር በመቀናጀትና በሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች ጋር የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡

ሰ. ማንኛውም የኮቪድ-19 ታማሚ መሆኑ በምርመራ የተረጋገጠ ግለሰብ ከባድ የህመም ምልክቶችን ካሳየ በተቋሙ እና በጤና ቢሮ በተለዩ የጤና ተቋማት ክትትል እንዲደረግለት የማድረግ ግዴታ አለበት፡

ሸ. ማንኛውም ኮቪድ-19 በሽታ አለብኝ ብሎ እራሱን የሚጠረጥር ወይም በሽታው አለበት ተብሎ የሚጠረጠር የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል እና ስለመኖሩ የሚያውቅ ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ማኅበረሰብ አባል በተቋሙ ለዚሁ ዓላማ ተብሎ ለተቋቋመ ማዕከል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ በተመሳሳይ ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ይህንኑ መረጃ ለጤና ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ እና በተዋረድ ላሉ ቢሮዎች በአቅራቢያው ለሚገኙ የጤና ተቋም ወይም ባለሞያ በወቅቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

22) It is mandatory to prohibit all sports and games that can cause close physical proximity and contact.

23) Alternative entrances and exits should be provided to prevent congestion at entrances and exits.

24) In regard to identification and treatment of COVID-19 suspects: all Educational and Training Institutions:

a. All Education and Training Institutions shall collect health data using temperature sensors at all entrances and inform and follow-up with the coordinating task force and the center.

b. All Education and Training Institutions shall set up quarantine and isolation centers to place and follow-up individuals suspected of being infected. It is mandatory to set up a fully equipped and functional clinic in conjunction with relevant local health institutions.

c. All Education and Training Institutions shall set-up a system that would immediately separate, address and follow-up on individuals on campus who may exhibit respiratory problems.

d. All Education and Training Institutions shall establish a fast and regular communication system with relevant health authorities and the CVD-19 prevention and control bodies and ensure that it is always in a ready mode.

e. Any member of the education and training community if suspected of or is diagnosed to have the corona virus, is required to remain under the care of health professionals and comply with the instructions and requirements of the health authorities.

f. Teachers, staff or administrators who may have contact with a COVID-19 suspect or patient are required to self-isolate at home and to place suspected or diagnosed students in an on-campus isolation center and properly follow-up in collaboration with relevant health facilities and trained health professionals.

g. Any diagnosed COVID-19 patient should be treated and monitored only at off campus health facilities.

h. Any member of the Education and Training Institute community who suspects he/she may have contracted the virus or suspects someone on campus may have the virus has the obligation to report the case to any task force member organized for this purpose. Similarly, the Education and Training Institute is required to



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

ቀ. ማንኛውም ወደ የትምህርትና ሥልጠና ተቋም አገልግሎት ለማግኘት የሚመጡ ተገልጋዮች በዚህ መመሪያ መሰረት ቫይረሱን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን የመጠቀም፣ አፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የማድረግ፣ በአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ሁለት የአዋቂ እርምጃ ተራርቀው የመቆም ወይም የመቀመጥ ግዴታ አለባቸው::

በ. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ተገልጋዮች አንድ ሜትር ተራርቀው የሚቆሙበትን ቦታ ምልከት የማድረግ የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፣

25) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም የትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጥ በህግ በተወሰነው የመጫን አቅም ልክ ሰዎችን የመጫን፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ያላደረጉ ሰዎችን አገልግሎት ያለመስጠት፣ ተሽከርካሪውን ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ በጸረ-ተህዋሲያን ኬሚካል ወይም ቴክኖሎጂ የማጽዳት፣ መስኮቶችን በመክፈት በተሽከርካሪው ውስጥ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር የማድረግ እና በዘርፉ በመመሪያ የሚወጡ ሌሎች መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የመተግበር ግዴታ አለበት::

26) በትምህርትና ሥልጠና ተቋም ግቢ ውስጥ የሚገኙ የገንባታ ፕሮጀክት አሠሪዎች በግንባታ ሳይቶች ላይ አስፈላጊውን ንጽህና ለመጠበቅ የሚረዱ እንደ ውሃ፣ ሳሙና፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ፣ ሳኒታይዘር ወይንም አልኮል፣ የሙቀት መለኪያ መሳሪያ እንዲሁም የጸረ ተህዋሲያን ግብዓት የማቅረብ ወይንም የማሟላትና የመጠቀም፣ ሰራተኞቻቸው በተቻለ መጠን ርቀታቸው ጠብቀው እንዲሰሩ የማድረግ፣ በግቢ ውስጥ የሚኖራቸውን ለንኪኪ የሚያጋልጡ እቅስቃሴዎችን የመገደብ እንዲሁም በኮንስትራክሽን ዘርፍ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተጋላጭነትን ለመከላከል፣ ዝግጁነት ለማረጋገጥና ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታን በተመለከተ የሚወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች የማክበር እና የማስከበር ግዴታዎች አለባቸው::

27) ማንኛውም በትምህርትና ሥልጠና ተቋም ውስጥ የምግብ ቤት፣ የሱፐር ማርኬት፣ የሱቅ፣ የውበት ሳሎን፣ የፎቶ ኮፒና የጽሕፈት መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አካላት በሰራተኞቻቸው እና ተገልጋዮቻቸው መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ወይም የሁለት ሜትር ርቀት እንዲኖር የማድረግ፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን የመቆጣጠር፣ በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን የማዘጋጀት፣ ለሰራተኞቻቸው የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን የማቅረብ፣ በአንድ ጠረጴዛ ከሶስት ሰው በላይ አለማስቀመጥ ሌሎች በአገልግሎቱ ዘርፉ የሚወጡ መመሪያዎችን የመተግበር ግዴታ አለባቸው።

28) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ኮቪድ-19ን ምክንያት በማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱና ጥራቱ እንዳያስተጓጉል፣ በተማሪዎችም ላይ አላስፈላጊ ጫና እንዳይፈጠር የተቋሙ አቅምና ነባራዊ ሁኔታ በፈቀደ መጠን አገልግሎቱን የማመቻቸትና ክትትል የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት::

report the case to the Ministry of Health, the Ethiopian Institute of Public Health, the nearest health facility or health professionals, in a timely manner.

i. In accordance with this Directive, all service recipients and providers who come to the Education and Training Institutions are required to use hygienic materials to prevent the spread of the virus, and while waiting for service to stand or sit at least two feet from the next individual.

j. Every Education and Training Institution has the obligation to monitor and ensure service recipients stand apart by marking one-meter distances on surfaces.

25) When any Education and Training Institution provides transportation services, do not exceed the legal capacity for loading people; do not provide services to people who do not use masks properly; cleaning the vehicle at least twice a day with antimicrobial chemicals or technology, opening windows and providing adequate ventilation is required. It is also mandatory to take other precautionary measures as directed.

26) Construction project workers on the premises shall provide water, soap, mask, sanitizer or alcohol, thermometer and anti-bacterial cleaners to maintain the necessary hygiene at the construction sites. They have the duty to respect, enforce, and take key precautionary measures to prevent exposure, ensure readiness, and respond to exposure as needed.

27) Any person operating campus food services, shops, photocopy services and stationeries shall ensure that all employees and clients stand at least two meters apart from each other and that all wear masks and take the necessary measures to prevent the disease. No more than three persons may sit at any table with other precautionary measures taken to prevent the spread of the disease.

28) Any Education and Training Institution shall have the responsibility and obligation to facilitate and supervise its services to the extent possible in order to ensure that the teaching and learning process is not disrupted and that unnecessary pressure is not placed on the students.

Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

29) ማንኛውም ተቋም የመማሪያ፣ የማደሪያ፣ የቤተ-ሙከራ፣ የወርክሾፕ፣ የቤተ-መጽሐፍት፣ የምግብ ቤት፣ የክሊኒክ፣ የለይቶ ማቆያ ማዕከል...ወዘተ ሕንጻዎች ጥገና ኮቪድ-19 የመከላከልና የጥንቃቄ ተግባራትን ታሳቢ በማድረግ ተማሪዎችን መልሶ ለመቀበል ጥሪ ከማድረጉ በፊት የማጠናቀቅ ግዴታ አለበት።

30) ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም በተረጋገጠና ዕውቅና ባለው ከተህዋሲያን ማጽጃ ኬሚካል ወይም ቴክኖሎጂ ግቢውን፣ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትንና ማደሪያና መማሪያ ህንጻዎችን፣ ቤተ-ሙከራና ዎርክሾፖችን፣ ሌሎች የጋራ መገልገያ ሕንጻዎችንና ቦታዎችን ተማሪዎች ወደ ተቋሙ ግቢ ከመግባታቸው በፊት የማጽዳት ግዴታ አለበት።

31) የተማሪዎች ቅበላ ጥሪ

ሀ. ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለመልሶ ቅበላ የተማሪዎች ቅበላ ጥሪ ከማድረጋቸው በፊት ቅድመ ዝግጅታውን በአግባቡ ስለማጠናቀቃቸው ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ወይም ውክልና ከተሰጠው አካል ፈቃድ የማግኘት ግዴታ አለበት።

ለ. ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም የተማሪዎች ቅበላ ጥሪ ማድረግ የሚችለው የተማሪዎችን ብዛትና የተቋሙን መሠረተ ልማት ታሳቢ በማድረግ ቢያንስ በሶስት ዙር ነው። በልዩ ሁኔታ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ካልተፈቀደ በስተቀር ለመልሶ ቅበላ ሁሉን ተማሪዎች በአንድ ጊዜ መጥራት የተከለከለ ነው።

32) የተሟላ መረጃን ተደራሽ ማድረግ

ሀ. ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ተማሪዎች ኮቪድ-19 ለመከላከል በግቢ ውስጥ ስለሚደረጉ ጥንቃቄዎች በቂ መረጃ እንዲኖረው የተለያዩ የመረጃ መንገዶችን በመጠቀም ተደራሽ ማድረግ ይኖርበታል።

ለ. እንደተቋሙ ነባራዊ ሁኔታ ለሁሉም ተማሪ በጽሑፍ የተዘጋጀ አጭር ኮቪድ-19ኝን ለመከላከል የሚያስችሉ የጥንቃቄ መልዕክቶችን የየዘ ጽሑፍ በበየነ መረብ እንዲደርስ ማድረግና በየተማሪዎቹ ዶርም ውስጥ በቋሚነት መለጠፍ ይኖርበታል።

ሐ. በተማሪዎች ጥሪ ወቅት በጉዞና በግቢ ውስጥ በአጠቃላይ ማድረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች በሁሉም የመገናኛ መንገዶች በተለይም በተቋሙ በየነ መረብ ላይ ዝርዝር ጉዳዮችን እንዲያውቁ የማድረግ ግዴታ አለበት።

33) የግቢ መግቢያ በር ፍተሻ

ሀ. ማንኛውም ፈታሽ የእጅ ጓንት፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የማድረግ ግዴታ አለበት።

ለ. ተማሪዎች ወደ ግቢ ሲገቡ የያዙትን ሻንጣ በራሳቸው እየከፈቱና በውስጡ ያሉትን ዕቃዎችና አልባሳት በዝርዝር ለሚፈትሽ ሰው እንዲያሳዩ የአካል ንኪኪ በማይኖር መልኩ መከናወን አለበት።

29) Facilities including dormitories, laboratories, workshops, libraries, cafeteria, clinics, isolation centers, etc. shall first be renovated and ready for service prior to announcing readiness to enroll students.

30) All Educational and Training Institutions are required to thoroughly clean service centers, dormitories, laboratories, workshops, and other common facilities with anti-bacterial disinfectors prior to students and staff enter the premises.

31) Student Admissions

a. All Education and Training Institutions must obtain permission from the Ministry of Science and Higher Education or its delegated body by completing the pre-preparation process prior to enrolling students.

b. All Education and Training Institutions can only call for admission after taking careful review of its size and readiness of its infrastructure. When certified to open, it may call in its students in three rounds. It is forbidden to call all students at the same time, unless otherwise permitted by the Ministry of Science and Higher Education.

32) Providing complete information

a. All Education and Training Institutions should use a variety of information modalities to ensure that students and staff have clear, adequate and timely information on campus protection against COVID-19.

b. Depending on the prevailing situation, a written version of COVID-19 prevention and protection information should be posted on the institution's website and sufficient COVID-19 related information should be posted regularly in each dormitory.

c. As students are invited to their campuses, Institutions have the obligation to inform students on what they should be aware of and the precautionary measures they are required to take during their travel. Such information should be provided on campus in all media, especially on the institution's website.

33) Campus entrance inspection:

a. Any entrance inspector should wear hand gloves and proper masks.

b. When students enter the campus, they must open their own luggage themselves and show it to the inspector in detail.



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

ሐ. የግድ በፈታሽ እጅ መታየት ያለባቸው ሆኖ ሲገኝ ፈታሽ ግለሰብ ለእያንዳንዱ ፍተሻ የእጅ ማጽጃ ሳኒታይዘር ወይም 70 በሙቶ የሆነ አልኮል በመጠቀም ወይም ለአንድ ተማሪ ፍተሻ አንድ ጓንት በመጠቀም የሚፈትሽ ይሆናል፡፡

መ. የተማሪ መታወቂያን ማሳየትን በሚመለከት በሪጅስትራርና በትምህርት ክፍል በጋራ የተረጋገጠ የተማሪዎች ስም ዝርዝር መሠረት ተማሪዎች መታወቂያቸው እያሳዩ የሚገቡ ይሆናል፡፡

ሠ. ማንኛውም ተማሪ መታወቂያውን ለፈታሽ ወይም ለጠየቀው ህጋዊ አካል በግልፅ የማሳየት እንጂ በእጅ አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

ረ. የዲሲፕሊን ክስ ወይም ሌላ የተማሪውን መታወቂያ የሚፈልግ ጉዳይ ሲያጋጥም መታወቂያን ሳይቀበሉ የተማሪውን ሙሉ ስምና መታወቂያ ቁጥር በመጥቀስ ወይም አማራጭ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚፈጸም ይሆናል፡፡

ሰ. ማንኛውም ሰው ወደ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ግቢ ሲገባ የሰውነቱ ሙቀት በሙቀት መለኪያ መሣሪያ የሚለካ ሲሆን የልኬቱ ውጤት ወደ ኮቪድ-19 ጥርጣሬ የሚያመራ ከሆነ ከትንሽ ቆይታ በኋላ በድጋሚ ብመለካት አሁንም ሙቀቱ ከፍ ብሎ የሚገኝ ከሆነ በለይቶ ማቆያ ማዕከል የመቆየት ግዴታ አለበት፡

34) የምዝገባ ዝግጅት

ሀ. የተቋሙ ሪጅስትራር ከትምህርት ክፍሎች ጋር የተናበበና የተጣራ በትምህርት ላይ የሚገኙትን የተማሪዎች ዝርዝር ቀድሞ በማዘጋጀት የትምህርት ክፍላቸውን፣ መታወቂያ ቁጥራቸውን፣ የትምህርት ዓመታቸውን፣ ጾታ እና መሰል መረጃዎችን በሚገልጽ መልኩ በማዘጋጀት በተፈረመ ሽኝ ደብዳቤ በሁሉም ገጾች ማህተም ያረፈበትን መረጃ በበየነ መረብ ለተማሪዎች፣ ለተማሪዎች አገልግሎት፣ ለግቢ ጥበቃና ደህንነት እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

ለ. በተለያዩ ምክንያቶች በተቋሙ ተመዝግው ትምህርትና ስልጠና መቀጠል የማይችሉትንና የሌለባቸውን ተማሪዎች ቀድሞ ለይቶ ለተማሪዎች አገልግሎት፣ ለግቢ ጥበቃና ደህንነት እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስና ተማሪዎቹም እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

ሐ. በተለያየ ምክንያት ውሳኔ ያላገኙና በውጤት ማነስ ምክኒያት መመዝገብ የማይችሉትን ተማሪዎች ለይቶ ለመልሶ ቅበላ የተማሪ ጥሪ ከመደረጉ በፊት በሚመለከተው አካል ውሳኔ አግኝቶ ተማሪዎቹም ቀድመው እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

መ. የተማሪዎች ወደ ግቢ ከመምጣታቸው በፊት ባሉበት ቦታ ሆነው የተሟላ ምዝገባ ማድረግ እንዲችሉ የሚማሩበትን የኮርስ ዝርዝር የያዘ መመዝገቢያ ፎርማት (Registration Slip) በማዘጋጀት በተቋሙ ድረ ገጽ ላይ መቀመጥ ወይም በበየነ መረብ አማራጮች ለተማሪዎች እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

ሠ. የሪጅስትራሩ አጠቃላይ አሠራሮች በእጅ የሚቀባበል የወረቀት አሠራርን ያስወገደ ወይም የቀነሰ መሆን አለበት፡፡

c. When it is necessary for the inspector to personally inspect persons, the examiner must use hand sanitizer or 70% alcohol solution for frequent hand rub or wear separate gloves for each person.

d. Students will be required to present their student ID and will be permitted to enter the campus in accordance with the certified name list jointly provided by the Registrar and Institution's Academic Unit.

e. Students are required to present and show their student IDs to inspectors, but it is forbidden for students to hand over their IDs to inspectors for health reasons.

f. In the event of a disciplinary complaint or other matters requiring student IDs arise, it is sufficient to record student's name and ID no or to use relevant technology for the same.

g. At entrance points, student and staff body temperature shall be taken. If the result show possible symptoms, the individual shall be quarantined or taken to isolation centers.

h. At entrances of Education and Training Institutions, clearance certificates students and staff may possess will be investigated for authenticity.

i. Anyone who enters an Education and Training premises and does not possess clearance certificate will be quarantined or placed in isolation centers.

34) Registration readiness

a. The Registrar, in concert with the academic unit, shall prepare an official list of students by classroom, ID number, completion status, gender, and similar information and make it available online to students, student services, campus security and other stakeholders.

b. The list of students who are unable to enroll in the institution for any reason and who are unable to continue their education should be forwarded to student services, campus safety and security. The affected students should also be informed of their status.

c. When sending invitations, only students who can register should be invited. Cases of those who have registration questions should first be reviewed by the appropriate body and decisions made prior to being invited. Students with pending status must be informed before they make travel arrangements.

d. Electronic registration slip should be made available on the institution's website or online so that students can electronically enroll before they arrive on campus.

e. General registration procedures should reduce or eliminate paper or manual operations.

35) ምዝገባ

ሀ. የተማሪዎች ምዝገባ በበየነ መረብ መካሄድ አለበት፡፡

ለ. የተደራጀ የተማሪዎች ምዝገባ ማካሄጃ ቴክኖሎጂ የሌላቸው ተቋማት ወይም ለመጠቀም የሚቸገሩ ተማሪዎች ቢኖሩ በተለያዩ የበየነ መረብ መገናኛ (ኢ-ሜይል፣ ቴልግራም፣ ፌስ ቡክ፣ ዋትስ አፕ…ወዘተ) አማራጮች በመጠቀም በተጣራው የስም ዝርዝር መሠረት የምዝገባ ፎርሙን በመሙላት እንዲመዘገቡ መደረግ አለበት፡፡

ሐ. ተማሪዎቹም ሲመዘገቡ ስማቸው በተጣራው ዝርዝር መሠረት መመዝገብ በሚችሉ ተማሪዎች ዝርዝር ውስጥ መኖሩን በማረጋገጥ ወደ ግቢ ከመምጣታቸው በፊት መመዝገብ አለባቸው፡፡

36) መታወቂያ

ሀ. የመታወቂያ ዕድሳትም ሆነ ቅያሪ አገልግሎት የሚሰጠው ተጠሪቶ ምዝጋባ ላካሄዱ ተማሪዎች ብቻ ይሆናል፡፡

ለ. ዲጂታል መታወቂያ ያላቸው ተቋማት የመታወቂያ ዕድሳትን በተጣራው የተማሪዎች ዝርዝር መሠረት በአንድ ማዕከል በአካል መምጣት ሳያስፈልግ ያለ ንኪኪ ማደስ አለባቸው፡፡

ሐ. የመታወቂያ ደብተር የሚጠቀሙ ተቋማት አላስፈላጊ የተማሪዎች ሰልፍ መጨናነቅን ለመቀነስ የመታወቂያ ዕድሳት ወይም አዲስ መታወቂያ ዕደላ ተማሪዎቹ በሚገኙበት ትምህርት ክፍል መሆን አለበት፡፡

መ. መታወቂያ የጠፋበት ተማሪ ሲያመለከት ለአንድ ጊዜ ብቻ በትምህርት ክፍል ኃላፊ ተማሪው በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ሲማር የነበረና አሁንም መቀጠል የሚችል መሆኑን ሲያረጋግጥ በትምህርት ክፍሉ በኩል የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በድጋሚ ሲጠየቅ ግን መደበኛውን የመታወቂያ ዕድሳት ሂደት የሚከተል ይሆናል፡፡

37) የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በዕቅድ የሚመራ ግብረ ኃይል በማደራጀት የተጠናከረ የአዕምሮ-ጤና፣ የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ የምክር አገልግሎትና ድጋፍ (Mental Health and Psycho-social Support) ለተቋማቱ ተማሪዎች፣ መምህራን አስተዳደር ሠራተኞች እና የተለያዩ ሚዲዎችን በመጠቀም ለተማሪዎች ቤተሰብ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

## ክፍል ሶስት
## መማር ማስተማርና ምዘና

6. **መማር ማስተማር (የኮርስ ድልድል፣ የማስተማሪያ ግብዓቶች ዝግጅትና የትምህርትና ስልጠና አሰጣጥ)**

1) ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ኮቪድ-19ን የመከላከል ቅድመ-ሁኔታዎችንና ልዩ የመማር ማስተማር ፕሮግራምን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተማሪዎችን ከመጥራቱ በፊት :-

35) Registration process

a. Student registration must be done online.

b. For Institutions lacking the technology infrastructure and students who find it difficult to register online, generally available online communication options (e-mail, telegram, Facebook, WhatsApp, etc.) should be used verifying names in accordance with the official student list.

c. When enrolling, students must make sure that their names are on the official list of enrollees and complete their registration form prior to traveling to campus.

36) Student identification cards

a. ID card renewal and exchange services will be provided to registered students only.

b. Institutions with digital ID processing capabilities must renew student IDs using the verified student list, without requiring personal appearance.

c. Institutions that issue ID cards should distribute renewed IDs or issue new ones in the classroom to avoid long lines and reduce physical contact.

d. Students with lost IDs will only be given one chance by the head of the department to renew their IDs following confirmation that the student can legitimately enroll. Upon subsequent requests, the regular identification renewal process shall be followed.

37) Educational and Training Institutions are obliged to organize a task force that provides Mental Health and Psycho-social Support to students, teachers, support staff and administrators; and using various media outlets to student families.

## Part Three
## Learning, Teaching and Evaluation

6. **Learning and teaching (course allocation, preparation of teaching materials and provision of education and training)**

1) Before inviting students to campus, all Education and Training Institutions, having made adequate preparations to mitigate the covid-19 pandemic and for the teaching and learning programs shall:



Scanned with CamScanner

ሀ. በአንድ ጊዜ የተማሪ መምህር ግንኙነት ከ40 ደቂቃዎች ባልበለጠ ሆኖ የተሻሻለ የአካዳሚክ ካሌንደር ማዘጋጀት አለበት፡፡

ለ. መምህራን የሚያስተምሩትን የትምህርት ወይም የስልጠና ዓይነትና የመማሪያ ክፍል ድልድል በማድረግ ፕሮግራሙን ለተማሪዎችና ለመምህራኑ ቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡

ሐ. እያንዳንዱ መምህር/አሰልጣኝ ለሚያስተምረው/ ለሚያሰለጥነው ትምህርት/ስልጠና ዝርዝር ኮርስ አውትላይንን፣ የምዘና ዓይቶችንና ጊዜያትን በማካተት ተዘጋጅቶ ለተማሪዎች በበየነ መረብ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

2) የትምህርትና ስልጠና አሰጣጡ የተማሪዎችን እርስ በእርስና ከመምህሩ ጋር የአካል ግንኙነትን በሚቀንስ መልኩ፡-

ሀ. የኮርስ አሰጣጡ በገጽ ለገጽ፣ መምህራን በቴክኖሎጂ አማራጭ በርቀት በሚያደርጉት ድጋፍ ወይም ተማሪዎቹ በግላቸው በማንበብ በሚማሩበት አማራጮች የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ከእነዚህ ሶስት አማራጮች ውስጥ እንደኮርሶቹ ጠባይ በትምህርት/በስልጠና ክፍሉ ይወሰናል፡፡ አፈጻጸሙንም ዲኑ የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡

ለ. የኮርሱ ልዩ ባህሪይ አስገዳጅ ካልሆነ በስተቀር በቴክኖሎጂ አማራጭ በርቀት የሚደረጉ ወይም ተማሪዎቹ በግላቸው በማንበብ የሚማሩበት አማራጮች ከገጽ ለገጽ አማራጭ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ሐ. እያንዳንዱ የኮርስ መምህር ለተመደበበት ኮርስ የማስተማሪያ ሞጁሎችን፣ ማጣቀሻና አጋዥ መጽሐፍትን በሶፍት ኮፒ በጥራት በማዘጋጀት ለተማሪዎች ተደራሽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

መ. የኮርስ መምህሩ የሶፍት ኮፒ ማንበቢያ መሣሪያዎች የሌላቸው ተማሪዎችን እየለየ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ በሃርድ ኮፒ ተደራሽ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

ሠ. ማንኛውም መምህር በቀን ስምንት ሰዓት የመስራት ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡

3) መማሪያ ክፍልና የማስተማሪያ መሣሪያዎች አጠቃቀም

ሀ. ትምህርት ክፍሉ ያሉትን የመማሪያ ክፍሎች ለገጽ ለገጽ ትምህርትና ስልጠና ሲደለድል በአንድ ክፍለ ጊዜና በቀጣይ ክፍለ ጊዜ መካከል ለጽዳትና ለማናፈስ የሚሆን በቂ የጊዜ ክፍተት እንዲኖር ማድረግ አለበት፡፡

ለ. የመማሪያ ክፍል ወንበር አቀማመጥ

I. ለመምህሩ መንቀሳቀሻ የሚሆን ከመጻፊያ ሰሌዳና ከፊት ረድፍ በሚቀመጡ ተማሪዎች መካከል ቢያንስ የሁለት ሜትር ርቀት መኖር አለበት፡፡

II. ሁሉም ተማሪዎችና መምህሩ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የሚያደርጉ ስለሆነ የተማሪዎቹ የወንበር አቀማመጥ በተማሪዎቹ መካከል አንድ (1) ሜትር አካላዊ ርቀት የጠበቀ መሆን አለበት፡፡

a. Design for no more than 40 minutes at a time for student teacher interactions.

b. Teachers should inform students about the type of education/training they are teaching and the classroom designation.

c. Each instructor / trainer should prepare a detailed course outline for the course he / she is teaching, including assessment types and schedules, and make them available to students online.

2) Educational and training delivery method should be designed to minimize physical interactions between teachers and students as well as between students:

a. Course delivery will be provided on a face-to-face basis, with teacher support and distant technology options, and where students get to read individually. Of these three options, depending on the nature of the course, the education department shall determine the option to be employed. The dean is responsible for monitoring the performance and success of the course.

b. Unless the specific nature of the course makes it difficult, technology-supported and student independent learning options must take priority, avoiding the face-to-face option.

c. Each teacher should prepare instructional modules, references and textbooks in soft copy for the assigned course and make them accessible to students.

d. The teacher is responsible for identifying students who do not have access to soft copy materials and making them available in hard copy with due care.

e. On workdays, every teacher is required to work eight hours a day.

3) Classroom and use of teaching materials

a. In scheduling classrooms, there must be at reasonable time gap between classes to allow for cleaning and ventilation between sessions.

b. Classroom seating layout

I. There should be a distance of at least two meters between the wall and the front row for teacher movement

II. Given that all students and the teacher wear mask, each student should sit at least one meter away from the next student.



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Scanned with CamScanner

III. አንድ መማሪያ ክፍል የሚይዘው የተማሪዎች ብዛት የክፍሉን ስፋት ታሳቢ አድርጎ፣ በተማሪዎች መካከል አንድ ሜትር ርቀትን ጠብቆ፣ በቂ የአየር ዝውውር ያለው፣ አፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ሁሉም ተማሪ አድርጎ እስከ ተገኘ ድረስ በክፍሉ ስፋት ልክ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሐ. ማንኛውም ወደመማሪያ ክፍል የሚገባ መምህርና ተማሪ ከመግባቱ በፊት እጁን በሳሙና በአግባቡ በተዘጋጀው መታጠቢያ ቦታ መታጠብና በመማሪያ ክፍል ውስጥም አፍና አፍንጫውን በማስክ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡

መ. የመማሪያ ክፍሎች በርና መስኮት በመማር ማስተማር ወቅት ክፍት መሆን አለባቸው፡፡ መምህሩም በቂ የአየር ዝውውር መኖሩን እና ሁሉም ተማሪዎች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ በአግባቡ ማድረጋቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

ሠ. በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምንም ዓይነት አካላዊ ቅርርብ እንዲኖር የሚያደርግ የቡድን ውይይት ወይ የቡድን ሥራ የተከለከለ ነው፡

ረ. ማንኛውንም ተንቀሳቃሽ የማስተማሪያ መሣሪያ (ኤል ሲዲ፣ ፖይንተር፣ ዳስተር፣ ኮምፒዩተር...ወዘተ) በጸረ-ተህዋሲያን ወይም በሌላ ቴክኖሎጂ ሳይጸዳ በእጅ መቀባበል የተከለከለ ነው፡፡

ሰ. በመማሪያ ክፍል ተገጥመው የሚገኙትን ማንኛውንም የማስተማሪያ መሣሪያዎችን (ስማርት ቦርድ፣ ኤል ሲዲ፣ ...የመሳሰሉትን) ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማጽዳትም ሆነ መነካካት ክልክል ነው፡፡

ሸ. የመማሪያ ክፍሎችን መዝጋትና መክፈት ለዚሁ በተቋሙ በተመደቡ ሠራተኞች ብቻ የሚከናወን መሆን አለበት፡፡ የግዴታ ሲሆን የእጅ ጓንት በማደድረግና ፀረ-ተህዋሲያን ማጽጃ ኬሚካል በመጠቀም መዝጋትና መክፈት ይቻላል፡፡

4) ቤተ-ሙከራና ወርክሾፕ

ሀ. ማንኛውም ተቋም ቤተ-ሙከራና ወርክሾፖችን መሣሪያዎቹን ጨምሮ አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ በሚመች መልኩ የማደራጀትና የጸረ-ተህዋሲያን ኬሚካልን ወይም ቴክኖሎጂን በመጠቀም ተማሪዎችን ከመጥራቱ በፊት ማጽዳት ይኖርበታል፡፡

ለ. የትምህርትና ስልጠና ተቋማት መልሰው ለሚጠሩ ተማሪዎች በቂ ይሆን ዘንድ እንደአስፈላጊነቱ ተንቀሳቃሽ በሆኑ የቤተ-ሙከራና የወርክ-ሾፕ መሣሪያዎችንና ቁሳቁሶችን በመጠቀም ተጨማሪ ቤተ-ሙከራዎችንና ወርክሾፖችን ማዘጋጀት ይገባል፡፡

ሐ. ማንኛውም የቤተ ሙከራ ወይም የወርክ ሾፕ ትምህርትና ስልጠና የጋራ ዕቃዎች ላይ የሚኖረውን ንኪኪ ለመቀነስ የቤተ-ሙከራና የወርክ ሾፕ ትምህርቶች በቴክኖሎጂ ወይም በ" Simulation" በመታገዝ ለሚሰጡ ትምህርች ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡

መ. ማንኛውም ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም ለቤተ-ሙከራ ወይም ለወርክሾፕ ወይም ለሥራ ላይ ልምምድ የሚደረግ ጉዞ የተከለከለ ነው፡፡

III. Regular classrooms may hold up to their size as long as physical distance, proper mask usage and adequate ventilation can be maintained.

IV.

c. Before entering the classroom, teachers and students are required to wash their hands thoroughly with soap and water and cover their mouth and nose with masks during class time.
d. Classroom doors and windows should always be open during class sessions. The teacher should ensure that there is adequate ventilation in the room and that all students are wearing masks during class session.
e. Class activity that encourages physical closeness or contact is prohibited.
f. It is forbidden to touch any portable teaching device (LCD, pointer, duster, compute, etc.) without first cleaning it with antibacterial or other technology.
g. It is forbidden to clean or touch any teaching equipment (Smart Board, LCD, etc.) in the classroom except for authorized persons.
h. Opening and closing of classrooms should only be done by assigned staff. When impossible to locate assigned staff, it may be opened and shut using gloves and applying chemical cleaners.

4) Laboratories and Workshops

a. All Education and Training Institutions are required to set their laboratories and workshops to allow for safe physical distancing between students. The room and equipment must be cleansed using antimicrobial chemicals or technology.
b. Mobile labs and workshops should be set up as additional labs and workshops as needed.
c. Lab and workshops should take advantage of "simulation" technology to minimize contact with shared equipment and materials.
d. It is forbidden to travel from one institution to another in search of better laboratory or workshop facility to minimize spread of corona virus.



Scanned with CamScanner

ሠ. ከአንድ የቤተ-ሙከራ ወይም ወርክ ሾፕ ትምህርትና ስልጠና ክፍለ ጊዜና በቀጣይ ክፍለ ጊዜ መካከል የጽዳትና የማናፈሻ ጊዜ መኖር አለበት::

ረ. የቤተ-ሙከራው ወይም የወርክ ሾፑ ልዩ ባህሪይ ካላስገደደ በስተቀር ሁሉም ቤተ ሙከራና ወርክ ሾፕ ክፍሎች በቂ የአየር ዝውውር ያላቸውና የጸዱ መሆን አለባቸው::

5) ቤተ-መጽሐፍት

ሀ. ማንኛውም ሰው ወደ ቤተመጽሐፍት ሲገባ እጁን በሳሙና በአግባቡ መታጠብና ቤተ መጽሐፍት ውስጥ ሁል ጊዜ አፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የማድረግ ግዴታ አለበት::

ለ. ማንኛውም ትምህርትና ስልጠና ተቋም የቤተ-መጽሐፍት አቀማመጥ አካላዊ ርቀትን የጠበቀ፣ ተማሪዎች ፊት ለፊት የማይቀመጡበት (ጀርባ ለጀርባ የሚቀመጡበት) ፣ "እዚህ ይቀመጡ" እና "እዚህ አይቀመጡ" የሚል ምልከቶች የተደረገበት መሆን አለበት

ሐ. ቤተ-መጽሐፍት በቀን ቢያንስ ሁለት ጊዜ ሙሉ በሙሉ መጽዳት አለበት:: በተለይም የማንበቢያ ጠረጴዛዎች፣ ማንኛውም እጀታዎች፣ ሰርኩሌሽን ዴስክ፣ መግቢያና መውጫ በሮችና እጀታዎቻቸው ቢያንስ በቀን ሶስት ጊዜ በጸረ-ተህዋሲያን ኬሚካል መጽዳት አለባቸው::

መ. ቤተ መጽፍት ውስጥ የክፍት ቦታዎችን ስፋት መጨመርና ሁል ጊዜ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖረው መደረግ አለበት::

ሠ. ሁሉም ተቋማት በቤተመጽሐፍት ውስጥ መጨናነቅን ለመቀነስ ሁሉም ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግና ተጨማሪ አስፈላጊው ቁጥጥር የሚደረግባቸው አማራጭ የማንበብያ ቦታዎችን ማዘጋጀት አለባቸው፡

ረ. ሰርኩሌሽን አካባቢ ያለውን መጨናነቅ ለመቀነስ መጽሐፍትን በሶፍት ኮፒ ለተማሪዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግና ልዩ የረዥም ጊዜ የመጽፍት ውሰት ስርዓት ተዘጋጅቶ መተግበር አለበት::

## 7. የምዘና ስርዓት፣ ግብረ-መልስና የውጤት አሰጣጥ

1) የተከታታይ ምዘናና ግብረ መልስ በእጅ የሚደረገውን የወረቀት ቅብብሎሽ በሚቀንስ መልኩ በኢ-ሜይል ወይም በሌላ የቴክኖሎጂ አማራጭ በመጠቀም እንዲከናወን መደረግ አለበት::

2) ምዘና ለማከናወንና ለማስተዳደር የሚያግዝ ቴክኖሎጂ አማራጭ በተቋም ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች መድረስ አለበት::

3) የተማሪዎች የመመረቂያ ጽሑፍ መረጃ ለመሰብሰብ ካለው ሁኔታ አንጻር ተጋላጭነትን ስለምጨምርና ከፍተኛ የጊዜ አጥረት ስለሚያጋጥም እያንዳንዱ ተቋም በሴኔት ጉዳዩን እንድገመግምና እንዲወሰን መደረግ አለበት::

e. There should be time gap for cleaning and ventilation between laboratory or workshop sessions.

f. Unless conditions prohibit, all laboratories and workshops must have adequate ventilation.

5) Library

a. Anyone entering the library should first thoroughly wash their hands with soap and water and wear a mouth and nose mask at all times while in the library.

b. All Education and Training Institutions must avoid close sitting arrangements and allow for back-to-back sitting arrangement. Visible signs should direct users where to sit and where not to sit.

c. Libraries should be fully cleansed at least two times each day, especially tables, handles, circulation desk table, exit and enterance door handle and handrile should be cleansed at least three times per day with antimicrobials.

d. The open spaces in the library should be widened and there should always be adequate ventilation.

e. Additional supervised study facilities should be made available to offload regular libraries in order to reduce congestion.

f. To reduce congestion around the circulation desks, soft copies of books should be made available to students and arrangements should be made for students to checkout library books for longer periods of time.

## 7. Evaluation system, feedback and grading

1) Continuous evaluation and feedback should be done over e-mail or using other technologies to minimize manual paper handling.

2) Technology options should be developed by Institutions and be made available to users to better employ and manage the assessment program.

3) Required graduation research study should be reviewed and determined by the Senate in order to reduce the time requirement and avoid data collection related health risks.



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

4) የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ የትምህርትና ስልጠና ጊዜውንና አሰጣጡን ያዛባው በመሆኑ ልዩ ወይም አዲስ የተማሪዎች ምዘና ውጤት አሰጣጥ ስርዓት ወጥቶ በሴኔት ጸድቆ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

### ክፍል አራት
### የተማሪዎች አገልግሎት

**8. የተማሪዎች አገልግሎት**

1) የተማሪዎች ምግብ ቤት

ሀ. የመግብ ቤት ሰልፍ ተማሪዎች ርቀታቸውን ጠብቀው የሚሰለፉበት በየሁለት ሜትሩ የተደረገ ምልክት መኖር አለበት፡፡

ለ. በምግብ ቤት ሰልፍ ላይ መጨናነቅ ለመቀነስ ሁሉም ምግብ ቤቶች በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ማደረግ አለበት፡፡

ሐ. ምግብ ቤት ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ መጽዳትና በቂ አየር ዝውውር እዲኖረው መደረግ አለበት፡፡ የምግብ ቤት ጠረጴዛ በማጽጃ ኬሚካል ወይም በ70 በመቶ አልኮል መጽዳት አለበት፡፡

መ. የምግብ ቤት አገልግሎት መስጫ ሰዓት

I. ቁርስ 12፡30 – 2፡30 ሰዓት፣

II. ምሳ 5፡30 – 7፡30 ሰዓት እና

III. እራት 10፡30 – 1፡00 ሰዓት እንዲሆን ይመከራል፡

ሠ. የካፌ ቲከሮችና ስነ-ስርዓት አስከባሪዎች አገልግሎት ሲሰጡ ለአንድ የምግብ ክፍለ ጊዜ አንድ የእጅ ጓንትና የፊትና የአፍ መሸፈኛ ማስክ መጠቀም አለባቸው፡፡

ረ. የእጅ ንኪኪን ለመቀነስ ሲባል ተማሪዎች የምግብ መመገቢያ ካርዳቸውን ለካፌ ቲከሮችና ስነ-ስርዓት አስከባሪዎች በግልጽ ማሳየት እንጂ አሳልፈው መስጠት የለባቸውም፡፡ ለዚህም በየቀኑ ፕሪንት የሚደረግ የተማሪ መለያ ቁጥርን በመጠቀም የቁጥጥር ሥራዉን ማከናወን ይቻላል፡

ሰ. የተማሪዎች ምግብ ቤት የወንበር አቀማመጥ አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ የሚያስችልና አንዱ ተማሪ ለሌላው ተማሪ ጀርባውን ሰጥቶ የሚቀመጠበት ሆኖ መደራጀት አለበት፡

ሸ. በአንድ የምግብ ሰዓት ለአንድ ተማሪ አንድ የምግብ መብያ ሳህን/ትሪ፣ የውሃ/ሻይ መጠጫ ኩባያ፣ ማንኪያ/ሹካ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ በአንድ የምግብ ሰዓት ምግብ መብያ ቁሳቁሶችን አጥቦ መልሶ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

ቀ. የምግብ አዘጋጆች፣ አቅራቢዎች፣ አስተናጋጆች እና ምግብ ቤት ጽዳት ሠራተኞች አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ ሁሉ የእጅ ጓንት የማድረግ፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የማድረግና ጸጉር መሸፈኛ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ይንንም የሚቆጣጠር በተቋሙ የተመደበ አካል መኖር አለበት፡፡

4) Since the current situation has distorted the timing and delivery of education and training, a special or new student assessment and grading system should be developed and approved by the Senate.

### Part Four
### Student Services

**8. Student Services**

1) Student Cafeteria

a. For student queuing, two-meter marks should be placed on the ground to keep students at safe distances.

b. To reduce congestion in cafeteria queues, cafeterias should operate at full capacity.

c. Cafeterias should be cleansed and ventilated at least twice a day. The dining room table should be cleansed with disinfectants /sodium hypochlotite / calcium hypochlorite/ hypochlorous acid or 70% alcohol detergent.

d. Recommended cafeteria service hours

I. Breakfast - 6:30 - 8:30am

II. Lunch - 11:30 - 1:30pm, and

III. Dinner - 4:30 - 7:00pm

e. Cafeteria tickers and etiquette attendants should wear one pair of gloves and face mask for meal session.

f. To minimize hand contact, students should clearly display their dining card to cafe tickers and attendants, but not hand it over. This can be done by printing new student ID number for each day.

g. Student cafeteria sitting should be designed to maintain physical distance and where students can sit back-to-back with each other.

h. For each meal, one meal tray, water /teacup, spoon/fork should be provided per student. It is prohibited to wash and reuse utensils at same meal.

i. Caterers, waiters and cafeteria janitorial workers are required to wear gloves, mouth and nose masks and hair masks throughout service hours. Supervisors must be assigned to monitor compliance.



Scanned with CamScanner

በ. የምግብ ግብዓት አቅራቢዎች ኮቪድ-19 ለመከላከል የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን የመተግበር ግዴታ አለባቸው፡፡

ተ. ምግብ ቤቶች የምግብ ግብዓቶች የማይበላሹበትን ጊዜን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ቀድሞ በበቂ መጠን ማከማቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ቸ. ከምግብ ቤት ምግብ ማውጣት የተከለከለ ነው፡፡

ኀ. ከአንድ የምግብ ከፍለ ጊዜ በኃላ የምግብ ማዘጋጃና ማቅረቢያ እንዲሁም የመመገቢያ ዕቃዎችን ከተጠቀሙ በኋላ በሳሙና በማጽዳት ከዚያም በ0.5% በረኪና ዉህድ ለ 10 ደቂቃ ከዘፈዘፉ በኃላ በዉሃ ማለቅለቅ የግዴታ ነው፡፡

2) የተማሪዎች ክሊኒክ

ሀ. ለደረጃው የሚሆን በቂ ባለሙያ፣ መድኃኒት እና የህክምና መስጫ መሳሪያዎች ያለውና አገልግሎት መስጠት የሚችል ክልኒክ መደራጀት አለበት፡፡

ለ. በጤና ሚኒስቴር የወጡ በጤና ተቋማት ለኮቪድ-19 መከላከል የሚደረጉ ጥንቃቄዎች መተግበራቸውን ተቋሙ ያረጋግጣል፡፡

ሐ. በየዕለቱ የታከሙ ተማሪዎችን የተሟላ መረጃ ለሚመለከታቸው ማቅረብ ያለበት ሲሆን መረጃዎቹም ከኮቪድ-19 አንጻር የተተነተኑ መሆን አለባቸው፡፡

መ. ማንኛውም የኮቪድ-19 ምልከት የታየበት ታካሚ ሲኖር ወዲያውኑ ለሚመለከታቸው በማሳወቅ ክትትል እንዲደረግ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የኮቪድ በሽታ ምልከቶችን ያሳየ ታማሚ ባይኖር እንኳን በየእለቱ ለለሚመለከታው ጤና ተቋማት "ዜሮ ሪፖርት" ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ሠ. ታካሚዎች ርቀታቸውን ጠብቀው አፍና አፍንጫ መሸፈኛ አድርገው እንዲታከሙ ያደርጋል፡፡

ረ. እንደአስፈላጊነቱ ሜዲስንና የጤና ሳይንስ ትምህርት ክፍል ያላቸው ተቋማት መምህራኑ መምህራኑ በክሊኒኩ ውስጥ በህክምና ስራው የሚሳተፉበትን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ወይም ሌላ አሠራር መዘርጋት ይችላሉ፡፡

3) የተማሪዎች የዶርም ምደባና አኗኗር

ሀ. የዶርም ምደባ ህብረ-ብሔራዊ ሆኖ አስቀድሞ ተማሪው ከመጠራቱ በፊት ተጠናቆ ተማሪዎቹም በበየነ መረብ እንዲያውቁ መደረግ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተመሳሳይ ትምህርት ክፍል (አንድ መማሪያ ክፍል፣ ቤተ ሙከራ፣ ወርክሾፕ የሚጠቀሙ) እና ተመሳሳይ የትምህርት ዓመት የሆኑ ተማሪዎች ተመሳሳይ ብሎክና ዶርም ውስጥ እንዲመደቡ መደረግ አለበት፡፡

ለ. የተማሪዎች የዶርም ቁልፍ ርክክብ የእጅ ንኪኪ በማይኖርበት ሁኔታ መፈጸም አለበት፡

ሐ. በዶርም ውስጥ መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

I. ማንኛውም ጠረጴዛ በዶርም ውስጥ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡
II. ተማሪዎች ወደ ዶርም ሲገቡ ወጪ የተጠቀሙትን ጫማቸውን ከዶርም ውጪ ማጽዳት አለባቸው፡፡
III. ተማሪው የሚያድርበትን ዶርም በየቀኑ ማጽዳትና ከፍት አድርጎ ማናፈስ አለበት፡
IV. በአንድ ዶርም ቢበዛ ከዶርሙ የማስተናገድ አቅም 1/3ኛ ተማሪ ብዛት መመደብ አለበት፡፡
V. በተማሪዎቹ መካከል ሁለት ሜትር ርቀት መጠበቅ ከተቻለና በቂ የአየር ዝውውር ማድረግ የሚችልበት ዶርም ከሆነ የዶርሙ ስፋት መያዝ የሚለውን ያክል ተማሪ በአንድ ዶርም መመደብ ይቻላል፡፡

መ. ማንኛውም ተማሪ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የራሱ ወዳልሆነ ዶርም መግባት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

j. Food suppliers are required to take precautionary measures to mitigate the COVID-19 epidemic.

k. Cafeterias must prepare and store sufficient supply of food without the risk of spoilage.

l. Taking food out of the cafeteria is prohibited.

m. After each meal session, food preparation equipment should be thoroughly cleansed with antimicrobial chemicals or technology.

2) Student Clinic

a. A fully functioning student clinic should be established with sufficient health professionals, medicines and medical equipment.

b. All Institutions should ensure that their health clinics comply with all Ministry of Health issued precautionary measures against COVD-19.

c. Complete records on Covid-19 treated students must be provided to appropriate authorities with proper analysis of the data.

d. All student clinics will carefully monitor and immediately notify appropriate authorities if CV-19 symptoms are detected or one is diagnosed with the Corona virus.

e. The student clinics will maintain the required physical distances between patients while under their care at the clinic.

3) Dorm assignment and residence

a. Dorm assignment should be finalized before students are invited and the students should be informed of their assignment online. Students with the same department and batch should be assigned to the same blocks and dormitories.

b. Dorm room key handover must be accomplished without hand or physical contact.

c. Precautions to be taken in the dormitory

I. It is prohibited to place tables in the dorm.
II. Students should clean their shoes outside the dormitory building prior to entering the building.
III. Student must clean and ventilate the dorm room daily.
IV. For each dorm room, at most, one-third of the regular room capacity may be assigned.
V. Students can be allotted to the capacity of the dormitory room size under the circumstances where 2meter distance b/n students, and well ventilation of the room can be maintained.

d. It is strictly prohibited for students to enter a dorm room other than their own at any time.



Scanned with CamScanner

ሠ. ማንኛውም ተማሪ መጀመሪያ ከተመደበበት ዶርም ወደሌላ ዶርም ማዛወር አይቻልም፤ ሆኖም በህመም ወይም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ በተማሪዎች አገልግሎት ዳይክተር ተጠይቆ በዘርፉን በሚመራ ምክትል ፕሬዚዳንት ሲጸድቅ ማዛወር ይቻላል:

ረ. ማንኛውም ተማሪ የተጠቀመበትን መጸዳጃና ሻወር ቤት ማጽዳት አለበት::

ሰ. የመኖሪያ ህንጻ ኮሪደሮችና የህንጻው ዙሪያ በተቋሙ በተመደበ አካል መጽዳት አለበት:

ሸ. በተማሪዎች መኖሪያ ህንጻ ውስጥ ያሉ ዲ ኤስ ቲቪ ወይም የቴሌቪዥንን ከፍሎች በቂ አየር የሚዛወርባቸው፣ መደበኛ ጽዳት የሚደረግላቸው፣ አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ የሚመች የወንበር አቀማመጥ ያላቸው እና ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቦታው ወይም አዳራሹ ሊይዝ ከሚችለው 1/4ኛ ሳይበልጥ መሆን አለባቸው::

ቀ. ማንኛውም ተማሪ ከአንድ ብሎክ ወደ ሌላ ብሎክ መሄድ የተከለከለ ነው::

4) የእጅ መታጠቢያ፣ የምግብ ትራፍ እና የቆሻሻ አወጋገድ

ሀ. የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በሁሉም ግቢዎች ውስጥ ግቢ መግቢያ በር፣ በመማሪያ ከፍሎች፣ በተማሪዎች ማደሪያ ሕንጻ መግቢያ በር፣ ቤተ-መጽሐፍት መግቢያ፣ ክሊኒክ መግቢያ፣ ቤተ-ሙከራና ወርክሾፕ መግቢያ፣ ግቢ ውስጥ ባሉ ምግብ ቤቶች መግቢያ፣ የተማሪዎች መዝናኛ ቦታዎች፣ በአስተዳደር፣ የኮሌጅ፣ ፋኩልቲ፣ ትምህርት ቤት፣ ኢንስቲትዩት እና የትምህርት ክፍሎች ህንጻ መግቢያ፣ የምርምር ማዕከላት መግቢያ እና ሌሎች የግቢ ማህበረሰብ እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው ቦታዎች አካባቢዎች ላይ ከእጅ ንኪኪ ነጻ የሆኑ የእጅ መታጠቢያዎች አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ እንዲሁም የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት የመዘርጋት ሃላፊነት አለባቸው::

ለ. የእጅ መታጠቢያዎቹ አካባቢዎች ተጨማሪ ቆሻሻ እንዳያስከትሉ በቂ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ጋር የተቀናጁ መሆን አለበት::

ሐ. የደረቅ ቆሻሻ በየወቅቱ በተደራጀ አግባብ ተሰብስቦ መወገድ አለበት:: ለዚህም በሁሉም መማሪያ ከፍሎች፣ ዶርሞች፣ ቤተ-መጽሐፍት፣ ቤተ-ሙከራዎች፣ ግቢ ወስጥ የሰው እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው ቦታዎች ሁሉ ላይ ኪዳን ያለው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቅርጫቶችን ማስቀመጥ፣ በአግባቡ ማስወገድና መልሶ ቆሻሻ ከመሰብሰብ በፊት በጸረ-ተዋህሳ ኬሚካል እንዲጸዱ መደረግ አለበት::

መ. ከተማሪዎች ክሊኒክ፣ እና ሌሎች ዶርም የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ኮቪድ-19 ለመከላከል የሚደረገውን ጥንቃቄ ታሳቢ አድርገው መወገድ አለባቸው::

ሠ. የተማሪዎች ምግብ ቤት እና ሌሎች ግቢ ውስጥ ካሉ ምግብ ቤቶች የሚወጡ ትራፊ ምግቦች ለሌላ ለማንኛውም አካል ሳይተላለፉ በጥንቃቄ መወገድ አለባቸው::

e. No student may be transferred from his or her originally assigned dorm room to another. However, in case of illness or need for special support, transfers may be requested by the Director of Student Services and approved by the appropriate Vice President.

f. Every student should thoroughly clean the toilet and shower he/she used.

g. The corridors of residential buildings and their perimeter should be attended to by assigned staff.

h. DSTV or television rooms in dormitories should be well ventilated, regularly cleaned, with chairs arranged to accommodate not greater than ¼ of its capacity, proper physical distances and must be consistently monitored.

i. It is prohibited for students to move from one building block to another.

4) Hand washing, leftover food and garbage disposal

a. All Education and Training Institutions are to provide hands-free hand washing facilities in all their campuses, entrance gates, classrooms, entrances to dormitory buildings, library entrances, clinic entrances, laboratory and workshop entrances, cafeteria entrances, student recreation areas, administration buildings, colleges, and faculty centers. Such hygiene facilities should be provided at schools, institutes and classroom buildings, research centers, and other areas where there is a high level of community activity. Such locations should be constantly monitored and controlled.

b. Handwashing areas should be equipped with adequate drainage to prevent further contamination.

c. Dry waste should be collected and disposed of in an organized manner on a regular basis. Waste baskets should be placed in all classrooms, dormitories, libraries, laboratories, and other places where there is large gatherings or activities.

d. Dry and sewage discharge from student clinics and dormitories should be removed with due care to mitigate the spread of Covid-19.

e. Leftover food from cafeterias and other campus outlets must be carefully disposed of without access to anyone else.



Scanned with CamScanner

5) የልብስ ማጠቢያ ቦታዎች ዝግጅትና ቆሻሻ አወጋገድ

ሀ. በሁሉም ከምፓስ በቂ የልብስ ማጠቢያ ቦታዎች የተማሪዎችን አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ በሚመች መልኩ መዘጋጀት አለበት::

ለ. የልብስ ማጠቢያ አካባቢዎች ንጽህናቸው የተጠበቀና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገዱ በጥንቃቄ አከባቢን በማይበከልና ተጨማሪ የንኪኪ ዕድል በማይፈጥር መልኩ የተዘጋጀ መሆን አለበት::

ሐ. በቂ የልብስ ማስጫዎችን ማዘጋጀትና አላስፈላጊ ንኪኪ እንዳይኖር ተከታታይ ቁጥጥር የሚያደርግ አካል መመደብ አለበት::

መ. ማንኛውም ተማሪ ልብስ ለማስጣት ከተፈቀደለት ልብስ ማስጫ ውጪ (ለምሳሌ ሳር ላይ፣ አጥር ላይ፣ የዶርም መስኮት እና የመሳሰሉት ቦታዎች ላይ) ማስጣት የተከለከለ ነው::

ሠ. ማንኛውም ተማሪ የተጠቀመበትን የጋራ የልብስና ጫማ ማጠቢያ ቦታ በአግባቡ ሳሙና በመጠቀም ማጽዳት አለበት::

ረ. ማንኛውም ተማሪ ልብስና ጫማ ለማጠብ የተጠቀመበትን ቁሳቁስ በአግባቡ ማስወገድ አለበት:

### ክፍል አምስት

### የኮቪድ-19 ተጠርጣሪና ታማሚ አያያዝ እና ሞት ቢከሰት ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

**9. የኮቪድ-19 ተጠርጣሪና ታማሚ አያያዝ**

1) የትምህርና ስልጠና ተቋማት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ተዘጋጅቶ የተሰጠው ምቹ የሥራ ሁኔታ የተዘጋጀለት የኮቪድ-19 ተጠርጣሪን የሚከታተል ግብረ ኃይል የማቋቋምና የአሠራር ስርአትየመዘርጋት ግዴታ አለባቸው::
2) የኮቪድ-19 ተጠርጣሪና ታማሚ ሲገኝ የጤና ሚኒስቴር ባወጣው የአሠራር ሂደት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል::
3) የግብረ ኃይሉ ተጨማሪ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በተቋሙ ይወሰናል::

**10. ማቆያ፣ ለይቶ ማቆያ እና ህክምናን (Quarantine, Isolation and Treatment)**

1) ሁሉም የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በኮቪድ-19 ለሚጠረጠሩ፣ ራሳቸውን ለሚጠረጥሩ እና የበሽታውን የተለያዩ ምልክቶችን ለሚያሳዩ ተማሪዎች የሚሆን የለይቶ ማቆያ ማዕከል በግቢ ውስጥ የማዘጋጀት ግዴታ አለባቸው:: የሚጠረጠሩ ሲገኙም ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማትና ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት የጤና ሚኒስቴር ባስቀመጠው የአሠራ ሂደት መሠረት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አለበት::

5) Laundry facilities and fluid disposal

a. Adequate laundry facilities should be made available at all campuses to accommodate required student physical distance.

b. Laundry areas should be kept clean and discharged fluids disposed of in a manner that does not pollute the environment and create unwanted contact opportunities.

c. Adequate clotheslines should be set up and staff should be assigned to monitor and prevent unnecessary contact.

d. It is prohibited for students to dry their laundry outside of the provided clotheslines (for example on the grass, fences, dormitory windows, etc.).

e. Every student should thoroughly clean the shared laundry area with soap and water.

f. Student should properly remove the materials they used to wash their clothes and shoes.

### Part Five

### Precautions to be Taken in the Care, Treatment and Death of CVD-19 Suspects and Patients

**9. Care and treatment of CVD-19 suspects and patients**

1) Education and Training Institutions are obligated to set up a task force to monitor the CVD-19 suspects, with detailed set of functions and responsibilities.
2) In the case of CVD-19 suspects and patients, their care and treatment shall be carried out in accordance with the directives issued by the Ministry of Health.
3) The detailed tasks and responsibilities of the Taskforce shall be determined by the Institution.

**10. Quarantine, Isolation and Treatment**

1) All educational and training institutions are obligated to set up isolation centers on campus for students who are suspected of having COVID-19 or have various symptoms of the disease. Individuals suspected of contracting the virus should cooperate with the relevant health facilities and professionals in accordance with the directives issued by the Ministry of Health.



Scanned with CamScanner

2) ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ማህበረሰብ አባል ኮቪድ-19 ያለበት መሆኑ በምርመራ ውጤት ሲረጋገጥ ቀላል ህመም ከሆነ በቤት ውስጥ ወይንም በተዘጋጁት ለይቶ ማቆያዎች በማቆየት ክትትል መደረግ ወይንም ደግሞ ከባድ ህመም ከሆነ ደግሞ በተለዩ የህክምና ተቋማት ውስጥ ክትትል መደረግ አለበት፡

**11. በኮቪድ-19 ምክንያት ሞት ብከሰት**

በትምህርትና ስልጠና ተቋም በኮቪድ-19 ምክንያት ሞት ብከሰት የሬሳ አያያዝ፣ ማጓጓዝና የቀብር ስነ-ስርዓት ጤና ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ 30/2013 እና በጉዳዩ ላይ በተዘጋጀ ማኑዋል መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ሂደቱም በጤና ባለሙያዎች ግብረ ኃይል ተሳትፎ የሚመራ ይሆናል፡፡

**ክፍል ስድስት**

**የባለድርሻ አካላት ሚና**

**12. ጸንተው ባሉ ሕጎች የተገለጹ ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የዚህን መመሪያ ደንጋጌዎች ለመተግበር የባለድርሻ አካላት ሚና እንደሚከተለው ይሆናል፡፡**

1) የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሚና

ሀ. የተጓደሉ የሥራ አመራር ቦርድና የተቋማት የበላይ አመራሮች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

ለ. በኮቪድ-19 ወቅትና ድህረ-ኮቪድ-19 ወቅት ትምህርትና ስልጠናን ለማስቀጠል የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችን ያወጣል፤ የተለያዩ ስልቶችን ይነድፋል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

ሐ. ለአመራር ቦርድ አባላት፣ ለክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/አመመራሮች፣ ለከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አመራሮችና ተቋማቱ ላሉበት አከባቢ አስተዳደር አመራሮች ግንዛቤ በመፍጠር ስምሪት ይሰጣል/ያስተባብራል፤

መ. የድጋፍና ክትትል ግብረ- ሃይል በማደራጀት በየተቋማቱ የተቋረጠዉን ትምህርትና ስልጠና ለማስቀጠል አስቻይ ሁኔታዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል፤ ከሚመለከታቸው የክልል ቴ/ሙ/ት/ስ/ አመራሮች ጋር በጋራ ይሰራል፤ የተደራጀ ግብረ መልስ ይሰጣል፤

ሠ. ወረርሽኙን እየተቆጣጠሩ የመማር ማስተማሩን ስራ ያለስጋት መተግበር ይቻል ዘንድ አጋሮችና ባለድርሻ አካላት ከየግል መከላከያ እና የንጽህና መጠበቂያ ቁሶች ጀምሮ ሌሎች የመማር ማስተማሩን በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ድጋፎችን ለየተቋማቱ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤

ረ. በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የተቋረጠዉን የ2012 ዓ.ም ትምህርትና ስልጠና በተያዘው ልዩ የትምህርትና ስልጠና ካሌንደር ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ለሚደረገው ርብርብ ተቋማቱ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት መንገድ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር አብሮ ይሰራል፤

2) Any member of the Education and Training community who may have contracted the Covid-19 should be assisted in their own home or isolation centers when be with mild symptoms and in treatment center whene in sever symptoms in collaboration with relevant health facilities upon verification.

**11. If death occurs as a result of covad-19**

In the event of death due to CVD-19 at Education and Training Institutions, the handling, transport and burial of bodies shall be carried out in accordance with the directives issued by the Ministry of Health. The process should be guided by the participation of health professionals.

**Part Six**

**The Role of Stakeholders**

**12. The role of stakeholders in the implementation of this Directive shall be in accordance with the functions and responsibilities specified in the applicable laws.**

1) The role of the Ministry of Science and Higher Education (MoSHE) shall be to:

a. Fill potential gaps created by managing boards and the top management of Institutions.

b. Develop legal frameworks for continuation of education and training during COVID-19 epidemic, and design various strategies and monitor their implementation and performance.

c. Provide coordination of members of the Board of Directors, regional TVET leaders, leaders of higher education and training institutions, and local administrators and leaders.

d. Establish support and monitoring Taskforce to create a conducive environment for the resumption of education and training. Collaborate with relevant regional TVET leaders and provide organized feedback.

e. Encourage partners and stakeholders to provide technical support to other institutions, including personal protective and sanitary materials, the teaching of technology so as to safely mitigate the epidemic.

f. Work with relevant government bodies to help complete the education and training work disrupted due to Covid-19 epidemic (second semester 2020).



Scanned with CamScanner

ሰ. ለሰላማዊ መማር ማስተማርና በኮቪድ-19 ወቅት የማስፈጸሚያ መመሪያ ያወጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

ሸ. የመማር ማስተማር ሂደቱን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስኬድ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ ግምገማና ከትትል ያደርጋል፡፡

ቀ. ተቋማት ተማሪዎችን መልሰ በመቀበል ትምህርና ስልጠና እንዲቀጥሉ ዝግጁነታቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ ይሰጣል፤ ዝግጁ ያልሆኑትንም በቂ ዝግጅት ሳደርጉ እንዳይቀበሉ ያግዳል፣ ከትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

**2) የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሥራ አመራር ቦርድ ሚና**

የትምህርትና ስልጠና ተቋማትን በበላይነት የመምራት ኃላፊነት የተጣለበት የየተቋማቱ ስራ አመራር ቦርድ ከተለመደው አመራር ለየት ባለ ተነሳሽነትና ትኩረት የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውን ይጠበቃል፡፡

ሀ. የሁሉም ተቋማት ሥራ አመራር ቦርድ የተቋማት የአመራር ከፍተት ያለበትን ቦታ በመለየት በተሻለ ፍጥነት ከሚኒስትሩ ወይም ከክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ አመራሮች ጋር በመመካከር በልዩ ሁኔታ የማሟላት ስራ ይሰራል፤

ለ. የሁሉም ተቋማት ሥራ አመራር ቦርድ የተቋማትን ዝግጁነት ይገመግማል፤ የራሱ የሆነ በኮቪድ-19 ወቅትና ድህረ-ኮቪድ-19 የመማር ማስተማር ስራ የሚመራበትን ልዩ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ አተገባበሩንም ይከታተላል፤

ሐ. በኮቪድ-19 ወቅት የመማር ማስተማሩን ስራ ለማስቀጠል ከተለያዩ ምንጮች ሀብት የማሰባሰቢያ ስልቶችን በመቀየስ ተቋማቱ ድጋፍ እንዲያገኙ ያስችላል፤

መ. ተቋማቱ ኮቪድ-19 ወቅትና በድህረ ኮቪድ-19 መማር ማስተማሩን ማስቀጠል የሚያስችል በዚህ መመሪያ መሠረት ማኑዋል እና ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፤ ለአፈጻጸሙም ድጋፍና ከትትል ያደርጋል፤

ሠ. ትምህርትና ስልጠናዉን በማስቀጠል ሂደት የሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮችን ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ፈጣን ምላሽ እዲያገኙ ያደርጋል፡፡

ረ. የመማር ማስተማር ሂደቱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስከሄድ የሚያስችል ተቋማዊ ሁኔታ ስለመኖሩ ይገመግማል፤የቅርብ ከትትል ያደርጋል፤

ሰ. ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ያልቻሉ አመራሮች ላይ ወቅታዊ እምጃ እርምጃ ይወስዳል፤ ሪፖርት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያቀርባል፡፡

g. Issue instructions and guidelines for the creation and implementation of peaceful teaching and learning, research and community service during the COVID-19 epidemic, and to carefully monitor the performance.

h. Evaluate and monitor the effectiveness of the teaching-learning process in a peaceful manner.

i. Certify readiness of Institutions to continue the education and training process; assist, monitor, and support those who are unprepared.

2) The Boards of Directors of Education and Training Institutions are expected lead with renewed focus and zeal and carry out the following activities with special initiatives:

a. The Board of Directors of all institutions will identify the leadership gap of institutions and consult with the Minister or the regional TVET leadership as soon as possible.

b. The Board of Directors of all institutions shall evaluate the readiness of institutions to reopen; develop its own master plan to guide the teaching and learning activities during and the post-COVID-19 epidemic; and the Boards shall monitor the implementation of its master plan.

c. The Boards shall chart the way for the continuation of the teaching and learning process during COVID-19. The Boards shall enable their institutions to gain support by developing resource mobilization strategies from various sources.

d. Boards will ensure that Institutions develop a manual and plan in accordance with this manual to enable them to continue the teaching and learning process during and the post-COVID-19 epidemic. The Boards shall also provide support and monitor for the implementation processes;

e. Boards shall work collaboratively with stakeholders and find prompt solutions to address serious challenges encountered during the COVID-19 epidemic.

f. Boards shall evaluate and closely monitor the institutional environment in which the teaching-learning process can proceed peacefully.

g. Boards shall take timely actions against leaders who fail to discharge their responsibilities and submit reports to the Ministry of Science and Higher Education.



Scanned with CamScanner

**3) የትምህርትና ስልጠና ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች ሚና**

ሀ. ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ያለው፣ ምቹ የሥራ ሁኔታ የተፈጠረለት በኮቪድ-19 ወቅት ትምህርትና ሰልጣናን ለማስቀጠል የሚከናወኑ ተግባራትን የሚከታተልና የሚደግፍ ግብረ-ሃይል ያደራጃሉ፣ ይከታተላሉ፣ ይደግፋሉ፤

ለ. በዚህ መመሪያ ለተደነገጉ የተቋማት ግዴታዎች ኃላፊነት ይወስዳሉ፤ ከተቋማዊ አደረጃጀትና አሠራር ጋር በማቀናጀት ይፈጽማሉ፤ ያስፈጽማሉ፤

ሐ. በ2012 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ዘመን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርትና ስልጠና ከመቋረጡ በፊት የኮርሶች/ሞጁሎች አፈጻጸም የነበረበትን ደረጃ በፕሮግራም፣ በትምህርት ክፍል፣ በፋኩልቲ እና በተቋም ደረጃ በጥልቀት በመገምገም ከኮርሶቹ/ሞጁሎቹ ባህርይ እንዲሁም ከጊዜ ገደብና ከሀብት (ወጪ) አንጻር የተቀናጀ ዝርዝር እቅድ በማዉጣትና የአፈጻጸም መርሃ-ግብር በማዘጋጀት እና በሴኔት በማስጸደቅና ወደ ስራ ያስገባሉ፣ ይከታተላሉ፤

መ. በ2012 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ዘመን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የተቋረጠዉን ትምህርትና ስልጠና ለማስቀጠል የተዘጋጀዉን ዕቅድና የአፈጻጸም መርሀ-ግብር እንዲሁም ይህንን መመሪያ የተቋሙ ማህበረሰብና የሚመለከታው ባለድርሻ አካላት የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙ ያደርጋሉ፤

ሠ. በ2012 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ዘመን የተቋረጠዉን ትምህርትና ስልጠና በልዩ ፕሮግራም ለማጠናቀቅ የተከለሰ ካላንደር በማዘጋጀትና በሴኔት በማጸደቅ ለሚመለከታቸዉ ሁሉ ተደራሽ በማድረግ በየደረጃው በቂ ዝግጅት መደረጉን ያረጋግጣሉ፤ ይከታተላሉ፤

ረ. በ2012 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ዘመን የተቋረጠዉ ትምህርትና ስልጠና በተቀመጠዉ መርሃ-ግብር መሰረት ለማጠናቀቅ የሚያስችል የሰዉ ሃይል (መምህራን/አሰልጣኞች፣ የላቦራቶሪ ቴክኒሽያን...) እና ሌሎች ግብዓቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣሉ፣

ሰ. ሁሉም የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በልዩ ፕሮግራም ለሚሰጡ ኮርሶች/ሞጁሎች የትምህርትና ስልጠና ጥራቱን በማይጎዳ ሁኔታ የኮርሱ ዋና ዋና የብቃት አሃዶች (Core competencies) ማስጨበጥ በሚያስችል ሁኔታ የማስተማሪያ/ዶኩሜንት ወይም አጋዥ ሌክቸሮችን ወይም ሃንዳውቶችን/ፐTLM፣ ከገላጭ ፓዎር ፖይንት ጋር በሶፍት ኮፒና በሀርድ ኮፒ እንዲያዘጋጁ እና ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋሉ፤

**3) The role of the heads of Education and Training Institutions**

a. Institution heads shall organize, monitor, and support the Taskforce to coordinate and lead activities related to the continuation of education and training during and the post-COVID-19 period. The Taskforce shall prepare detailed functions and responsible to team members and shall create favorable working conditions.

b. Heads of institutions are responsible for the implementation of institutional obligations set out in this Directive. They do so in conjunction with existing institutional structure and practices.

c. Top institutional heads shall monitor the comprehensive review of the performance of courses / modules prior to the cessation of education and training due to the COVID-19 epidemic (spring 2020) and then ensure that a comprehensive plan is developed in terms of the nature of the courses / modules as well as time constraints and resources. The Heads of institutions will ensure that plans are developed and shall review and monitor implementations of programs that are approved by the Senate.

d. The heads of institutions shall make every effort to communicate and make known the institutional plan to mitigate the COVID-19 epidemic and create common understanding on campus and among community members and relevant stakeholders.

e. Ensure that adequate preparations are made at all levels by developing a revised academic calendar and securing Senate approval to complete the education and training programs that were discontinued during the 2019/2020 academic year.

f. Ensure that the required manpower (teachers, trainers, laboratory technician, etc.) and other resources are sufficiently available to complete the education and training program that was discontinued during the 2019/2020 academic year.

g. All Education and Training Institutions shall provide tutors or tutorials, TTLM, with Description Power Points in soft and hard copies for the benefit of maintaining the Core Competencies of the course without compromising the quality of education and training.



Scanned with CamScanner

ሸ. መምህራን/አሰልጣኞች የኮረስ አዉትላይን፣ ማስተማሪያ፣ መልመጃዎች፣ ማጣቀሻና አጋዥ መጽፍትን በሶፍት ኮፒና በሀርድ ኮፒ (በድምጽ እና በምስል) እንዲያሰባስቡና ከሚስተምሩት ትምህርትና ስልጠና ጋር አደራጅተውና አቀናጅተው ለተማሪዎች ተደራሽ ማድረጋቸውን ያረጋግጣሉ፤

ቀ. ተማሪዎች/ሰልጣኞች ከተለመደዉ መደበኛዉ ፕሮግራም በአጠረ ጊዜ በሚተገበር በልዩ ፕሮግራም ትምህርትና ስልጠናቸዉን የሚያጠናቅቁ በመሆናቸው ልዩ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት እንዲሁም አካዳሚያዊ የምክር አገልግሎት በተጠናከረ መልኩ እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

በ. ከትምህርት ክፍል እስከ የተቋሙ የበላይ አመራሮች ያለውን የግንኙነት ስርዓትን በማጠናከር የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱ ፈጣንና ችግሮች ሲፈጠሩም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋሉ፤

ተ. ተማሪዎች/ሰልጣኞች መማር ማስተማሩን አስመልክቶ ለሚኖራቸው ቅሬታ በአስቸኳይ መፍትሄ ሊሰጥ የሚችል ግብረ-ኃይል ያደራጃሉ፤

ቸ. የተማሪዎች/ሰልጣኞች ወደ ተቋማት ሲመለሱ በተሻለ ፍጥነት ጥሪ ያደርጋሉ እንድሁም የምረቃ፣ ሠርቲፊኬት እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን የማስፈጸሚያ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

ኀ. የተግባር ትምህርትና ስልጠና እና ምዘና ያላቸዉ ተመራቂ ተማሪዎች/ሰልጣኞች ባሉበት ተቋማት ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር በከራሽ ፕሮግራሙ ወቅት እንዴት መምራት እንደሚገባቸዉ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ዝርዝር የአፈጻጸም ዕቅድ በማዘጋጀት ይተገብራሉ፤

ነ. የአስተዳደር ስራዎችን የሚከታተል ግብረ-ሃይል በማደራጀት ካለዉ መዋቅር ጋር በማቀናጀት ወደ ስራ በማስገባት ከኮሮና እና ሰላማዊ መማር ማስተማር ጋር የተያዙ ጉዳዮችን ለመከታተል ዝርዝር ዕቅድ ያዘጋጃሉ፤

ኘ. ቫይረሱን ለመከላከል የተቀመጡ የጥንቃቄ መንገዶችን በባነር፣ በፖስተር፣ በስክሪን ወዘተ በማዘጋጀት በሚታዩ ቦታዎች ላይ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፣

አ. ቫይረሱን ለመከላከል የተቀመጡ የጥንቃቄ መንገዶችን አለመከተል ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑን በግልጽ በማሳወቅ ከቅበላ በፊት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል በህዝብ መገናኛ ብዙሃን እና በተቋማት ለተማሪዎችና ለተቋሙ ማህበረሰብ ግልጽ መደረጉን ያረጋግጣሉ፣

h. Heads of Institutions shall ensure that teachers and trainers compile coursework, tutorials, exercises, references and textbooks in soft and hard copies (audio and video) and organize and make these accessible to students.

i. Students, trainees will complete their education and training in a special program that will be implemented in a shorter period of time relative to the regular program. Institutions shall implement a special system of counseling and counseling services as well as stronger academic counseling services to students and trainees;

j. By strengthening the communication system from the education unit to top management of the institution, a strong monitoring and support system shall be set up as soon as possible.

k. A Taskforce should be established to follow-up on and resolve possible grievances students and trainees may have regarding the teaching and learning process.

l. Upon the return of students and trainees, top management shall execute the plan to expedite the preparation and implementation of programs that facilitate graduation, certification and other related activities;

m. For students, trainees whose programs require professional/practical evaluation, special arrangements shall be made for them during the crash program, that in consultation with relevant authorities, a special and detailed plan shall be prepared and implemented to assist them to meet graduation requirements.

n. A Taskforce shall be set up to coordinate with the administration and develop a detailed plan to address issues related to corona virus and peaceful teaching and learning.

o. Management shall display in appropriate locations on campus using banners, posters, screens, etc. information for the public regarding precautionary measures to be taken against the virus.

p. The management of each institution shall inform students and the Education and Training Institution community ahead of sending invitations, that failure to comply with the precautionary measures outlined in the Directive shall have serious consequences. Such information shall be made broadly avail through the Ministry of Science and Higher Education, the media and through institutional communication schemes



Scanned with CamScanner

ዐ. ተማሪዎች/ሰልጣኞች ግቢ ዉስጥ እስካሉና ወረርሽኙ እስካልጠፋ ድረስ ዉሃ፣ ሳንታይዘር፣ ማስክ እና ሳሙና ያለ እጅ ንክኪ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ፣

ከ. በ2012 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ዘመን በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የተቋረጠዉን ትምህርትና ስልጠና ለማጠናቀቅ የሚያስችል በጀት በልዩ ሁኔታ ማግኘት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳሉ፤

ኸ. የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ መገዛት የሚገባቸዉ ቁሶች (የተማሪዎች ምግብ፣ የላቦራቶሪ ኬምካሎች፣ የላቦራቶሪ ዕቃዎች፣ የዎርክሾፐ ማቴሪያሎች፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች፣ ሳንታይዘሮች፣ የፊት መሸፈኛ ጭምብሎች፣ የእጅ ጓንቶች፣ ከንክኪ ነጻ የእጅ መታጠቢያ ማሽኖች ወዘተ) በአግባቡ በመለየት ፈጣን ግዥዎችን ማከናወን የሚያስችል አሰራር ይዘረጋሉ፤

ወ. ስራዎችን ለማሳለጥ የሚያስችሉ አሠራር ስርዓቶች፣ የተክኖሎጂ እና ሌሎች መሠረተ ልማት ምቹ ሁኔታ ተቋማዊ በሆነ መልኩ መፈጠሩን ያረጋግጣሉ፤

የ. ዝርዝር ስራዎችን በየጊዜዉ ይገመግማሉ ፈጣን የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፤

ደ. ለማቆያነት ሲያገለግሉ የነበሩ ተቋማት በኬሚካል ማጽዳትና ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፤

ጀ. ተማሪዎች/ሰልጣኞች ወደ የተቋማቱ ሲጠሩ በጉዞ ሂደት ለወረርሽኙ ያላቸውን ተጋላጭነት ለመቀነስ የሚያስችል የትራንስፖርት አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ከትራንስፖርት ሚኒስቴርና ሌሎች ከሚመለከታው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፤

ገ. የቫይረሱ ምልክት በተቋም ደረጃ ቢታይ (ተጠርጣሪ ቢገኝ) በግቢ ዉስጥ የለይቶ ማቆያና ልዩ ህክምና መስጫ ማዕከል መኖሩን ያረጋግጣሉ፣ እንድሁም በየተቋማቱ ከሚገኙ የተማሪዎች ክሊኒክ፣ ከዞን/ወረዳ ጤና ማዕከላት ጋር በቅርበት ይሰራሉ፣

ጠ. የመመገቢያ ሰዓትን በማራዘም፣ ተማሪዎች/ሰልጣኞች በመመገቢያ አዳራሽ ርቀታቸዉን ጠብቀዉ የሚመገቡበት ሁኔታ ያመቻቻሉ፣

ጩ. ቫይረሱ በተቋም/በካምፓስ ደረጃ በወረርሽኝ መልክ ቢሰፋፋ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር አስፈላጊዉ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፣

ጰ. የመማር ማስተማር ሂደቱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስከሄድ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ ግምገማና ክትትል ያደርጋሉ፣

q. While the epidemic is ongoing, students/trainees are mandated to taking precautionary measures by continuing to clean their hands with water and soap, sanitizer, wear masks, and avoid physical contact while on campus.

r. Management will devise a strategy to find a special way to complete the education and training activities that were suspended in spring 2020 due to the COVID-19 epidemic.

s. Proper procurement procedures shall be put in place to conduct a proper and fair bidding and selection process and sign required agreements to allow timely purchase of all the necessary materials including food stuff, laboratory chemicals, laboratory equipment, workshop materials, teaching materials, sanitizers, masks, hand gloves, hand-free washing facilities, etc.

t. Management shall ensure that systems, technology and other infrastructure are facilitated in an institutional manner.

u. Management shall regularly review implementation activities and take immediate and corrective actions, as necessary.

v. Isolation facilities used for quarantine purposes should be thoroughly cleaned with chemicals in preparation for other uses.

w. As students/trainees are invited back to the institutions, management shall work in collaboration with the Ministry of Transport and branch offices at all levels to facilitate safe transportation services to protect students from being exposed to the epidemic during their journey.

x. If symptoms of the virus are detected at the institutional level, or there is suspicion of it, management shall ensure that there is an on-site isolation and specialized treatment center, and that they will work closely with student clinics, and zonal/woreda health centers.

y. Management will reduce risk of contamination, among other things, by extending dining hours such that students/trainees can sit at sufficient distances in dining halls.

z. If the virus dangerously spreads at the institutional/campus level, the management shall consult relevant authorities and stakeholders, and take appropriate actions.

aa. The management shall assess and monitor the learning and teaching process and shall create the conditions for peaceful execution;



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

ጸ. ተማሪዎች በየጊዜዉ አስፈላጊዉን የጤና ምርመራና ክትትል እንዲያደርጉ ይመከራል፣

ፀ. ለተማሪዎች የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ መምህራንና ሰራተኞች አስፈላጊዉ የጤና ምርመራና ክትትል እንዲያደርጉ ይመከራል፣

ፈ. ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ የበታች አመራሮች፣ መምህራን/አሰልጣኞች፣ ተማሪዎች/ሰልጣኞችና አስተዳደር ሰራተኞች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳሉ

#### 4) የመምህራን/አሰልጣኞች ሚና

ሀ. በዚህ መመሪያ መምህራንን/አሠልጠኞችን በሚመለከት ለተደነገጉ ግዴታዎች ኃላፊነት ይወስዳሉ፤ መመሪያውን የማስተዋወቅ፣ የማክበርና የማስከበር ሥራ አሪአያት ባለው መልኩ ይተገብራሉ፤

ለ. የተቋረጠውን ትምህርትና ስልጠና ለማስቀጠልና በአጠረ ጊዜ በልዩ ፐሮግራም ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ የሞጁል ዝግጅት፣ ዎርክሾፖችንና ቤተ ሙከራዎችን የማደራጀት፤ በቴከኖሎጂ የታገዘ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅቶችን ያደርጋሉ፤

ሐ. ሰላማዊ መማር ማስተማር እንዲሰፍን ተማሪዎችን በመምከር፣ የግጭት መንስኤና አባባሽ ከሚሆኑ አስተሳሰቦችና ተግባራት የመቆጠብና ሌሎችም እንዲቆጠቡ የማድረግ ሥራ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን በቅንጅት ይሰራሉ፤

መ. ብሔርንና ኃይማኖትን መሠረት ያደረጉ በተቋሙ ማህረሰብ ዘንድ አለመግባባን፣ ጥርጣሬንና ግጭትን በመቀስቀስ በትምህርና ስልጠና ሂደትና ስርዓቱ ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ተግባራትና አስተሳሰቦች መቆጠብና ሌሎችም እዲቆጠቡ የማድረግ ከፍተኛ ሚና ይበቅባቸዋል፡፡

ሠ. ተቋሙን፣ የተቋሙን ማህረሰብ አባል ወይም ቡድን ከኮቪድ -19 ጋር በተያያዘ ባልተገባ መንገድ በፍርሃት ወይም በስጋት ውስጥ በመከተት አሉታዊ የስነልቦና ጫና ወይም ማህበራዊ ጉዳት የሚያደርሱ ጽሑፎችን መጻፍ የለባቸውም፤ የሚጽፉ ካሉም እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡፡

ረ. በሚደረግላቸው ጥሪ መሰረት በስራ ቦታቸው በመገኘት ኮቪድ-19ን ለመከላከል የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን እና የተቀመጡትን ክልከላዎች በመተግበር ትምህርትና ስልጠናውን ያከናውናሉ

ሰ. በጤና ሚኒስተርና በሳ.ከ.ት.ሚ. የሚወጡ ኮቪድ-19 ስርጭትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የተዘጋጁ መመሪያዎችን ተማሪዎች/ሰልጣኞች እንዲተገብሩ ያደርጋሉ

bb. Management shall encourage that students and trainees receive regular health check-ups and necessary follow-ups.

cc. Management shall ensure that teachers and campus staff who provide educational services to students to have the necessary health check-ups and follow-ups.

dd. The top management of all institutions shall take appropriate action against underperforming leaders, teachers, trainers, students, trainees and/or administrative staff.

#### 4) The role of teachers/trainers

a. In this Directive, teachers/trainers are responsible for the duties assigned to them. They are expected to serve as models by supporting, promoting, enforcing, and showing respect to the guidelines.

b. Teachers/trainers shall organize modules, workshops and laboratories needed to continue the discontinued education and training and to complete the special programs in a shorter period of time. They shall also arrange for and conduct technology-based learning.

c. Teachers/trainers shall work in partnership with stakeholders to advise students, promote peaceful learning, avoid conflict-ridden attitudes and practices, refrain from participating in, and prevent others from engaging in conflicts.

d. Teachers/trainers play significant toles in dissuading students from engaging in ethnic and religious-based conflicts arising from misunderstandings, suspicions. They must refrain from personally engaging and/or fostering community sentiments that promote discord, suspicion and/or conflict. They are expected to personally refrain from such activities and prevent students/trainees from engaging in activities and attitudes that are detrimental to the education and training processes and the system.

e. Teachers/trainers should not engage in writings that may cause negative psychological stress or social harm by instigating or inciting commotion in the institution, in the community or in campus groups in ways that are inappropriate or intimidating. Teachers/trainers who promote false sentiments in relation to Covid-19 will be counseled.

f. F. When summoned for collaboration in campaigns against Covid-19 or in implementing the Directive, teachers/trainers are expected to play their part by appearing on campus in person as well as by conducting the education and training activities in accordance with the guidelines.

g. Teachers/trainers shall ensure that students/trainees comply with directives issued by the Ministry of Health and MoSHE to control the spread of Covid-19 epidemic.



Scanned with CamScanner

ሸ. በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ተማሪዎች/ሰልጣኞች ትምህርታቸውን/ስልጠናውን እንዲያጠናቅቁ ከተለመደው ተጨማሪ ጊዜን ስራ ላይ በማዋል የአዲሱን ኖርማል አሰራር ተግባራዊ ያደርጋሉ

ቀ. የተማሪዎችን/ሰልጣኞችን ውጤት በጊዜ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ሪፖርት ያደርጋሉ፤ በውጪ አካል የሚመዘኑ ሰልጣኞችንም በመለየት ዝርዝራቸውን ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ፤

በ. በትምህርትና ስልጠና አቀባበላቸውም ይሁን በሌሎች ጉዳዮች ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎችን/ሰልጣኞችን ለይተው ከሚመለከታው ጋር በመሆን ድጋፍ በማድረግ እንዲበቁ ያደርጋሉ፤

## ክፍል ሰባት

## የጥፋት ምድብ፣ የሚያስከትለው የቅጣት ዓይነት እና የዚህን መመሪያ ደንጋጌ በሚተላለፉ ተቋማትና የተቋማቱ ማህረሰብ ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች፤

**13. የዚህን መመሪያ ድንጋጌ በመተላለፋቸው ተጠያቂ የሚሆኑት የሚከተሉ ናቸው፡፡**

1) ተቋም
2) የተቋም አመራር
3) መምህራን
4) አስተዳደር ሠራተኞች
5) ተማሪዎች
6) ሌሎች በግቢ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ግለሰቦች፣ ተቋማት ወይም ማህበራት ይሆናሉ፡፡

**14. አነስተኛ ጥፋቶች**

አነስተኛ ጥፋቶች ተብለው የሚመደቡ የዚህ መመሪያ ድንጋጌ መተላለፎች በዚህ ክፍል ይካተታሉ፡፡

1) በምክር የሚታለፉ ጥፋቶች፣
   ሀ. የመመገቢያ እቃዎችን በተገቢው ቦታ ያለማስቀመጥ /ያለመመለስ/
   ለ. በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድላቸው ካልሆኑ በስተቀር አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ላይ ተራን አለመጠበቅ፤
   ሐ. ለመጀመሪያ ጊዜ አልኮል ጠጥቶ ሰክሮ ወደ ግቢ መግባት፣
   መ. የመማሪያ ክፍሎች፣ የአዳራሾችና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ወንበሮችና ጠረንጴዛዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ከቦታ ቦታ ማዛወር፣ አውጥቶ ደጅ ጥሎ መሄድ፣
   ሠ. ሌሎች መሰል የሥነ-ምግባር ጥፋቶችን መፈጸም፣

2) የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች

የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች ሆነው በማስታወሻ መዝገብ የሚያዙ እና ግለሰቡም ለጥፋቱ የሚፈርምበት ሆኖ በጽሁፍ የሚሰጡ ናቸው፡፡

h. By adjusting to the "New Normal", teachers and trainers will commit the necessary time for students/trainees to complete their academic requirements within the allotted time.

i. Teachers/trainers will finalize student/trainee results/grades within the required time, and for those who need external evaluation done, teachers/trainers will prepare the student list and share with the appropriate external body in a timely manner.

j. Teachers/trainers shall identify students/trainees who need special support in their education and training and collaborate with relevant bodies to provide them with the necessary support and ensure that the students/trainees meet their educational requirements.

## Part Seven

## Category of Misconducts, Types of Measures to be Taken against Higher Education Institutions' Community

**13. The following are responsible for violating the provisions of this Directive.**

a. Institution
b. Institutional leader
c. Academic Staff and Technical Assistants
d. Administrative staff
e. Students
f. Other individuals, institutions or associations that provide services on the campuses.

**14. Minor faults**

The following actions are considered as minor offenses or violations of this directive:

1) Offenses that call for reprimand,
   a. failure to return dining utensils to their proper place
   b. failure to wait in line at service facilities unless otherwise permitted;
   c. getting drank and entered the compound for first time,
   d. moving out and failing to return back chairs and desks and other materials from classrooms, halls and other service rooms for first time,
   e. Committing other similar misconducts;

2) Offenses that call for verbal warning

The University may take anyone of the following verbal warning against any individual in the campus who is found to be responsible for violations of disciplinary regulation of this directive. The Verbal warnings shall be recorded and signed by the individual for his misconduct.



Scanned with CamScanner

ሀ. ከላይ የተዘረዘሩትን በምክር የሚታለፉና መሰል ጥፋቶችን በድጋሚ ፈጽሞ መገኘት
ለ. እጅን ባልተፈቀደ ቦታ መታጠብ፣
ሐ. ወደ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ሲገቡ በተዘጋጀው የእጅ መታጠቢያ ላይ በአግባቡ እጅን አለመታጠብ
መ. በመኝታ ክፍል ውስጥና በኮሪደር፣ በእጅና ፊት መታጠቢያ ቦታዎች በመተላለፊያ መንገድ ላይ ልብስ ማጠብ፣

i. የትምህርትና ስልጠና ተቋም ግቢ ሲገባ በተዘጋጀው ቦታ የሰውነት ሙቀት ሳይለካ መግባት
ii. በመማሪያ ክፍሎች፣ በአብያተ መጽሀፍት፣ በመኝታ ህንፃዎችና በሌሎች የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ግድግዳዎች እንዲሁም በወንበሮችና ጠረጴዛዎች ላይ ማንኛውንም ጽሑፍ መፃፍ/ስዕል መሣል፣
iii. ውሃና የኤሌክትሪክ ሃይል ያለአግባብ መጠቀም (ማባከን)፣ ውሃ ከፍቶና መብራት አብርቶ መሄድ፣
iv. አብረው ከሚኖሩ የመኝታ ቤት ተጋሪዎችና አብረው ከሚማሩ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች ጋር ተግባብቶና ተስማምቶ አለመኖር፣
v. በመኝታ ክፍል ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ጽሑፍ እና/ወይም ስዕል መለጠፍ፣ተቋሙ ባወጣው አሰራር መሰረት መታወቂያ ወይም የምግብ ካርድ እንዲያሳይ ተጠይቆ ፈቃደኛ አለመሆን፤
vi. አትክልቶችንና አበባዎችን መርገጥ ወይም መቁረጥ፤
vii. ፍራሽ ከአልጋ አውርዶ መገኘት፣
viii. የታጠበ ልብስን ከልብስ ማስጫ ቦታ ውጭ ማስጣት፤
ix. በግቢ ውስጥ ከፍተኛ ድምጽ ወይም ጩኸት በራስ ድምጽ ወይም በማንኛቸውም የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች በማሰጮህ የአካባቢን ፀጥታን ማደፍረስ፤ (በጫማም ይሁን በሌላ መንገድ)
x. ሌሎች መሰል የስነ ምግባር ጥሰቶችን መፈጸም፤

**15. ቀላል ጥፋቶች**

ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና እንደአስፈላጊነቱ ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያስቀጡ ጥፋቶችን ያካትታል::

1) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም ከ30 ያላነሰ ከ50 ሰዓታት ያልበለጠ ማህበራዊ አገልግሎት (የጉልበት ሥራ) ወይም በሁለቱም ሊያስቀጡ የሚችሉ ጥፋቶችን
   ሀ. ከላይ በአነስተኛ ጥፋቶች የተዘረዘሩትን የቃል ማስጠንቀቂያ ወይም ነጻ ማህበራዊ አገልግሎት የሚያሰጡ ጥፋቶች መካከል አንዱን ጥፋት ተፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳይታይና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ ጥፋት ደግሞ መፈጸም፤

a. repetition of the above-mentioned offenses and similar offenses
b. Hand washing in an unauthorized place,
c. Failure to wash hands properly in the designated hand wash areas when entering service areas,
d. Washing clothes in dormitories, in the corridors, hallway, shower rooms, and other unauthorized places,
e. Entering the premises of higher learning institute without getting body temperature measured,
f. Drawing any text, picture or sign on the walls of classrooms, libraries, dormitories and other service rooms, as well as on chairs and tables.
g. Misuse of water and electricity; leaving water tap and electric lights on;
h. Conflicting with roommates and classmates;
i. Posting inappropriate text and/or pictures in the dormitories, refusing to show ID and/or Meal card in accordance with procedures established by the institution;
j. Treading or cutting trees and flowers;
k. Getting a mattress out of bed,
l. Dispose of washed clothes outside the designated place;
m. Creating noise pollutions or making screams in the living yard and/or around classrooms, libraries, and laboratories by any electronic devices, talking, walking or otherwise,
n. Committing other similar violations;

**15. Simple offenses**

The following acts or violations of the regulations shall constitute minor offenses or misconducts by individuals in campuses. These actions call for measures that range from a simple written warning to a severe written warning and, as needed, social services.

1) Simple offenses that call for written warning or penalties for not less than 30 and not more than 50 hours of social service (mainly labor work) or both.
   a. If no improvement is recorded after one is reprimanded or advised for committing the same or similar offenses listed above in the minor offenses or those that justify provision of free social services;



Scanned with CamScanner

ለ. ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል አላስፈላጊና በሳይንስ ያልተረጋገጡ የኮቪድ-19 መረጃዎችና አስታየየቶችን በመረጃ መረብም ሆነ በማንኛዉም መልኩ ማሰራጨት የተከለከለ ነዉ፡

ሐ. ወደ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ቅጥር ግቢ የመግቢያና መውጫ የሰዓት ገደብ አለማክበር፤

መ. ለተማሪዎች በቂ የልብስ ማጠቢያ ቦታዎችን አለማዘጋጀት

ሠ. እንደየተቋሙ ሁኔታ ፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ መሠረተ ልማት፣ ፋሲሊቲና የአሠራር ስርዓት አለማኖር

ረ. በተራ ምድብ ወቅት የመኝታ ክፍልን፣ መጸዳጃ ቤትን፣ የመኖሪያ ሕንፃ ኮሪዶርን፣ የመኖሪያ ሕንጻ አካባቢን አለማጽዳት፣ የራስን አልጋ አለማንጠፍና የግል ንጽህናን አለመጠበቅ፣

ሰ. የትምህርትና ስልጠና ተቋማትና የተቋማቱ ማህበረሰብ አባላት የተማሪዎች ቅበላ ጥሪን፣ የተሟላ መረጃን ተደራሽ ማድረግን፣ የግቢ መግቢያ በር ፍተሻን፣ የምዝገባ ዝግጅትን፣ ምዝገባን እና መታወቂያን በሚመለከት በዚህ መመሪያ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መጣስ ወይም ኃላፊነትን አለመወጣት

ሸ. ግለሰቦችን ለተራ ጥል መጋበዝ፣ ማጣላት፣ ነገር መቆስቆስ፣ ማጋጋል፣ ጥል ሲነሳ አለመገላገል፣ ወገን ለይቶ ማበር፣ በነገር ማቆራቆስ፣

ቀ. ከተፈቀደ ቦታ ውጭ በትምህርትና ስልጠና ግቢ ውስጥ ቆሻሻ መጣል፤

በ. በትምህርትና ስልጠና ተቋም ተገቢ አካል የተሰጠን ሕጋዊ ትእዛዝ አለማክበር፤

ተ. ለጋራ ጤንነት አደገኛ የሆኑ ድርጊቶችን መፈጸም፤

ቸ. ያለ ግለሰቡ ወይም በትምህርትና ስልጠና ተቋሙ ፈቃድ የግለሰብ ወይም የዩኒቨርሲቲ ንብረት መጠቀም፣

ኀ. የሌላ ሰው መታወቂያ ወይም የምግብ ካርድ መጠቀም፣

ነ. የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት ሳያውቁ በየትኛውም መንገድ ከተማሪዎች ገንዘብ መሰብሰብ፣

ኘ. የተማሪዎችን ትራንስፖርትና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን በማመቻቸት ሽፋን ለግል ጥቅም ሲባል ተማሪዎችን ከፍተኛ ክፊያ መጠየቅ ወይም እንዲጠየቁ መተባበር፣

አ. በተቋሙ ግቢ ውስጥ ሲጋራ ማጨስ፤ ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት፤ ሌሎችም አጭሰው ወይም ይዘው እያዩ ዝም ማለት

ዐ. የጋራ መገልገያዎችን አለአግባብ ለግል ጥቅም ማዋል፣

ከ. አጭበርብሮ የገንዘብ ድጋፍ ከትምህርትና ስልጠና ተቋም ለማግኘት መሞከር፣

ኸ. ምንም ውክልና ሳይኖር የተማሪዎች ህብረት አባል፣ የክበብ ተጠሪ ነኝ ወዘተ በማለት ሰዎች መረጃ እንዲሰጡት መጠየቅ ወይም መስራት፣

b. It is prohibited for any member of the Institution to disseminate unnecessary and scientifically unsubstantiated Covid-19 information and comments on the Internet or in any form.

c. Failure to comply with entry and exit hours on the premises of the Institution;

d. Lack of adequate laundry space for students

e. Lack of sewerage and solid waste disposal infrastructure, facilities and systems according to the need of the Institution.

f. Not cleaning dormitory, toilet, living room corridor, living room area when assigned, and not preparing own bed and not keeping personal hygiene,

g. Violation or non-compliance with the provisions of this Directive regarding admission of students, provision of complete information, doing inspection at entrance gates, preparation for registration, processing of registration and ID cards by members of the Institution,

h. Inviting individuals to conflict, provoking others to quarrel, causing others to fight, not interceding between quarreling individuals, threatening others, fighting in groups,

i. Dispose of rubbish outside the permitted area of the institution;

j. Failure to comply with legal orders issued by the appropriate body of the Institution;

k. Engaging in activities that are dangerous to public health;

l. Use of private or Institution's property without the consent of the individual or the permission of the institution;

m. Using someone else's ID or food card,

n. Collecting money from students in any way without the knowledge of student services and student unions;

o. Facilitate student transportation and other services by requesting students or cooperating with others for personal gain to pay higher fees,

p. Smoking in the premises; use or possession of illicit drugs; not informing the instituting while others smoke or possess cigarette or illicit drugs,

q. Misuse/and or abuse of common resources for personal use;

r. Fraudulent attempt to obtain financial assistance from the institution;

s. Ask or work for information from students and others in the Institution acting as a student union member, club representative, etc. without any representation.



Scanned with CamScanner

2) ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና እንደአስፈላጊነቱ ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያስቀጡ ጥፋቶች

ሀ. ከላይ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም ከ30 ያላነሰ ከ50 ሰዓታት የሚያስቀጡ ጥፋቶች መካከል አንዱን ወይም ተመሳሳይ ጥፋት ፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳያሳዩ ያንኑ ወይም ተመሳሳይ ጥፋት ደግሞ መፈጸም፤

ለ. ከተማሪዎች ምግብ ቤት እና ከሌሎች ግቢ ውስጥ ካሉ ምግብ ቤቶች የሚወጡ ትርፍራፊ ምግቦችን ለሌላ ለማንኛውም አካል አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

ሐ. በግቢው ውስጥ በተለይም በጋራ መገልገያ አካባቢዎች ማለትም በመኝታ፣ በመመገቢያና በመማሪያ ክፍሎች፣ በቤተ መፃህፍት፣ በወርክሾፖች፣ በቤተሙከራ በክሊኒክና በዲ.ኤስ.ቲቪ ወዘተ አካባቢ ያልተገባ ጩኸት ማሰማት፣ ሁከትና ግርግር ማንሳት፣

መ. ያልተፈቀደ ማንኛውንም ዓይነት ማስታወቂያ ግቢ ውስጥ በማንኛቸውም ቦታዎች መለጠፍ

ሠ. አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ላይ ርቀትን ጠብቆ አለመሰለፍ

ረ. ተማሪዎች በግል ካልሆነ በስተቀር የቡድን ስፖርት መስራት አይፈቀድም፡፡

ሰ. በኮቪድ-19 ተጠርጥሮ ወይም ምልክቶች እየታዩበት ለምርመራ ፈቃደኛ አለመሆን፣ ወይም ወደ ለይቶ ማቆያ ለመግባት ፈቃደኛ ያለመሆን ወይም የተጭበረበረ መረጃ ማቅረብ ወይም ተደብቆ መኖር

ሸ. ብመጠጥ ሀይል ሰክሮ በግቢው ውስጥ ሁከት መፍጠር (የአካባቢ ፀጥታን ማደፍረስ) ፣

ቀ. በፍራሽ ወይም ትራስ ወይም የፍራሽ ልብስ ቀዶ መገኘት፣

በ. ባልተፈቀደለት መኝታ ቤት ማደር ወይም የመኝታ ቦታን ያለፈቃድ መቀየር

ተ. ያልተፈቀደለት ሰው በመኖሪያ ቦታ እንዲኖር፣ እንዲዳበል ወይም እንዲያድር ማድረግ፤

ቸ. ያለፈቃድ የበሰለ ምግብ ከዳቦ ውጭ ከማንኛውም ቦታ ወደ ዶርም ይዞ ገብቶ ሲጠቀሙ መገኘት፣

ኀ. ማንኛውንም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ንብረት በአግባቡ አለመጠቀም፣ ማበላሸት፣

ነ. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በአጥር ዘሎ ወይም ሾልኮ መግባትና መውጣት፣

ኘ. በመኝታ ክፍል ውስጥ ያልተፈቀዱ የኤሌክትሪክ እቃዎችን መጠቀም፣

አ. ለትምህርትና ስልጠና ተቋም መምህራን፣ ሰራተኞችና ሀላፊዎች ሥራው የሚጠይቀውን አስፈላጊውን ትብብር አለማድረግ፣

ዐ. ህጋዊ ያልሆነ ስብሰባ ወይም በተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር ወይም በትምህርትና ስልጠና ተቋም ከፍተኛ አመራር ፈቃድ ያላገኘ ትእይንት ማሳየት ወይም ለማሳየት መሞከር፣

2) Misconducts that call for severe written warnings and penalties for providing social services as needed

a. Performing the same or similar offenses without showing any improvement of actions after written warnings were given for any of the above or any other offenses punishable by free social services not less than 30 hours and not more than 50 hours;
b. It is forbidden to transfer leftover food from a student cafeteria or other campus to anyone else.
c. Making loud noises, screaming, and shouting in and around common facility areas such as dormitories, dining rooms, classrooms, libraries, workshops, laboratories, clinics, DSTV, etc.
d. Post any unauthorized advertisement anywhere in the campus,
e. Failure to line up at service points keeping appropriate distances
f. Students are not allowed to play group sports except in private.
g. Failure to be tested፣ or admition to isolation center, or self hiding or providing fraudulent information or bearing facke certificate when showing symptoms of COVID-19,
h. Involved in fight and violent actions being under the influence of alcohol and other substances,
i. Putting mattresses and/or pillows on the ground, or destroying mattress and/or pillows,
j. Staying in an unauthorized dormitory or changing dormitory without permission,
k. Allowing an unauthorized person to live, cohabit or let stay at the dormitory;
l. Bringing unauthorized food into the dorm from anywhere except bread,
m. Misuse, abuse, or vandalism of any properties of the institution,
n. Illegally jumping over the fence;
o. Using unauthorized electrical appliances in dormitories;
p. Failure to provide the necessary cooperation to the teachers, staff and officials in the Institution;
q. Conducting illegal meetings or showing drama, theatre or performing other activities without prior permission from the Director of Student Affairs or the top management of the Institution;



Scanned with CamScanner

ከ. የራስን ሃይማኖት፣ እምነትና የፖለቲካ አመለካከት ሌሎች እንዲቀበሉ ጫና መፍጠር፣ መረበሽ

ኸ. በመግቢያ በርና በአገልግሎት መስጫዎች የመታወቂያ (የመገልገያ) ካርድ ሲጠየቅ ለማሣየት ፈቃደኛ አለመሆን፣

ወ. ሃይማኖታዊ በአሎችንና ትዕይንቶችን በግቢው ውስጥ ማካሄድ፣ እንዲካሄዱ መቀስቀስ፣ ማነሳሳት፣ መምራት፣

የ. ሌሎች መሰል የስነ-ምግባር ጥፋቶችን መፈፀም፣

**16. መካከለኛ ጥፋቶች**

1) ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም የተጣለበትን ተቋማዊ ግዴታ አለመወጣት
2) በየደረጃው ያለ ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም አመራር ከተሰጠው የሥራ ተግባርና ኃላፊነት ጋር የተያያዙ በዚህ መመሪያ የተደነገጉ የተቋምና በአመረር ደረጃ ሊፈጸሙና ሊተገበሩ የሚገባቸውን ግዴታዎች አለመወጣት
3) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ኮቪድ-19 ለመከላከል ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚችልበትን አጠቃላይ ሁኔታ የሚደነግግና ከዚህ መመሪያ ጋር የተጣጣመ ማንዋል አለማዘጋጀት፣ አለማስተዋወቅና አለማስፈጸም
4) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ኮቪድ-19 ወረርሽኝን በመከላከል ትምህርትና ስልጠናን ለማስቀጠል በየደረጃው የሚያስተባብር ግብረ-ኃይል አለማደራጀት፣ ተቋማዊ የግንኙነት መሥመር አለማዘጋጀትና ለተጠቃሚዎች ምቹ በሆነ መንገድ አለማስተዋወቅ
5) ማንኛውም ሰው በትምህርትና ስልጠና ተቋም ውስጥ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ ቀሪ መሆኑ እስከሚወሰንበት እና ስልጣን ባለው አካል በይፋ እስከሚገለጽበት ጊዜ ድረስ ከመኝታ እና ከመመገቢያ ሰዓት ውጪ በማንኛውም ቦታ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርግ መንቀሳቀስ
6) የትምህርትና ስልጠና ተቋም ውስጥ ተገልጋዮች በሚቀመጡበት ጊዜም ይሁን በማንኛዉም አኳኋን አገልግሎቱን ሲያገኙ ከሁለት ሜትር በታች ተጠጋግተው እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርጉ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ወይም ከተማሪዎች ምግብ ቤት ውጪ ባሉ ምግብ ቤቶች ጠረጴዛቸው በአንድ ጠረጴዛ ከሶስት ተገልጋዮች በላይ እንዲቀመጡ ማድረግ
7) የተቀደደ፣ በአግባቡ ያልጸዳ ወይም በአግባቡ ያልጸዳ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግ
8) በተቋም ግቢ ውስጥ በሚደረግ እንቅስቃሴና የጋራ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ቦታዎች ከሁለት ሜትር በታች ርቀት መቆምም ሆነ መቀመጥ

r. Pressuring others to accept their own religion, beliefs and political views, disturbing others otherwise,

s. Refusal to show ID card when asked for at the entrance gate and/or at service provision points,

t. Carrying out religious ceremonies and demonstrations in the compound, inciting and directing others to do the same,

u. Committing other similar misconducts;

16. Medium **offenses**

1) Failure to fulfill institutional obligations of any educational and training institution
2) Failure to fulfill leadership duties and responsibilities of the institution at any level of the management hierarchy related this Directive and other regulations assigned to the management of any educational and training institution,
3) Failure to prepare, promote and implement a manual in accordance with this guideline, which stipulates the general conditions under which any educational and training institution may provide education and training to prevent COV-19.
4) Failure of any education and training institution to organize a task force to coordinate the resumption of education and training at all levels designing mechanisms to prevent the outbreak of CVD-19 epidemic, and failure to establish an institutional communication line and to promote it in a user-friendly manner.
5) Failure to wear a face mask up until public body notifies a decision to quit the use of mask in educational and training institution.
6) failure to ensure that customers in an educational and training facility sit or stand close to each other in two meters gap without using face masks when receiving services, or that no more than three customers use one table other settings out of students' dining hall,
7) Wearing a torn, unwashed or improperly cleaned face mask
8) Standing or sitting at a distance of less than two meters in activities and common service areas of the institution premises,



Scanned with CamScanner

9) በሁሉ የተቋሙ ግቢዎች ውስጥ ባሉ ግቢ መግቢያ በር፣ በመማሪያ ክፍሎች፣ በተማሪዎች ማደሪያ ሕንጻ፣ ቤተ-መጽሐፍት መግቢያ፣ ክሊኒክ መግቢያ፣ ቤተ-ሙከራና ወርክሾፕ መግቢያ፣ ግቢ ውስጥ ባሉ ምግብ ቤቶች መግቢያ፣ የተማሪዎች መዝናኛ ቦታዎች፣ በአስተዳደር፣ የኮሌጅ፣ ፋኩልቲ፣ ትምህርት ቤት፣ ኢንስቲትዩት እና የትምህርት ክፍሎች ህንጻ መግቢያ፣ የምርምር ማዕከላት መግቢያ እና ሌሎች የግቢ ማህበረሰብ እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው ቦታዎችና አካባቢዎች ላይ ከእጅ ንኪኪ ነጻ የሆኑ የእጅ መታጠቢያዎች አገልግሎት እና ውሃ አለማዘጋጀት እና የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋት

10) ከተማሪዎች ምግብ ቤት እና ከሌሎች ግቢ ውስጥ ካሉ ምግብ ቤቶች የሚወጡ ትራፊ ምግቦችን ለሌላ ለማንኛውም ግልሰብም ሆነ አካል አሳልፎ መስጠት ወይም መሸጥ

11) ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ማህበረሰብ አባል ተቋሙ ካለበት ከተማ ውጪ ከአቅም በላይና አሳማኝ በሆነ ምክንያት የተጓዘ እንደሆነ ቀድሞ የጉዞ ታሪኩን ተቋሙ ውስጥ ላለው ማዕከል ማስመዝገብ ያለበት ሲሆን ከጉዞ መልስ ራሱን በለይቶ ማቆያ ውስጥ ሳያቆይ በቀጥታ ከሌላው ማበህረሰብ ጋር መቀላቀል

12) ማንኛውም የአካል ቅርርብንና ንኪኪን የሚፈልጉ የተማሪዎች የቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ያሉ መዝናኛዎች፣ የመዝናኛ መሳሪያዎችና ጨዋታዎች እና በማንኛውም ደረጃ የሚደረግ የቡድን ስፖርት ውድድር ማድረግ

13) በግል ካልሆነ በስተቀር በቡድን ስፖርታዊ እቅስቃሴ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

14) ግቢ ውስጥ የስነ-ጽሑፍ ምሽቶችና የተለያዩ የመዝናኛ መሰባሰቦች ማካሄድ፣ ማስተባበር፣ መምራት

15) በግቢ ውስጥ ባሉ ማንኛውም የመዝናኛ ስፍራዎች በቡድን መጫዎት

16) በግቢ ውስጥ ባሉ ላዉንጆችና መዝናኛ ቦታዎች የሚገኙ የቤት ውስጥ መዝናኛ ጨዋታዎች ማድረግ

17) የተማሪዎች ዶርም ምደባ ህብረ-ብሔራዊ አድርጎ፣ አንድ ትምህርት ክፍል፣ አንድ መመሪያ ክፍል የሚገቡትን ተመሳሳይ የትምህር ዓመት ተማሪዎችን በተመሳሳይ ብሎክና ዶርሞች መድቦ አስቀድሞ ተማሪው ከመጠራቱ በፊት መድቦ ለተማሪዎቹም በበየነ መረብ አለማሳወቅ

18) በተማሪዎች ዶርም ውስጥ ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎችን አለማድረግ

19) የትምህርትና ስልጠና ተቋማትና የተቋማቱ ማህበረሰብ አባላት በተማሪዎች ምግብ ቤት እንዲተገበሩ በዚህ መመሪያ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መጣስ ወይም ኃላፊነትን አለመወጣት

20) በዚህ መመሪያ የተማሪዎች የዶርም ምደባና አኗኗርን በሚመለከት የተጣሉ ግዴታዎችን አለመወጣት ወይም የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መጣስ

21) በዚህ መመሪያ የተማሪዎች ክልኒክን በሚመለከት የተጣሉ ግዴታዎችን አለመወጣት ወይም የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መጣስ

9) Failure to set up automatic hand-washing facilities and availing water and other sanitation materials to the community of the Institution at the entrances of the premises of all busy areas of the institution, such as classrooms, dormitories, libraries, clinics, laboratories, workshops, student dining halls and cafeterias on campus, recreation areas, administration buildings, colleges, faculty, departments, Research Centers, and other areas of the campus; and failure to establish monitoring and controlling system to oversight proper functioning of sanitation services thereof,

10) Handing over or selling food leftovers (wastage) from student dining halls and other campus cafeterias to any individual or entity,

11) Any member of the Education and Training Institution community, who traveled outside the city in which the institution is located for justifiable reasons, and who joined the community directly without checking for Covid-19 and staying at a quarantine after his return trip, but who failed to report and get registered his travel history to the center within the facility,

12) Using recreational equipment and other facilities that cause hand touch and physical contact involving indoor and outdoor activities, recreation, and games by the Institution's community

13) Group sport activities is prohibited except in private.

14) Preparation of literary evenings and various leisure gatherings in the campus,

15) Playing in groups at any recreational area on campus

16) Playing indoor recreation games in lounges and recreation areas in campuses,

17) failure to prepare dormitory placements of students ensuring multiculturalism in every dorm as well as placing the same department and batch students to the same block and dormitories before students are called and not notifying the same to students online,

18) Failure to take necessary precautionary actions in student dormitories,

19) Violation of the provisions of this Directive and failing to execute responsibilities as stated in appropriate regulations of education and training institutions to be applied by institutions' community members to regulate student cafeteria,

20) Failure to fulfill the obligations or violation of provisions in this Directive of students' dormitory placement and living,

21) Failure to fulfill the obligations of students' clinic or violation of the provisions of this Directive in this regard,



Scanned with CamScanner

22) በዚህ መመሪያ መማር ማስተማርን፣ መማሪያ ክፍሎችንና ማስተማሪያ መሣሪያዎችን፣ የወንበር አቀማመጥን፣ አካላዊ ርቀትን፣ ቤተ-ሙከራና ቤተ-መጽሐፍተና ወርክሾፕ ውስጥ ሊተገበሩ የሚገቡ ድንጋጌዎችን፣ የምዘና ስርዓት፣ ግብረ-መልስና የውጤት አሰጣጥ በሚመለከት ያሉ ድንጋጌዎችን በሚመለከት ኃላፊነትን አለመወጣት ወይም መጣስ

23) የኮርስ ድልድል፣ የማስተማሪያ ግብዓቶች ዝግጅትና የትምህርትና ስልጠና አሰጣጥን በሚመለከት የተጣሉ ግዴታዎችን አለመወጣት ወይም የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መጣስ

24) ማንኛውም መምህር/አሠልጣኝ በመማሪያ ክፍል፣ በቤተ-ሙከራ ወይም በወርክ-ሾፕ በቂ የአየር ዝውውር ሳይኖር፣ ሁሉም ተማሪዎች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ በአግባቡ ሳያደርጉ እና አካላዊ ርቀትን ሳይጠብቁ ማስተማር

**25) ለአንድ ወሰነ ትምህርት ከትምህርትና ስልጠና ገቢታ የሚያሳግዱ ጥፋቶች**

ሀ. ከላይ የተጠቀሱት ወይም ተመሳሳይ ጥፋት በድጋሜ ፈጽሞ መገኘት፣

ለ. ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በህክምና ባለሙያ ተረጋገጠ ምንም ዓይነት የኮቪድ-19 ምልክቶችና ስሜቶች ሳይኖሩት ሆነ ብሎ በዉሸት የኮቪድ-19 ተማሚ ነኝ በሚል በተቋሙ ላይ ስጋት ወይም ፍርሀት እንዲነግስ ማድረግ

ሐ. ፈተና መስረቅ ወይም ፈተና መኮረጅ ወይም ማስኮረጅ፣ የሌላ ሰው ሥራን የራስ አስመስሎ ማቅረብ፣

መ. ሴትም ሆነ ወንድ ተማሪዎችን በንግግር፣ በጽሁፍ፣ በስልክ፣ ወዘተ ማስፈራራት፣ ማስቸገር፣ ማስጨነቅ፣ መሳደብ

ሠ. የተለጠፉ ህጋዊ ማስታወቂያዎችን መገንጠል፣ መቅደድ፣ መደለዝ ወይም ማበላሸት፣

ረ. በምንም ይሁን በምንም ሁኔታ ከተማሪ ጋር ጥል መፍጠር፣ ለድብደባ መጋበዝ

ሰ. የትምህርትና ስልጠና ተቋምን መምህር፣ ሰራተኛ ወይም ሌሎችን መዝለፍ፣ ማንጓጠጥ፣ መሳደብ፣ ለመምታት መጋበዝ

ሸ. ህጋዊ ፍቃድ የሌላቸው ስብሰባዎችንና ምክክሮችን በግቢው ውስጥ ማካሄድ፣ መሳተፍ፣

ቀ. የራስ መታወቂያ ወይም የመመገቢያ ካርድን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፣

በ. በሌላ ተማሪ መታወቂያ ወይም መመገቢያ ካርድ አገልግሎት ለማግኘት ማጭበርበር፣ ሲመገቡ መገኘት

ተ. ለተማሪዎች የትራንስፓርት አገልግሎት ለመስጠት በሚደረገው እንቅስቃሴ በማንኛውም ስም ከተመን በላይ ማስከፈል፣ ለማስከፈል መሞከር፣ ለማስከፈል ማስተባበር መተባበር

ቸ. የአንድን ተማሪ መታወቂያ ወይም የመመገቢያ ካርድ ወይም ሌሎች ንብረቶችን ገንዘብ ወይም ሌሎች ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት በቅድመ ሁኔታነት መያዣ ማድረግ፣

22) Failure to comply with or violate any provisions related to teaching, use of classroom and instructional materials, chair arrangement and placements, physical distancing, laboratory, library and workshops, evaluation system, feedback and grading.

23) Failure to comply with obligations regarding course allocation, preparation of teaching materials and provision of education and training, or violation of provisions stated in this Directive.

24) Teaching students without adequate ventilation in classroom, laboratories or workshops, without wearing face mask and keeping body distance.

25) Offenses that exclude a student from the education and training institution for one Semester

a. Performing the same or similar offenses without showing any improvement of actions after measures were taken for any of the above offenses,
b. Any member of the Education and Training Institute community who falsely claimed he has been certified by a medical professional for having Covid-19 to intentionally cause fear among the community of the Institution,
c. Stealing exam papers or cheating during examination, plagiarism and impersonation;
d. Threatening, harassing, terrorizing and insulting both students through speech, writing, telephone call, etc.
e. Obliterating, tearing down, deleting or damaging posted legal notices;
f. Conflict with a student in any form, inciting violence
g. Humiliating, harassing, insulting, or beating a teacher, an employee, or others,
h. Conducting and participating in unauthorized meetings and gatherings on campus;
i. Passing an ID or a meal card to someone else; or trying to use someone else's ID or meal card to dine or get other services,
j. Overcharging students for claiming to coordinate transportation services to them,
k. holding a student's ID or dining card or other personal belongings of a student for cash or other benefits;



Scanned with CamScanner

ኀ. በተቋሙ ውስጥ የሚካሄድ አካዳሚያዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ፣ ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን መረበሽ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት መፈጸም፤

ነ. ማንኛውም ተማሪ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የራሱ ወዳልሆነ ዶርም ገብቶ መገኘት

**26) ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት የሚያስቀጡ ጥፋቶች በዚህ ምድብ ይካተታሉ፡፡**

ሀ. ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በተቋሙ ላይ ወይም በሌላ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ አሉታዊ የስነ-ልቦና ይሁን የማህበራዊ ጫና ወይም ጉዳት የሚፈጥር ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ መረጃዎችና አስታያየቶችን በመረጃ መረብም ሆነ በማንኛዉም መልኩ ማሰራጨት

ለ. ሆን ብሎ የፈተና ወረቀት ሳያስረክብ ይዞ መውጣት፣ የሌላ ተማሪ የታረመም ሆነ ያልታረመ የፈተና ወረቀት ለማጥፋት መሞከር ወይም ማጥፋት ወይም መቅደድ፣

ሐ. በፈተና ወረቀቱ ላይ ስሙን ቀይሮ እንዲፈተንለት ሌላ ዲፓርትመንት ተማሪ ወይም ተማሪ ያልሆነ ሰው በራሱ ቦታ ማስፈተን፣

መ. አልኮልና ጫት ይዞ መግባት፣ ለመግባት መሞከር፣

ሠ. መታወቂያና መመገቢያ ካርድ ሳይጠፋበት ጠፋኝ በሚል አመልክቶ ሁለተኛ ለማግኘት መሞከር ወይም አግኝቶ በሁለት ካርድ ሲጠቀም መገኘት፣

ረ. በቤተ መጽሐፍት ወይም በሌሎች ከፍሎች ውስጥ ያሉ መጽሐፍትን፣ ጆርናሎችን ወዘተ ገጽ መቅደድና መገንጠል፣ ወይም መስረቅ

ሰ. መረጃ በሌለበት በአሉባልታ፣ በመሰለኝና ባልታረጋገጠ ወሬ በስብሰባዎች ላይም ይሁን በሌሎች ሁነቶች የትምህርትና ስልጠና ተቋምን ኃላፊዎች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ተማሪዎችን ማቃለል፣ የሃሰት ንግግሮችን በማድረግ ና በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች በመጻፍ ክብር መንካት፣ ስም ማጥፋትና የመሳሰሉ ድርጊቶችን መፈጸም፣

ሸ. በትምህርትና ስልጠና ተቋም ማህበረሰብ አባል ላይ የስነ-ልቦና ጉዳት ማድረስ፣ መሳደብ፣ ማስፈራራት፣ መዝለፍ፣ መረበሽ፣ ማስጨነቅ፣ እንዲሁም አእምሮውን፣ ማህበረሰባዊ ግንኙነቱን፣ ህይወቱን ወይም እንቅስቃሴውንና የስራ ሞራሉን ሊጐዱ የሚችሉ ሃይለ ቃሎችን መናገር፣ በሥራው ላይ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ማድረግ፣

ቀ. ሳይታመም የታመመ በማስመሰል ከክሊኒክ መድኃኒት አውጥቶ ሲሸጥ ወይም ለሌላ ሰው ሲሰጥ መገኘት፣

በ. መታወቂያ ካርዱን ወይም መመገቢያ ካርዱን፣ የቤተ-መጽሐፍት መዋሻ ካርድ ወይም ሌላ የግል መለያውን ለሌላ ተማሪ አሳልፎ በመስጠት ማስጠቀም ወይም ከሌላው ተቀብሎ መጠቀም፣

l. disrupting or improperly interfering with academic, administrative, social, or other activities in the institution;

m. entering to other students' dormitory that is not his at any time and in any situation,

26) Offenses punishable by one to two years are exclude the student from the institution

a. Disseminating information and comments related to Covid-19 on any network in any form, about the educational and training institution, member of the Institution's community or any individual or group, which causes negative psychological or social impact.

b. Deliberately taking a test paper without submitting it, attempting to destroy or tear up another student's corrected or uncorrected test paper;

c. allowing another student or non-student to take a test on his behalf,

d. Entering or attempting to enter to the institution with alcohol and khat,

e. Trying to get a second ID and/or meal card claiming the first is lost, or trying to use or being caught with two cards.

f. Tearing (a) page(s) from books, research journals, magazines, etc. in a library or other rooms, or stealing the same,

g. Abuse of officials, teachers, administrative staff or other students at meetings and other events in the absence of information or based on unconfirmed rumors, defamation, assumptions, hypotheses, etc.

h. causing psychological harm to a member of the Institution through insulting, threating, bullying, harassing, and disturbing; as well as abusing the individual that may harm his or her mind, social interactions, life or activities, moral and work ethics;

i. providing or selling medicines to others prescribed from a clinic by pretending sick;

j. Handing over ID or meal card, library book borrowing card or other personal ID card to another student or using the ID or meal card of another student



Scanned with CamScanner

ተ. የሌላ ተማሪ መመገቢያ ካርድ፣ መታወቂያ ወይም ሌላ ዕቃ ሰርቆ ከወሰደ በኋላ እንዲመልስ ሲጠየቅ በገንዘብ ወይም በዓይነት ጥቅም ለማግኘት መደራደር ወይም ይህን ድርጊት ከሚፈጽም ሰው ጋር መተባበር፣

ቸ. በሆቴሎች፣ በጭፈራ ቤቶች ወይም በሌሎች ቦታዎች በሴተኛ አዳሪነት ተሰማርቶ መገኘት ወይም እነዚህን የሚመስሉ ተግባራትን መፈጸም ወይም ይህን እንዲያደርጉ መገፋፋት፣ እንደአገናኝ ማገልገል፣

ኀ. ያለግለሰቡ ፈቃድ ምስሉን ወይም ድምጹን በካሜራ ወይም በሞባይል ቀርፆ ለህዝብ ማሳየት ወይም ማሰማት፣ ለማንኛውም ተግባር እንዲውል ማድረግ፣

ነ. ለተማሪዎች ህብረት ስራ ማስኬጃ የተበጀተውን ገንዘብ ወይም የተማሪዎች ክበብ በድጋፍ ያገኘውን ወይም ከአባላት የተሰበሰበውን ገንዘብ የፋይናንስ የገቢና ወጭ ስርዓት ባልተከተለ መልኩ ማስኬድ፣ መመዝበር፣

ኘ. በተማሪዎች ህብረት አባላት ላይ ሆን ብሎ ማመጽ፣ ችግር መፍጠር፣ ማዋከብ፣ ብሔራቸውን ወይም ሌሎች ማንነታቸውን መሠረት አድርጎ ማጣጣል፣ መስደብ፣ሌሎች እንዲነሱባቸው መቀስቀስ፣ (ችግር ያለባቸውን ለይቶ በህጋዊ መንገድ እንዲነሱ በመረጃ ላይ የተደገፈ ጥያቄ ማቅረብ እንደተጠበቀ ሆኖ።)

አ. በዩኒቨርሲቲ ሰራተኛ ወይም ተማሪ ላይ በማስፈራራት ወይም በመዛት የሆነ ነገር እንዲያደርግ ወይም እንዳያደርግ ማስገደድ፣

ዐ. በሌሎች ተማሪዎች ወይም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ማህበረሰብ አባላት ላይ የሞራል ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ትዕይንቶችን፣ እንቅስቃሴዎችን፣ ፊልሞችንና የመሳሰሉ ነገሮችን ማሳየት፣ ማቀነባበር ወይም ማሰራጨት፣

ከ. የዲሲፕሊን ጉዳይ የሚያይ የኮሚቴ አባልን፣ አመልካች ወይም ምስክር ሆኖ የቀረበ ሰውን፣ የተከሳሹን ወይም መከላከያ ምስክሮቹን ማስፈራራትና ውሳኔ እንዳይተላለፍ የማድረግ ሙከራ፣ ማጣራት በትክክለኛ መንገድ እንዳይካሄድ ማድረግ፣

ኸ. ሐይማኖትን መሠረት በማድረግ ለራሱና ተከታዮቹ ልዩ መመገቢያ አዳራሽና ምግብ መጠየቅ፣ መመገቢያ አዳራሽ ውስጥ ከምግብ በፊትና በኋላ ፀሎት ሲያደርጉ ድምጽ ማሰማት፣ በቡድን ድምጽ እያሰሙ መጸለይ፣ ሌሎችን መረበሽ

ወ. ሐይማኖትን መሠረት በማድረግ ለራሱና ተከታዮቹ ልዩ የመመገቢያ ሰዓትና ምግብ በመጠየቅ ሁከት እንዲፈጠር ማድረግ፣

የ. በተማሪዎች ህብረት አባልነት ስም ሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም፣

ደ. በትምህርትና ስልጠና ተቋሙ በሚሰጡ ፈተናዎች ለሌላ ተፈታኝ ተማሪ ወይም አካል ሲፈተን መገኘት፣

ጀ. የሌሎችን የፖለቲካ፣ የኃይማኖት፣ ብሄር፣ ቋንቋ፣ አመለካከት፣ ባህልና እምነት ማንቋሸሽ፣ ማንኳሰስ፣ የሃይማኖት መጽሐፍት ማበላሸት፣ ማቃጠል፣ የበዓላት ቀናትን አሳብቆ መረበሽ፣ ወዘተ፣

k. Negotiating for money or in kind or to cooperate with the perpetrator when another student's ID card, ID or other item is stolen.

l. Engaging in sex work in hotels, nightclubs, or other places, or in similar activities, or acting as a liaison;

m. Displaying the image or revealing the sound of on camera or mobile device without the individual's consent or permission, for any purpose.

n. failing to appropriately manage funds earmarked for student unions or funds received or raised by members of the student club in accordance with the financial expenditure system.

o. Deliberately rebelling against members of a student union, causing trouble, harassing, insulting them based on their ethic or other identities, insulting, and instigating others to stand against them, (provided that formal requests to depose those student union members who have a problem and stand up legally).

p. Forcing to do or not to do something by threatening or intimidating a an employee or a student in the institution;

q. Showing, organizing, or disseminating scenes, activities, films, etc. that may cause moral harm to other students or members of the Institution's community;

r. Intimidating or attempting to distract or prevent a member of a discipling committee investigating a case to make decisions, an applicant, a witness, a defendant or a defense witness;

s. Asking for a special dining room and/or meal for followers on the basis of religion, praying loud before and after meals in dining hall, praying in a group with audible voice, and disturbing others,

t. To cause unrest by asking for special meal and meal time for followers on the basis of religion;

u. Abuse of power in the name of student union membership;

v. Taking exams for another student;

w. Insulting, demeaning, and degrading others for their political outlooks, religious beliefs, ethnicity, language, opinion, culture and beliefs, as well as burning religious books, disturbing the Institution in the name of holiday ceremonies, etc.



Scanned with CamScanner

ገ. ሌሎች በዚህ ምድብ ሊካተቱ የሚችሉ ጥፋቶች ተብለው በትምህርትና ስልጠና ተቋሙ በጽሑፍ የሚለዩ ጥፋቶችን መፈጸም ፣

**17. ከፍተኛ ጥፋቶች**

1) ማንኛውም ሰው በትምህርትና ስልጠና ተቋም ውስጥ ለሰላምታና ለሌላ ለማንኛውም አላማ በእጅ መጨባበጥ፣ የእርስ በእርስ አካላዊ ንክኪ ማድረግ
2) ኮቪድ-19ን ለመከላከል የሚደረጉ የጥንቃቄ መልዕክቶችን ይዘው የተለጠፉት ማስታወቂያዎችን መቅደድ፣ ሌላ ማስታወቂያ ደርቦ መለጠፍ፣ ማበላሸት ወይም በሌላ ቁስ መጋረድ
3) በመማሪያ ክፍሎች እና በምግብ ቤት አዳራሾች እንዲሁም በመዝናኛና በክሊኒክ ቦታዎች በምንም መልኩ ያልተገባ ጩኸት፣ ጠብ፣ ግርግር መፍጠር፣ መረበሽ
4) በአገልግሎት ዙሪያ ቅሬታ ሲኖር ሰላማዊ እና ሕጋዊ መንገድን ተከትሎ መጠየቅ ሲቻል አመፅ ማንሳት፣ ማስነሳትና መተባበር
5) የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በኮቪድ-19 ለሚጠረጠሩ፣ ራሳቸውን ለሚጠረጥሩ እና የበሽታውን የተለያዩ ምልክቶችን ለሚያሳዩ ተማሪዎች የሚሆን የለይቶ ማቆያ ማዕከል በግቢ ውስጥ አለማዘጋጀት
6) በኮቪድ-19 ምክንያት ሞት ብከሰት የሬሳ አያያዝ፣ ማጓጓዝና የቀብር ስነ-ስርዓቱን ጤና ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት አለመያዝና በዚህም በሌሎች ላይ የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ ጉዳት እንዲከሰት የሚያደርግ አሠራር መከተል
7) የትምህርና ስልጠና ተቋማት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ተዘጋጅቶ የተሰጠው ምቹ የሥራ ሁኔታ የተዘጋጀለት የኮቪድ-19 ተጠርጣሪን የሚከታተል ግብረ ኃይል አለማቋቋምና የአሠራር ስርአት አለመዘርጋት
8) ተማሪ ያልሆነ ወይም የተባረረ ተማሪን በተማሪዎች መኝታ ቤት ማሳደር ወይም ማኖር፣
9) በተቋማት ላይ የተጣሉ ግዴታዎችን አለመወጣት (ይህ በየደረጃው ባለው አመራር ላይ የሚቆጠር ጥፋት ነው)
10) የትምህርትና ስልጠና ተቋሙን ህግና ደንብ ለመጣስ፣ የአሰራር ስርአትና የሥራ አመራር ውሳኔ ለመቃዎም ተማሪዎችን ለአድማ፣ ለአመጽና ለረብሻ ማነሳሳት፣ ማስተባበር፣ የሃሰት ወሬ መፍጠርና የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ማስፋፋት፣ ለህገ-ወጥ ሥራ ህብረት መፍጠር፣
11) በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይና በሌላ ቦታ ብጥብጥና ሁከት የሚያስከትል ያልተፈቀዱ ጽሁፎችን መለጠፍ፣
12) በዚህ መመሪያ የተማሪዎች መዝናኛንና ስፖርታዊ እቅስቃሴን በሚመለከት ያሉ ድንጋጌዎችን መጣስ
13) በአግባቡ በመካሄድ ላይ ባለ የዲሲፕሊን ጥፋት ክርክር የመሰማት ሂደት ላይ ጣልቃ መግባትና ማደናቀፍ፣ በስርዓቱ መሠረት ለመዳኘት የሚያመለከቱ ተማሪዎችንና ሠራተኞችን ማደናቀፍ፣ በዲስፕሊን ኮሚቴዎች ላይ ወከባ በመፍጠር በገለልተኝነታቸው ላይ ተፅዕኖ ለመፍጠር መሞከር፣

x. Committing other offenses identified by the Institution that may be included in this category.

**17. Major offenses**

1) Shaking hands and making physical contact with anyone in the educational and training institution for greetings and any other purposes,
2) Tearing down, posting, damaging, or obscuring cautionary messages posted to prevent Covid-19,
3) Making noise, quarreling, and disturbing in and around classrooms, dining halls, as well as in recreation centers, and clinic areas,
4) Causing violence, upraising others for and participating in violent actions when there is a complaint about any service, while it is possible to demand for improvement of the case peacefully and in a legal way,
5) failing to set up a quarantine center on campus for students who are suspected of having Covid-19, and for those who show symptoms of the disease,
6) In the event of death due to Covid-19, failing to handle, transport and bury corpses in accordance with the Directives issued by the Ministry of Health, and causing psychological and social harm to others.
7) Failure to establish a task force to monitor Covid-19 suspect and to establish a system in which a detailed working environment and responsibilities of educational and training institution have been prepared.
8) accommodating a non-student or a dismissed student in one's dormitory;
9) Failure to fulfill the obligations of the institution (this is a violation of leadership at all levels)
10) In violation of the rules and regulations of the Education and Training Institute, inciting students to strike, riot and revolt, as well as coordinating, fabricating rumors and using various media to create illegal collusion.
11) Posting unauthorized notes and/or articles on billboards and elsewhere that may cause unrest;
12) Violation of the provisions regarding student recreation and sporting activities in this Directive,
13) Interfering and obstructing the progressions of disciplinary proceedings, obstructing students and staff applying for judicial proceedings, harassing disciplinary committees and influencing their impartiality;



Scanned with CamScanner

14) እንደ ማሪዋና፣ ካናቢስ፣ ሀሽሽ፣ ኮኬይን ወዘተ ያሉ ዕፆችን መጠቀም፤ በትምህርትና ስልጠና ተቋሙ ግቢ ውስጥ ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ ይዞ መገኘት ወይም በድብቅ ሲያዘዋውር ወይም ሲሸጥ መገኘት፣
15) ተማሪው የፖለቲካ ወይም የብሔር ምክንያቶችን በማንሳት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሰዎችን ለአመጽ ማነሳሳት፣
16) ሆን ብሎ የሌላ ተማሪን የስራ ውጤት መደበቅ ወይም ማጥፋት
17) ገንዘብ ወይም ሌላ ዋጋ የሚያወጣ ነገር በመስጠት ያልተገባ የትምህርትና ስልጠና ጥቅም ለማግኘት መሞከር፣
18) በትምህርትና ስልጠና ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ በህዝብ ፊት ራቁትን መታየት፣
19) የትምህርትና ስልጠና ተቋም በሚያወጣቸው ሕጎች ተገዢ ለመሆን አለመፈለግ፣ ያለበቂ ምክንያት የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች እንዲቀየሩ አመጽ ማስነሳት፣ ሰላምን ማወክ፣ በተደጋጋሚ እንደማይለወጡ ተነገሮ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን፣
20) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በግልም ሆነ በቡድን በማንኛውም መልኩ የተቋሙን ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት የሚያውክ እንቅስቃሴና ተግባራትን ማቀድ፣ መፈጸም፣ ማስተባበር፣ መተባበር የተከለከለ ነው፡፡
21) ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ማኅበረሰብ አባል በግልም ሆነ በቡድን ፖለቲካ፣ ኃይማኖት ወይም ብሔር ተኮር የግጭት መንስኤና አባባሽ የሆኑ፣ አለመግባበትና ጥርጣሬ የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎችና ተግባራትን መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

**18. በጣም ከፍተኛ ጥፋቶች**

1) ከፍተኛ የዲሲፐሊን ጥፋቶችን ፈጽሞ በተወሰደው እርምጃ መሻሻል ሳያሳይ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ፈፅሞ መገኘት፣
2) ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም የፊት ለፊት ትምህርትና ስልጠና መስጠት መጀመር እንደሚችል ከሚመለከተው አካል ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ/ፈቃድ ሳይሰጥ እንዲሁም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስራውን በተመለከተ የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር ወይም ሳይከተል ትምህርትና ስልጠና መስጠት
3) ማንኛውም ሰው በትምህርትና ስልጠና ተቋም ውስጥ ኮቪድ-19 እንዳለበት እያወቀ ወደ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ውስጥ መግባት፣ ከትምህርትና ስልጠና ተቋም ማህበረሰብ ጋር መቀላቀል ወይም ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ በሚችልበት ሁኔታ ከሌሎች ከትምህርትና ስልጠና ተቋማት ማህበረሰብ አባላት ጋር መገናኘት ወይም በሀሰት ቫይረሱ እንዳለበት/እንዳለባት አድርጎ ማስመሰል

14) Use of drugs such as marijuana, cannabis, hashish, cocaine, etc. Occupation of inside or outside the premises of the Education and Training Institution;
15) improperly inciting people to violence, citing political or ethnic reasons;
16) Deliberately hiding or destroying another student's performance
17) Trying to gain undue education and training benefits by giving money or other valuables;
18) being naked in public on the premises of the Institution;
19) Unwillingness to comply with the laws issued by the Institution, inciting violence to change education and training programs for no apparent reasons and being unwilling to accept the justifications given by relevant body regardless of the fact that they will not be changed, disturbing peace;
20) It is prohibited for any member of the Institution community to plan, carry out, coordinate or collaborate in any activities and actions that disrupt the peaceful learning and teaching process of the institution in any form, individually or collectively. Doing so would lead to disciplinary measures.
21) It is prohibited for any member of the Institution to engage in activities that cause misunderstandings and suspicions, which are personally or collectively politically, religiously or ethnically motivated actions that ignite conflicts. Doing so would lead to disciplinary measures.

**18. Extreme Offenses**

1) A second misdemeanor, without major improvement in disciplinary actions following performance of those offences under major offences,
2) Resuming classes in the Institution without any decision/permission from the relevant body and without ensuring the fulfilment of necessary condition or without complying with or taking precautionary measures to begin the overall teaching and learning process.
3) Anyone who knows that he's infected with Covid-19 and joins the Institution's community without taking care of others and revealing his case, or contacting with other members of the education community in a way that the virus can be transmitted to other people.



Scanned with CamScanner

4) ማንኛውንም ተቋሙንና የተቋሙን ማህበረሰብ አባላት የተመለከተ የኮቪድ-19 መረጃ ሳይፈቀድለት በተለያዩ መንገዶች መግለጽ
5) ሰላማዊ የመማር ማስተማርን ለማወክ ማቀድ ወይም ማስተባበር ወይም መተግበር ወይም መተባበር
6) በግቢ ውስጥ በቡድን ሆኖ ማንኛውንም ዓይነት ኃይማኖታዊም ይሁን ፓለቲካዊ እንቅስቃሴ ማድረግ
7) ሃይማኖትን፣ ብሔርን፣ ባህልንና ቋንቋን የሚያንቋሽሽ ማንኛውንም ንግግር ማድረግ፤ መጻፍ ወይም ድርጊት መፈጸም
8) ወደ ግቢ ውስጥ ማንኛውም ዓይነት አደንዛዥ እፅ ማዛወር፣ ማብቀል/መትከል፣
9) የትምህርና ስልጠና ማህበረሰብ አባል በምንም ሁኔታ መሳደብ፣ መዝለፍ፣ ማንጓጠጥ፣ ማስፈራራትና መዛት፣ ያልተገባና ፀያፍ ንግግር መናገር
10) በግቢው ውስጥ በግልም ሆነ በቡድን ፀብ ማንሳት ወይም መደባደብ ወይም በነዚህ መሠል ተግባራ መተባበር
11) የስርቆትና የሙስና ተግባር መፈጸም፤
12) በብሔር ወይም በኃይማኖት ወይም በትውውቅ አድሎ መፈፀም
13) የሌሎችን ብሔር ወይም ኃይማኖት የሚጎዳ ድርጊት መፈፀም ለምሳሌ፡- መንፈሳዊ መጽሐፍት፣ ስዕሎችና ቅርፃቅርፆች፣ ሐይማኖታዊ ምልክቶች እንዲቃጠሉ ወይም ቅርፃቸው እንዲጠፉ ማድረግ፣
14) ድምጽ ባለው ወይም በሌለው መሣሪያ የትምህርትና ስልጠና ተቋምን ማህበረሰብ አባል ሆነ ከትምህርትና ስልጠና ተቋሙ ውጭ ያሉ የማህበረሰብ አባላትን መጉዳት ወይም ለመጉዳት ሙከራ ማድረግ፣
15) በትምህርትና ስልጠና ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትሉ የሚችሉ ስለታማና ተተኳሽ መሳሪያዎች ወይም መርዛማ ነገሮችን ይዞ መገኘት፣ ለመግባት መሞከር
16) አስገድዶ መድፈር ወይም የተቃራኒ ፆታውን የመከላከል አቅም በጉልበት ወይም በስነ-ልቦና ጫና በማድከም ፆታዊ ጥቃት ማድረስ ወይም ለማድረስ መሞከር፣ በጉልበት ገፍቶ ወደ ተቃራኒ ፆታ መኝታ ቤት መግባት፤፤
17) በትምህርትና ስልጠና ተቋሙ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆን ብሎ ወይም በቸለልተኛነት ወይም በጥንቃቄ ጉድለት ቃጠሎ ለማስነሳት መሞከር ወይም ማስነሳት፣
18) በተጭበረበረ የትምህርትና ስልጠና ማስረጃ ተመዝግቦ መገኘት፣
19) ፊርማን መኮረጅ ወይም ሰነድን መደለዝ፣ በመሰረዝ ማጭበርበር፣ ለማጭበርበር መሞከር፣

4) Disseminating any Covid-19-related information about the institution and community members therein in various ways without permission.
5) Planning or coordinating or implementing or disrupting the peaceful teaching learning process.
6) Performing any kind of religious or political activity in a group on campus
7) Making any derogatory speech that offends others' religion, ethnic group, culture and language; as well as in writing or acting.
8) Transferring, growing / planting any type of illicit drug in the premises of the Institution;
9) Insulting, disrespecting, harassing, threatening and intimidating a member of the Institution's community, and making inappropriate and obscene remarks against an individual.
10) Arguing or fighting in the campus, either individually or as a group, or cooperating in such activities
11) Committing theft and corruption;
12) Discriminating others on the basis of ethnicism, religion or acquaintance,
13) Engaging in acts that harm other ethnics or religions, such as burning spiritual books, paintings and sculptures, religious symbols, or destroying images;
14) harming or attempting to harm members of the community outside the Institution with weaponries;
15) Possession of dangerous and deadly weapons or toxic materials on the premises of the Institution, or attempting to bring them into campuses,
16) Raping or attempted sexual assault by force or by putting psychological pressure to weaken the opposite sex's defense; entering the opposite sex's dormitory;
17) Setting or attempting to set fire to, intentionally or unintentionally, recklessly, the premises of the Institution;
18) Getting registered using fraudulent certificates,
19) Copying signatures or deleting documents, deleting fraudulently, attempting to defraud;



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

20) በማስፈራራትና ጉልበት በመጠቀም የሌላ የተቋሙን ማህበረሰብ አባል ንብረት መውሰድ ወይም ለመውሰድ ሙከራ ማካሄድ (ዘረፋ መፈፀም) ፣
21) ተገቢውን ክፍያ ሳይፈጽም ወይም የወጭ መጋራት ውል ሳይፈርም መማር ወይም የአገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን መሞከር፣
22) የሌላ ተማሪን ቋንቋ፣ ብሔር፣ ሐይማኖት እና ማንነት ማንቋሸሽ፣
23) ተማሪው ባገኘው ውጤት ወይም ሠራተኛው በተሰጠው የሥራ አፈጻጸም ውጤት ቅር በመሰኘት በመዛኙና በመዛኙ ቤተሰብ ላይ ጉዳት ለማድረስ መሞከር ወይም ማድረስ፣
24) በመመገቢያ አዳራሽ አካባቢ ከምግብ ጋር አያይዞ ወይም በየትኛውም ምክንያት ዓመጽ ማስነሳት ወይም ለማስነሳት መሞከር፣ በስራ ላይ ያሉ ስራተኞችን መደባደብ፣
25) ሌሎች ከነዚህ ጋር ይመሳሰላሉ ብሎ ተቋሙ በጽሑፍ የሚጨምራቸው ጥፋቶች

## 19. የቅጣት ዓይነቶች

በዚህ መመሪያ መሠረት ጥፋት በፈጸሙ የትምህርና ስልጠና ተቋማትና ማህራሰብ አባላት ላይ ሊወሰዱ የሚችሉ ቅጣቶች የሚከተሉት ናቸው:

1) የቃል ግሳጼ፤ በጽሑፍ የሚሰጥ የቃል ማስጠንቀቂያ
2) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ (ቀላል፣ ከባድና የመጨረሻ)
3) ስለ ጉዳዩ ለቤተሰብ ማሳወቅ
4) ማህበራዊ አገልግሎት የሚያሰጥ ቅጣት፣
5) ጥፋት የፈፀመበትን ንብረት መውረስና በጥፋቱ የተጎዱ ወይም ዋጋቸው የቀነሰ፣ ወይም ሙሉ በሙሉ የወደሙ ንብረቶች ወይም ሕንፃዎች፣ ተገጣጣሚዎች ካሉ የሚተኩ ከሆኑ እንዲተኩ ማድረግ፣ ካልሆነ የትምህርትና ስልጠና ተቋሙ በባለሙያ አስጠንቶ በሚያቀርበው የወቅቱ የገበያ ዋጋ መሠረት ዋጋውን ማስከፈል
6) የወር ደመወዝ ቅጣት
7) ከኃላፊነት ቦታ ማስነሳት
8) ከኃላፊነት ቦታዎች ውድድር መታገድ ወይም በድጋሚ በኃላፊነት ቦታዎች እንዳይሰም ማገድ
9) ደረጃ ዝቅ ማድረግ
10) ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርትና ስልጠና ዕድልና የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ለውጥ ወይም ጥቅማ ጥቅም ማገድ
11) ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርትና ስልጠና ማገድ
12) የትምህርትና ስልጠና ማስረጃን ለተወሰነ ጊዜ መያዝ
13) የትምህርትና ስልጠና ማስረጃ ፈጽሞ አለመስጠት
14) ሙሉ በሙሉ መሰናበት
15) ጉዳዩን በወንጀል ወይም በፍታብሔር ሕግ እንዲታይ ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ
16) በተቋም ደረጃ የተጣለውን ግዴታ ያላሟላ ተቋም ከስድስት ወራት እስከ ሶስት ዓመት በጊዜያዊነት ትምህርትና ስልጠና እንዳይሰጥ ሊታገድ ይችላል፡፡

20) Taking or attempting to take the property of another member of the institution through intimidation and force (robbery);
21) Learning or attempting to be a beneficiary of a service without making appropriate payment or signing a cost sharing agreement,
22) Disdaining other students' language, ethnicity, religion and identity;
23) Attempting to inflict harm on a teacher, an employee or evaluator of performance and/or his family for low performance score;
24) Attacking or attempting to provoke or incite violence in the vicinity of a dining hall related to quality or whatsoever of food,
25) Other offenses that are similar to these which the institution includes in writing.

## 19. Types of penalties

Penalties to be imposed on any member of the education and training institution for failing to act in accordance with this Directive are as follows:

1) Verbal reprimand, verbal warning given in writing,
2) Written warning (simple, hard and final)
3) Informing students' family about the matter
4) Punishment in the form of providing social services;
5) Confiscation of property used by an offender; replacement of damaged or devalued, or completely destroyed property or buildings, if any of the fittings are to be replaced, otherwise the price shall be charged in accordance with the current market value provided by the Institution.
6) Salary deduction or suspension,
7) Removal from leadership post
8) Suspension from competition for leadership positions, or indefinitely ban for reapplication to leadership positions
9) Demotion from positions
10) Suspension from education and training opportunities and promotions, salary increases or benefits for a period of time
11) Suspension from education and training for a period of time
12) Holding education and training certificates for a period of time
13) Complete denial of education and training certificates
14) Complete dismissal or firing from job
15) Referring the matter to criminal or civil law for further cause
16) An institution that does not fulfill its obligations at the institutional level may be temporarily suspended from providing education and training for six months to three years.



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

## 20. የቅጣት ዓይቶች ከነምድባቸውና ከተጠያቂ አካላት ጋር

| ንዑስ አንቀጽ | የጥፋት ምድብ | የዚህን መመሪያ ድንጋጌ በመተላለፋቸው ተጠያቂ የሚሆኑት አካላትና የቅጣት ዓይነት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተማሪዎች | መምህራን | አስተዳደር ሰራተኛ | አመራር |
| 1) | አነስተኛ | • ምክር<br>• የቃል ማስጠንቀቂያ | የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | • ምክር<br>• የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ |
| 2) | ቀላል | • ጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም<br>• ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና 30-50 ሰዓት ማህበራዊ አገልግሎት | • ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ<br>• የአንድ ወር ደመወዝ ቅጣት | • ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ<br>• የአንድ ወር ደመወዝ ቅጣት | • የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ<br>• የአንድ ወር ደመወዝ ቅጣት |
| 3) | መካከለኛ | ከአንድ ወሰነ ትምህርት እስከ ሁለት ዓመት የሚያስቀጡ | • የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያና<br>• የሶስት ወር ደመወዝ ቅጣት | • የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያና<br>• የሶስት ወር ደመወዝ ቅጣት | • ከኃላፊነት ቦታ ማስነሳትና<br>• የሶስት ወር ደመወዝ ቅጣትና<br>• እስከ 5ዓመት ከኃላፊነት ቦታዎች ውድድር መታገድ |
| 4) | ከፍተኛ | ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት ከትምህርትና ስልጠና ገበታ መታገድ | • አንድ ደረጃ ዝቅ ማድረግ እና 3 ወር ደመወዝ ቅጣት<br>• ከ2-3 ዓመት<br>○ ከትምህርትና ስልጠና ዕድልና የደረጃ ዕድገት፣<br>○ የኃላፊነት ቦታ ውድድር፣<br>○ የደመወዝ ለውጥ<br>○ ጥቅማ ጥቅም መታገድ | • አንድ ደረጃ ዝቅ ማድረግ<br>• ከ2-3 ዓመት<br>○ ከትምህርትና ስልጠና ዕድልና የደረጃ ዕድገት ውድድር፣<br>○ የኃላፊነት ቦታ ውድድር፣<br>○ የደመወዝ ለውጥ<br>○ ጥቅማ ጥቅም መታገድ | • ከኃላፊነት ቦታ ማስነሳትና<br>• አግባብነት ባለው ሕግ መጠየቅና<br>• በድጋሚ በኃላፊነት ቦታዎች አይሰየምም<br>• ከ2-3 ዓመት:-<br>○ የደረጃ ዕድገት ውድድር፣<br>○ የደመወዝ ለውጥ<br>○ ጥቅማ ጥቅም መታገድ |
| 5) | በጣም ከፍተኛ | • ከትምህርትና ስልጠና ተቋም የትምህርትና ስልጠና መርሃ-ግብር ሙሉ በሙሉ መሰናበት እና<br>• ለ2ዓመት በየትኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም መማር አይችልም | • ከሥራ ገበታ ሙሉ በሙሉ መሰናበት እና<br>• እስከ 3ዓመት በየትኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ውስጥ በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት ቅጥር መፈጸም አይችልም:: | ከሥራ ገበታ ሙሉ በሙሉ መሰናበት | • ከሥራ ገበታ ሙሉ በሙሉ መሰናበት እና<br>• አግባብነት ባለው ሕግ መጠየቅ |
| 6) | የትምህርትና ስልጠና ተቋም በተቋም ደረጃ የተጣለበትን ግዴታዎች ሳይወጣ ቢቀር ወይም በተቋም ደረጃ ሊያሟላ የሚገበውን የግዴታ ጉዳዮች ባያሟላ በበላይ አመራሩ ላይ የሚጣለው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ ከስድሰት ወራት እስከ ሶስት ዓመት በጊዜያዊነት ትምህርትና ስልጠና እንዳይሰጥ ሊታገድ ይችላል:: ቀጣይ ዝግጅቱም በልዩ ሁኔታ በተከታታይ እየተገመገመ የሚመራ ይሆናል:: አጠቃላይ ሂደቱም እንደአስፈላጊነቱ በመገናኛ ብዙሃን ሊገለጽ ይችላል:: | | | | |



በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

**20. Types of penalties with their categories and accou ntable parties**

| Sub-Article | Offense Category | The parties responsible for violating the provisions of this Directive and the type of Penalties | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | Students | Academic Staff | Administrative staff | leaders |
| 1 | Minor | Reprimand<br>Verbal Warning | Written Warning | Reprimand<br>Written warning | Severe written warning |
| 2 | Simple | Written warning<br>Severe written warning and 30-50 hours of social service | Severe written warning<br>One-month salary penalty | Severe written warning<br>Three-month salary penalty | Final written notice<br>One-month salary penalty |
| 3 | Medium | Misconducts resulting in penalties from one semester to two years | Final written warning<br>Three-month salary penalty | Final written notice and<br>Suspension of three-month salary | Dismissal<br>Three-month salary penalty<br>Suspension from competition for leadership positions up to 5 years |
| 4 | Serious offenses | Misconducts punishable by a maximum of two to three years (dismissal from the Institution) | Postponement of academic rank for a period not exceeding two years and three-month salary penalty<br>Suspension for 2-3 years of<br>An opportunity to further education, or postponement of the next promotion competition for leadership positions,<br>Salary increase<br>Other benefits | Demotion one level from current position<br>2-3 years<br>Suspension for 2-3 years of<br>an opportunity to further education, or postponement of the next promotion competition for leadership positions,<br>Salary increase<br>Other benefits | Dismissal from position<br>Accountable by appropriate law<br>Suspension from reappointment as a leader<br>• Suspension for 2-3 years of<br>the next promotion,<br>salary increase<br>benefits |
| 5 | Very Serious | Complete dismissal from the Institution<br>Ban for 2 years to study in any educational institution. | Complete dismissal<br>Ban for 3 years to be employed on a permanent or temporary basis in any educational or training institution. | Complete dismissal | Complete Dismissal<br>• hold accountable by appropriate law |
| 6 | If the institution of education and training fails to fulfill its obligations at the institutional level or does not meet its obligations as stipulated in this Directive, the institution may be temporarily suspended from providing education and training for a period of six months to three years. The Institution's next readiness shall be assessed by a series of special reviews. The whole process can be described in the media as needed. | | | | |



Scanned with CamScanner

## ክፍል ስምንት
## የዲሲፕሊን ኮሚቴ

### 21. የዲሲፕሊን ኮሚቴ ስለማቋቋም

የተማሪዎችና የሠራተኞች (መምህራንና አስተዳደር ሠራተኛ) ዲስፕሊን ኮሚቴ በተቋም ደረጃ እና በካምፓስ ደረጃ ጸንተው ባሉ ህጎች መሠረት በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚቋቋም ነው፡፡

### 22. የዲሲፕሊን ኮሚቴው ተጠሪነት

1) በተቋም ደረጃ ያለ የዲሲፕሊን ኮሚቴ አስተዳደር ዘርፍን ለሚመራ ምክትል የተቋም ኃላፊ ተጠሪ ይሆናል፡፡
2) በካምፓስ ደረጃ ያለ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለካምፓሱ ኃላፊ ይሆናል፡፡
3) ስለሆነም ኮሚቴው ማንኛውንም የዲሲፕሊን ክስ የውሳኔ ሐሳብ ተጠሪ ለሆኑበት አካላት በማቅረብ ያስጸድቃል፡፡

### 23. የተማሪዎች የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባላት

ስብጥሩም ከመምህራን፣ ከተማሪዎች ህብረትና ከአስተዳደር ሠራተኞች የተውጣጡ አባላት ያሉት ይሆናል።

1) የተማሪዎች የዲሲፕሊን ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል፡፡ እነርሱም፡-
   - ሀ. አንድ ነባር መምህር ...................................ሰብሳቢ (በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም)
   - ለ. ሁለት የተማሪዎች ህብረት ተወካዮች (አንድ ወንድና አንድ ሴት............አባል (በተማሪዎች ህብረት ስራ አስፈጻሚ የሚወከል)
   - ሐ. የመምህራን ማህበር ተወካይ...........................አባል (በመምህራን ማህበር ሰብሳቢ ወይም ም/ሰብሳቢ)
   - መ. አንድ የአስተዳደር ሠራተኛ.........................አባልና ፀሐፊ (በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም)

2) የሠራተኞች የዲሲፕሊን ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል፡፡ እነርሱም፡-
   - ሀ. አንድ ነባር መምህር ...........................................ሰብሳቢ (በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም)
   - ለ. የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ዳይሬክተር......................አባል
   - ሐ. የመምህራን ማህበር ተወካይ-...............................አባል (በመምህራን የሚወከል)
   - መ. የአስተዳደር ሠራተኞች ተወካይ ...........................አባል (በሠራተኞች የሚወከል)
   - ሠ. አንድ ነባር የአስተዳደር ሠራተኛ ...................አባልና ፀሐፊ (በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም)

## Part Eight
## Disciplinary Committee

### 21. Establishment of Disciplinary Committee

Student and Staff (Teachers and Administrative Staff) Disciplinary Committees shall be established by the top leader of the institution in accordance with applicable laws at the institutional level and on campus.

### 22. Accountability of the Disciplinary Committee

1) The Committee shall be accountable to the Administrative vice President/Director/Head of the Institution.
2) A disciplinary committee at the campus level shall be responsible for the campus leader.
3) the committee shall submit any disciplinary decisions to the responsible bodies for approval.

### 23. Members of the Student Discipline Committee

The composition of the committee shall consist of members from teachers, student unions and, as needed, administrative staff.

1) The Student Disciplinary Committee shall have five members. They:
   - a. Senior academic staff ............ Chairperson (to be appointed by the head of the institution)
   - b. Two student union representatives (one male and one female ............ member (represented by student union executive)
   - c. Teachers Union representative .........Member (by the Chairman or Vice-Chairman of the Union of Teachers)
   - d. Administrative staff .................... Member and Secretary (designated by the head of the institution)

2) The staff disciplinary committee shall have five members, which include:
   - a. Senior Academic Staff ............ Chairperson (to be appointed by the head of the institution)
   - b. Director of Women, Children and Youth......Member
   - c. Teachers' Union Representative ...... Member (represented by teachers)
   - d. Administrative Staff Representative...Member (represented by staff)
   - e. Senior administrative staff ............ Member and Secretary



Scanned with CamScanner

**24. የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባላት የሚከተሉትን ሊያሟሉ ይገባል፤**

1) በተቋሙ ውስጥ በስነ-ስርዓት አክባሪነታቸው፣ በታማኝነታቸውና በቁርጠኝነታቸው የሚታወቁና ፍትሃዊና ሚዛናዊ እይታ ያላቸው፤ የማያዳሉ፤
2) በዲሲፕሊን ጥፋት ተከሰውና ተቀጥተው የማያውቁ
3) በተቋሙ ውስጥ በአብዛኛው ወገን ተቀባይነት ያላቸው
4) በተቋሙ ቢያንስ የአንድ ዓመት ቆይታ ያላቸው
5) ከላይ በንዑስ 1) እስከ 4) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ ተቋም/ካምፓስ ሲቋቋም የተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚወስን ይሆናል::

**25. የኮሚቴው ሥልጣን**

1) ኮሚቴው የቀረበለትን የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ በዚህ መመሪያ መሠረትና ሌሎች በተቋሙና በተቋሙ ማህበረሰብ ላይ ተፈፃሚነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል::
2) የዲሲፕሊን ኮሚቴ በይግባኝ የቀረበ ከሆነ መርምሮ የውሳኔ ሃሳቡን ለአስተዳደር ዘርፍ ምክትል ኃላፊ ያቀርባል::
3) ከሱን በሚመለከት ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም የሥራ ክፍል መረጃው ጠይቆ የመውሰድ፣ ማንኛውንም አካል አስቀርቦ የመመርመር ሥልጣን ይኖረዋል:: የሥራ ክፍሎችም የመተባበር ግዴታ አለባቸው::

**26. የኮሚቴው አባላት መጓደል**

ከኮሚቴው ውስጥ አንድ አባል የተጓደለ ከሆነ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ እንዲያውቀው ተደርጎ በኮሚቴው ሰብሳቢ አቅራቢነት ተጠሪ የሆኑበት የቅርብ ኃላፊ ተተኪ ይመድባል:: ከአንድ በላይ አባል ከሆነ ግን የኮሚቴ አሰየየምን ተከትሎ ይፈጸማል::

**27. ከኮሚቴ አባልነት ስለመነሳት**

1) የኮሚቴው ሰብሳቢ ከሳሽ በሚሆንበት ጊዜ በአባላቱ ውሳኔ መሠረት ከአባላቱ መካከል አንዱ ሰብሳቢ ይሆናል::
2) የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም ማንኛውም አባል ክስ ከቀረበበት ግለሰብ ጋር የግል ጠብ ወይም የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ለዚህ ጉዳይ ብቻ በጊዜያዊነት ከሰብሳቢነቱ ወይም ከአባልነቱ እንዲነሳ ይደረጋል።
3) ማንኛውም የኮሚቴ አባል ራሱን ከጉዳይ በማግለል በሌላው አባል ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር ወይም ችግር ውስጥ ለማስገባት ከባለጉዳይ ጋር እየተገናኘ ሚስጢር ያወጣ ወይም ቃለ ጉባኤዎችን፣ መረጃዎችንና ጽሁፎችን ለባለጉዳይ ያሳየ ወይም የገለጸ ወይም የሰጠ እንደሆነ ከአባልነቱ ይነሳል፣ በከፍተኛ የዲስፒሊን ጥፋትም በአባላቱ ወይም በሰብሳቢው ይከሰሳል፤ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል።

**24. Members of the Disciplinary Committee shall meet the following criteria:**

1) They should be disciplined, honest and committed and have a fair and balanced view; be impartial:
2) Those who have never been prosecuted and punished for disciplinary offenses
3) Respected and accepted by the majority of the community in the institution
4) Those who have at least one year of service in the institution
5) Subject to sub-articles 1 to 4, in the establishment of a new institution/campus the head of the Institution shall determine the members of the committee.

**25. Powers of the committee**

1) The Committee shall investigate allegations of disciplinary offenses in accordance with this Directive and other laws applicable to the institution and the community of the institution.
2) The Disciplinary Committee shall, upon appeal, examine and recommend the decision to the Administrative vice President or Deputy Head of the Institution.
3) It shall have the power to inquire into any part of the work in connection with the case and to investigate any part of the case. Work units also have a duty to cooperate.

**26. Incompleteness of Committee Members**

If a member of the committee is absent, the head of the institution shall be notified and the chairperson of the committee shall submit a nominee to the immediate head for which the committee is accountable for appointment to replace the absentee. If there is more than one member, it will be done following the procedures of committee appointment.

**27. Withdrawal from committee membership**

1) When the chairperson of the committee is the plaintiff, one of the members shall be the chairperson in accordance with the decision of the members.
2) Where the chairperson or any member of the committee finds that he or she has personal conflict, or kinship or marital relationship with the accused person, he or she shall be temporarily removed from the chair or membership only for this purpose.
3) Any member of the committee who excludes himself or herself from the case, in order to influence or cause trouble for another member, shall be removed from his membership if he communicates with the client or discloses secrets, minutes, evidence and articles to the client; This shall be considered as severe breach of duty for which necessary administrative action shall be taken.



Scanned with CamScanner

4) ማንኛውም የኮሚቴ አባል በተደጋጋሚ ያለ ማንም ፈቃድ የኮሚቴ ስብሰባ ጥሪ ሲደረግ የሚቀር ከሆነ የጽሑፍ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ይደረጋል፤ ጉዳዩም በፋይሉ ውስጥ እንዲያያዝ ይደርግና ከአባልነቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡ በዲስፐሊን ጥፋትም ሊጠየቅ ይችላል፡፡

## 28. የኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤና ድምጽ አሰጣጥ፤

1) በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ግማሽ (50%) አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ሙሉ ይሆናል፡፡
2) አከራካሪ ጉዳይ ሲያጋጥም የኮሚቴው አስተያየት የሚያልፈው በድምጽ ብልጫ ሲሆን እኩል በኩል ከሆነ ሰብሳቢው ባለበት ወገን የቀረበው ሃሳብ ይፀድቃል፤ በሃሳብ የተለየ አባል ካለ የተለየበት ምክንያት በቃለ ጉባኤው ላይ ይሰፍራል፡፡
3) ሰብሳቢው የክስ ሂደቱን በአግባቡ መምራት አለበት፡፡ በክርክሩ ወቅት አንድ የኮሚቴ አባል የስነ-ምግባር ግድፈት ካሳየ ከስብሰባው በጊዜያዊነት እንዲወጣ ማድረግ ይችላል፡፡ ይህ ምልዓተ ጉባኤውን ሊያጎል የሚችል ከሆነ አስተዳደር ዘርፍ ም/ኃላፊ እንዲያውቀው በማድረግ የጎደለው አባል እንዲተካ ወይም ባሉት አባላት ውሳኔ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4) ማንኛውም የኮሚቴው አባል በስብሰባው ኖረም አልኖረም የሃሳብ ልዩነት ኖረውም አልኖረውም በቃለ ጉባኤው ላይ ይፈርማል፣

## 29. የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜና የአባላት ሰዓት አከባበር

1) ኮሚቴው የሚሰበሰብበትን ቀንና ሰዓት እንደየከሱ ጉዳይ አንገብጋቢነትና ብዛት እየታየ በኮሚቴው ሰብሳቢ ይወሰናል፡፡ ቢያንስ ከአንድ ቀን በፊትም ለአባላቱ አመቺ በሆነ መንገድ የሚገለጽ ይሆናል፡፡
2) ማንኛውም የኮሚቴው አባል አስቀድሞ ሰብሰቢውን ሳያስፈቅድ፣ አሳማኝ ባልሆነ ሰበብ አስባብ ለተደጋጋሚ ቀናት ቢቀር ወይም ስብሰባውን ቢያስተጓጉል ሰብሳቢው በሚያቀርበው ማስረጃ መሠረት በአስተዳደር ዘርፍ ም/ኃላፊ በኩል ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## 30. የዲሲፐሊን ኮሚቴው የስራ ዘመን

የኮሚቴው የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አባላት እንደገና ተመርጠው ለሁለት ዙር ብቻ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

4) If any committee member is repeatedly absent from a committee meeting without permission, he or she shall be required to present a written explanation for his/her case; the case shall be attached to his/her personal file; his/her membership shall be terminated. Disciplinary action may also be taken.

## 28. Plenary and vote of the committee;

1) The quorum shall be full if half (50%) of the members are present at the meeting.
2) In the event of a dispute, the committee's opinion shall be passed by a majority vote, and if the same number of committee members support two proposed solutions for the disputing case, the proposal supported by the chairperson shall be approved; if a member disagrees on an issue, he/she can get his/her reasons shall be recorded in the minutes.
3) The Chairperson must conduct the proceedings of the case properly. If a committee member demonstrates misconduct during the debate, he or she may be temporarily expelled from the meeting. If this may abate the quorum, the chairperson may inform the Administrative Deputy Head of the Institution to allow the missing member to be replaced or to allow the committee to make decision by the existing members.
4) Any member of the committee, whether present or not during the meeting, shall sign the minutes of the meeting.

## 29. Observation of Committee Meeting Time and Member Punctuality

1) The date and time of the meeting of the committee shall be determined by the chairperson of the committee depending on the urgency and number of cases. The meeting date and time shall be announced at least one day in a way that is convenient to the members.
2) Any member of the committee who, without prior approval of the Chairperson, is absent for several days without good reason or interrupts the meeting, shall be subject to appropriate administrative action by the Administrative Deputy Head of the Institution on the basis of the evidence presented by the Chairperson.

## 30. Term of the Disciplinary Committee

The term of office of the Committee shall be two years. However, members can be re-elected and serve only two terms.



Ministry of Science and Higher Education
Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

## ክፍል ዘጠኝ
## የሥነ-ስርዓት ድንጋጌዎች

### 31. የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ አመሠራረት

1) ማንኛውም ከመማር ማስተማር ጋር የተያያዙ ጥፋቶችን ተፈጽመው ሲገኙ ግለሰቡ (ተማሪ፣ መምህር፣ አስተዳደር ሠራተኛ) አባል ሆኖ ያለበት የትምህርት ክፍል ኃላፊ ወይም የሥራ ክፍል ኃላፊ በጽሑፍ የተደራጀ ክስ ይመሰርታል፡፡ ይህም ከምዘናና ከፈተና አስተዳደር፣ ከቤተ መጽሐፍት፣ ከሪጅስትራር፣ ከመማሪያ ክፍል፣ ከዩኒቨርሲቲ ውስጥና ከዩኒቨርሲቲ ውጭ ባሉ ቤተ ሙከራዎች፣ በመስክ ላይ በሚደረግ የተግባር ትምህርትና ልምምድ፣ ከዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር፣ ከመምህራን፣ ከወርክሾፕና ከላቦራቶሪ ሠራተኞች ጋር በተገናኘ እና መሠል ከመማር ማስተማሩ ጋር ተያያዥ የሆኑ ዲስፕሊን ጥፋቶችን ያካትታል፡፡
2) ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት ማንኛቸውም ጥፋቶች በተማሪዎች ተፈጽመው ሲገኙ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ተደርገው ተወስደው የተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር ክስ ይመሰርታል፡፡
3) ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት ማንኛቸውም ጥፋቶች በመምህራን ወይም በአስተዳደር ሠራተኞች ተፈጽመው ሲገኙ በሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይከተር ክስ ይመሰርታል፡፡

### 32. የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ አቀራረብ

ማንኛውም የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች ተከትሎ ይቀርባል፡፡

1) ማንኛውም የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ በጽሑፍ ይቀርባል።
2) የዲሲፕሊን ጥፋት የክስ ጽሑፍ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡
   ሀ. የከሳሹን ስም፣ ፊርማና አድራሻ እንዲሁም ክሱ የተመሰረተበት ቀን
   ለ. የተከሳሽ ስም፣ የሥራ ክፍል፣ መታወቂያ ቁጥር፣ የትምህርትና ስልጠና ዓመት (ለተማሪ)
   ሐ. የዲሲፕሊን ጥፋቱ የተፈፀመበትን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት
   መ. የዲሲፕሊን ጥፋቱን ዝርዝር ማብራሪያ
   ሠ. የተከሰሰበት የዲሲፕሊን ጥፋቱ ደረጃ
   ረ. የማስረጃዎች ዝርዝር (ምስክር/እማኝ ካለ ስምና አድራሻ እንዲሁም የጽሑፍ) ከዋናው ጋር የተመሳከረ ቅጂ በማያያዝ
   ሰ. ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ (ካለ)
   ረ. ተከሳሹ ከአንድ በላይ በሆነ የዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰ ከሆነ ለእያንዳንዱ ጥፋት ተለይቶ ከላይ (ሀ)- (ሰ) በተመለከተው መሠረት መቅረብ አለበት፡፡
   ሸ. በጋራ እና ተመሳሳይ ጥፋት የተሳተፈ ከሆነ በጣምራ ሊከሰሱ ይችላሉ፡፡

## Section Nine
## Discipline provisions

### 31. Establishing Charges for Disciplinary Offenses

1) In the event of any misconduct related to teaching and learning, the head of the department or the section of which the individual (student, teacher, administrative staff member) is a member shall file a written complaint. This includes disciplinary offenses related to assessment and testing management, libraries, registrar, classrooms, university and out-of-university laboratories, field-based learning and practice, university-industry linkages, faculty, workshops and laboratory staff, and so on. .
2) Any offense other than those mentioned in sub-article (1) above shall be considered administrative matters and the Director of Student Affairs shall process the prosecution.
3) Any offense other than those mentioned in sub-article (1) above shall be prosecuted by the Director of Human Resource Development and Administration when it is committed by teachers or administrative staff.

### 32. Disciplinary offenses presentation

Any disciplinary offense shall be subject to the following provisions.

1) Any disciplinary offense shall be filed in writing.
2) Disciplinary misconduct charge sheet should include the following.
   a. Plaintiff's name, signature and address, as well as the date of the indictment
   b. Defendant's name, class, ID number, year of education and training (for student)
   c. The place, date and time of the disciplinary offense
   d. Detailed description of the disciplinary offense
   e. Level of disciplinary offense charged
   f. List of evidence (name and address of witness, as well as written evidence, if any) by attaching a certified copy to the original
   g. Additional evidence (if any)
   h. If the defendant is charged with more than one disciplinary offense, it must be set aside for each offense as set out in (a) - (g).
   i. If the disciplinary offence is carried out jointly, the perpetrators shall be prosecuted together.



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

**33. ክስ መመስረቻ ጊዜ**

1) የዲሲፕሊን ጥፋቱ ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፤
2) የዲሲፕሊን ጥፋቱ አነስተኛ ከሆነና ለዲስፕሊን ኮሚቴ መቅረብ የሌለበት ከሆነ ሥልጣን የተሰጠው አካል ጥሰቱ በተፈጸመ በ3 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ እርምጃ ወስዶ ያሳውቃል፡፡
3) ከላይ በ(1)ና በ(2) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ መሠረት ያልተፈጸመ ከሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተቋሙ ኃላፊዎች ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በየትኛውም ጊዜ ጉዳዩን ማንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡

**34. ክስን ስለማሻሻል**

1) በዲስፕሊን ጥፋት የክስ ጽሁፍ ውስጥ የተገለጸው ጥፋት ዝርዝር በሚመለከት መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ስህተት ወይም ግድፈት መኖሩ ሲታወቅ የውሳኔ ሐሳብ ከመቅረቡ በፊት በማናቸውም ጊዜ ክሱን ማሻሻል ይቻላል፡
2) በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የዲሲፕሊን ክሱ ሊሻሻል የሚችለው በከሳሹ አነሳሽነት ወይም ክሱን በሚያጣራው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ጥያቄ መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡

**35. ክስ ስለማቋረጥ**

1) የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ የቀረበበት ተከሳሽ በሞት ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ከተቋሙ ጋር ያለው ግንኙነት ሙሉ በሙሉ የተቋረጠ እንደሆነ ክሱ መታየት ያቆማል፡
2) ነገር ግን መካከለኛና ከዚያ በላይ የዲሲፕሊን ጥፋት የፈጸመ ተከሳሽ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ለመማር የተመዘገበ ከሆነ ወይም የተቀጠረ ከሆነ ክሱ መታየቱን ይቀጥላል፡፡ ውሳኔውም ለመማር ወደተመዘገበበት ወይም ለመስራት ወደተቀጠረበት አዲሱ ተቋም ለአፈጻጸም ይላካል፡፡ ውሳኔውን የሚፈጽም ተቋም በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔውን ያስፈጽማል፤ ያልተረዳው የግንዛቤ ጉዳይ ካለ ውሳኔውን ያሳለፈውን ተቋም ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3) ከውሳኔ በፊት የዲሲፕሊን ክስ የተመሠረተበት ተከሳሽ ዝውውር አይፈቀድም፡፡

**36. ክስን ስለማሳወቅ**

1) የዲሲፕሊን ኮሚቴ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ የክሱን ጽሑፍና ማስረጃዎች ቅጅ አባሪ በማድረግ የክስ ማስታወቂያ አስፈርሞ ይሰጠዋል፡፡
2) የክስ ማስታወቂያው ክሱ የሚሰማበትን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት የሚገልጽ ሆኖ ክሱ ከሚሰማበት ቀን ቢያንስ ከሶስት የሥራ ቀናት በፊት ለተከሳሹ መድረስ አለበት፡፡

**33. Prosecution time**

1) The disciplinary offense must be filed within 5 working days from the date of the offense;
2) If the disciplinary offense is minor and should not be reported to the Disciplinary Committee, the authorized body shall take action within 3 consecutive working days.
3) Notwithstanding the provisions of (1) and (2) above, if this is not the case, subject to the accountability of the relevant authorities, the heads of the institution concerned may at any time pursue the matter.

**34. Improving the charge**

1) If there is an error or omission on the details of the charge described in the Disciplinary Offense prescription or presentation, the case may be amended at any time before a decision is made.
2) Subject to sub-article (1), the disciplinary sue may be modified at the request of the plaintiff or at the request of the disciplinary committee investigating the case.

**35. Dismissal of charges**

1) A disciplinary charge shall be terminated if the defendant charged with disciplinary misconduct is dead or if he/she discontinue his/her membership of the Institution for any other reason.
2) However, if the defendant commits a moderate or sever disciplinary offense, he/she shall continue to be prosecuted if he is registered or employed in any educational and training institution in accordance with sub-article (a). The decision will be sent to the institution where he/she is registered to study or employed. The decision-making body of the Institution he/she joined shall implement the decision in accordance with this Directive: If there is a misunderstanding, the institution that admitted the student or employed the staff may ask for an explanation from the former Institution.
3) transfer from one institution to another shall not be permitted for a defendant prior to a decision is made about his/her case.

**36. Letting the charge to the defendant**

1) The Disciplinary Committee shall give a copy of the charge with attachment of evidence to the defendant to present his/her response.
2) The charge shall state the place, date and time of the hearing and shall be delivered to the defendant at least three working days prior to the date of the hearing.



Scanned with CamScanner

3) ከሳሹ ሊገኝ ባለመቻሉ ወይም ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ የክስ ማስታወቂያውን ለመስጠት ያልተቻለ እንደሆነ በግልጽ በሚታይ የተቋሙ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ ለአምስት ተከታታይ ቀናት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

**37. የክስ መልስ ስለማቅረብ**

1) ተከሳሽ የክስ መልሱን ማቅረብ ያለበት በጽሑፍ ነው፡፡
2) ተከሳሽ የተከሰሰበት ጉዳይ፡-
   ሀ. በዲሲፕሊን ጥፋት የማያስከስሰው ከሆነ ወይም
   ለ. ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ክሱ ሊታይ አይገባውም የሚል የክስ መቃወሚያ የማቅረብ መብት አለው፡፡
   ሐ. ከላይ (ሀ) እና (ለ) መሠረት የቀረበውን መቃወሚ የዲሲፕሊን ኮሚቴው የተቀበለው እንደሆነ ክሱ እንዲቋረጥ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡ መቃወሚያውን ያልተቀበለው ከሆነ በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ያዘዋል፡፡
   መ. የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ክሱን በማመን ወይም በመካድ መልሱን ማቅረብና ሲጠራም በአካል በመቅረብ ለዲስፕሊን ኮሚቴው ስለጉዳዩ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡
   ሠ. የክስ መልሱ በክሱ ለተጠቀሰው ለእያንዳንዱ የዲሲፕሊን ጥፋት የተሰጠውን ምላሽና ተከሳሹ የሚፈልጋቸውን የመከላከያ ማስረጃዎችን ዝርዝር የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡
   ረ. የክስ መልሱ ተከሳሽ ከዘረዘራቸው የመከላከያ ማስረጃዎች መካከል በእጁ የሚገኙትን የጽሑፍ ማስረጃዎችን ቅጅ የያዘና የዲሲፕሊን ኮሚቴው እንዲያስቀርብለት የሚጠይቃቸውን ማስረጃዎች የትና በማን እጅ እንዳሉ ብግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡
   ሰ. በዲሲፕሊን የተከሰሰ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃዎችን አቅርቦ የማሰማት መብት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ቅረብ በተባለበት ዕለትና ሰዓት ባይቀርብ በቀረቡት ሪፖርቶችና ማስረጃዎች ላይ መሰረት ተደርጎ የቅጣት ውሳኔ ይተላለፍበታል፡፡
   ሸ. በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽ በማመን መልስ የሰጠ እንደሆነ ተጨማሪ ማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ክሱን ከዚህ መመሪያ ጋር በማገናዘብ የውሳኔ ሐሳብ ይቀርባል፡፡
   ቀ. በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽ በመካድ መልስ የሰጠ እንደሆነ ኮሚቴው የሁለቱንም ወገን ምስክሮች በመስማትና ሌሎች ማስረጃዎችን በመመርመር አጣርቶ የውሳኔ ሐሳቡን ያቀርባል፡፡

3) If the plaintiff is unable to attend or refuses to accept the charge, it shall be posted on the notice board of the institution for five consecutive days.

**37. Presenting response to the charge by the defendant**

1) A defendant must file a response to the charge in writing.
2) A defendant has the right to file a counterclaim in the response that:
   a. the case cannot subject him/her to be prosecuted or
   b. the case should not be considered for the reason that a decision has already been made,
   c. if the disciplinary committee accepts the objection based on (a) and (b), it shall recommend that the case be dismissed. If he or she does not accept the objection, the defendant is ordered to respond to the charge.
   d. a defendant who has been charged with a disciplinary offense is obliged to respond to the charge and to report it to the disciplinary committee in person.
   e. The indictment must include a response to each disciplinary offense and a list of defense evidence required by the defendant.
   f. The indictment must contain a copy of the written evidence in the defendant's possession and clearly indicate where and by whom the disciplinary committee is requesting.
   g. a defendant charged with disciplinary action shall have the right to present defense evidence. However, if he does not appear on the date and time, he shall be charged based on the reports and evidence provided.
   h. Unless further investigation is found to be necessary to determine whether the defendant charged with a disciplinary offense has accepted the charge and responded accordingly, a recommendation shall be made in accordance with this directive.
   i. If the defendant has pleaded not guilty to a disciplinary charge, the committee shall hear the testimony of both parties and examine other evidence and shall make its decision.



Scanned with CamScanner

**38. ምስከር ስለመጥራት**

1) የዲሲፕሊን ኮሚቴው ምስከሮች ከሚፈለጉበት አንድ ቀን ቀደም ብሎ ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ መጥሪያ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡
2) በአንድ የዲሲፕሊን ጥሰት ላይ የሚመሰከሩ ምስከሮች በአንድ ጊዜ ተጠርተው ተራ በተራ በኮሚቴው ፊት ቀርበው እንዲመሰከሩ ይደረጋል፡፡
3) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ምስከሮችን ከሳሹ ወይም ኮሚቴው ሊያቀርቡና ምስከርነታቸውም ሊሰማ ይችላል፡፡

**39. የምስከር ቃል ስለመስማት**

1) ምስከሮች ሲሰሙ በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽና ከሱን ያቀረበው አካል ሁለቱም በተገኙበት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን አንዱ ወገን ተነግሮት የቀረ እንደሆነ የምስከሮቹን ቃል ከመቀበል አያግድም፡፡
2) የምስከሮቹ መልስ ቃል ቢቃል የሚመዘገብ ይሆናል፡፡
3) ተከራካሪ ወገኖች የቀረቡ ምስከሮችን ተጨማሪ ወይም መስቀለኛ ጥያቄዎችን መጠየቅና ይህም እንዲመዘገብላቸው ማድረግ ይችላሉ፡፡

**40. በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽ የመጨረሻ ቃል**

የዲሲፕሊን ኮሚቴው የዲሲፕሊን ጥፋቱን የማጣራት ሥራ ከማጠናቀቁ በፊት ተከሳሹ የመጨረሻ ሐሳቡን በተከሰሰበት ጉዳይ ላይ እንዲናገር ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ይህም ቃል በቃል ይመዘገባል፡፡ በቅጣት አወሳሰንም ለቅጣት ማከበጃነት ወይም ማቅለያነት ሊያገለግል ይችላል፡

**41. የውሳኔ ሐሳብ ስለማቅረብ**

1) የዲሲፕሊን ኮሚቴ የዲሲፕሊን ጥፋቱን አጣርቶ እንዳጠናቀቀ ወዲያውኑ የምርመራውን ውጤትና ሊወሰድ የሚገባውን የዲሲፕሊን እርምጃ የሚያመላከት የውሳኔ ሐሳብ ፊርሞ ተጠሪ ለሆነበት ኃላፊ ያቀርባል፤
2) የኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ የሚከተሉትን ሊይዝ ይገባል፤
    ሀ. የተከሳሹን ሙሉ ስም፣ መታወቂያ ቁጥር፣ የሥራ/የትምህርት ክፍል፣ የትምህርት/የስልጠና ዓመት፣ የሚኖርበት ሕንጻና ዶርም ቁጥር፣
    ለ. ተከሳሹ ተማሪ ከሆነ የተማሪውን የትምህርት/የስልጠና ውጤት፣ የሠራኛ ከሆነ የሥራ አፈጻጸም
    ሐ. የተከሳሹ የቀድሞ ሪከርድ
    መ. የዲሲፕሊን ጥፋቱን ዝርዝር፣ ደረጃና የተፈጸመበትን ሁኔታ
    ሠ. የተከሳሽ ምላሽ
    ረ. የምስከሮችን ቃል፣
    ሰ. ዝርዝር የውሳኔ ሐሳብ
    ሸ. የኮሚቴው አባላት ፊርማ ያለበት ቃለ ጉባኤ ከነአባሪ ማስረጃዎች ጋር
    ቀ. የሰብሳቢው ፊርማ ያለበት ሸኚ ደብዳቤ

**38. Calling a witness**

1) The Disciplinary Committee shall summon witnesses to appear before the due date.
2) Witnesses testifying against a disciplinary offense shall be summoned at the same time and testify one by one before the committee.
3) Where necessary, the plaintiff or the committee may present additional witnesses and their testimony may be heard.

**39. Hearing of witnesses**

1) In the presence of witnesses, both the defendant and the plaintiff shall be present. However, if one party is informed but not present, it does not preclude the testimony of witnesses.
2) The oral testimony of the witnesses shall be recorded.
3) The parties may request additional inquiries or cross-examination for witnesses and they can request this be recorded.

**40. The last response of the defendant charged with a disciplinary offense**

Before the disciplinary committee completes its investigation of the disciplinary offense, the defendant is given the opportunity to state his or her final opinion on the case. This shall be recorded verbatim. This can be used to justify or mitigate the level of punishment during the final decision of the committee.

**41. Recommendations**

1) As soon as the Disciplinary Committee investigates the disciplinary offense, it shall conduct the investigation, it shall submit the proceedings and action to be taken fully signed and completed to the immediate head of the Institute to which the committee is accountable.
2) The committee's recommendation should include the following:
    a. Defendant's full name, ID number, department, year of study, building and dorm number,
    b. If the defendant is a student, the student's academic performance, if he/she is an employee his/her result of performance evaluation
    c. Defendant's previous record
    d. Details of the disciplinary offense, the category of the offence, and the circumstances of the incident
    e. Defendant's response
    f. The testimonies of witnesses,
    g. Detailed recommendations
    h. Minutes signed by committee members with attached evidence
    i. Cover letter with the Chairperson's signature



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned with CamScanner

**38. ምስክር ስለመጥራት**

1) የዲሲፕሊን ኮሚቴው ምስክሮች ከሚፈለጉበት አንድ ቀን ቀደም ብሎ ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ መጥሪያ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡
2) በአንድ የዲሲፕሊን ጥሰት ላይ የሚመሰከሩ ምስክሮች በአንድ ጊዜ ተጠርተው ተራ በተራ በኮሚቴው ፊት ቀርበው እንዲመሰከሩ ይደረጋል፡፡
3) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ምስክሮችን ከሳሹ ወይም ኮሚቴው ሊያቀርቡና ምስክርነታቸውም ሊሰማ ይችላል፡፡

**39. የምስክር ቃል ስለመስማት**

1) ምስክሮች ሲሰሙ በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽና ክሱን ያቀረበው አካል ሁለቱም በተገኙበት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን አንዱ ወገን ተነግሮት የቀረ እንደሆነ የምስክሮቹን ቃል ከመቀበል አያግድም፡፡
2) የምስክሮቹ መልስ ቃል በቃል የሚመዘገብ ይሆናል፡፡
3) ተከራካሪ ወገኖች የቀረቡ ምስክሮችን ተጨማሪ ወይም መስቀለኛ ጥያቄዎችን መጠየቅና ይህም እንዲመዘገብላቸው ማድረግ ይችላሉ፡፡

**40. በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተከሳሽ የመጨረሻ ቃል**

የዲሲፕሊን ኮሚቴው የዲሲፕሊን ጥፋቱን የማጣራት ሥራ ከማጠናቀቁ በፊት ተከሳሹ የመጨረሻ ሐሳቡን በተከሰሰበት ጉዳይ ላይ እንዲናገር ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ይህም ቃል በቃል ይመዘገባል፡፡ በቅጣት አወሳሰንም ለቅጣት ማክበጃነት ወይም ማቅለያነት ሊያገለግል ይችላል፡

**41. የውሳኔ ሐሳብ ስለማቅረብ**

1) የዲሲፕሊን ኮሚቴ የዲሲፕሊን ጥፋቱን አጣርቶ እንዳጠናቀቀ ወዲያውኑ የምርመራውን ውጤትና ሊወሰድ የሚገባውን የዲሲፕሊን እርምጃ የሚያመላክት የውሳኔ ሐሳብ ፊርሞ ተጠሪ ለሆነበት ኃላፊ ያቀርባል፤
2) የኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ የሚከተሉትን ሊይዝ ይገባል፤
   ሀ. የተከሳሹን ሙሉ ስም፣ መታወቂያ ቁጥር፣ የሥራ/የትምህርት ክፍል፣ የትምህርት/የስልጠና ዓመት፣ የሚኖርበት ሕንጻና ዶርም ቁጥር፣
   ለ. ተከሳሹ ተማሪ ከሆነ የተማሪውን የትምህርት/የስልጠና ውጤት፣ የሠራኛ ከሆነ የሥራ አፈጻጸም
   ሐ. የተከሳሹ የቀድሞ ሪከርድ
   መ. የዲሲፕሊን ጥፋቱን ዝርዝር፣ ደረጃና የተፈጸመበትን ሁኔታ
   ሠ. የተከሳሽ ምላሽ
   ረ. የምስክሮችን ቃል፣
   ሰ. ዝርዝር የውሳኔ ሐሳብ
   ሸ. የኮሚቴው አባላት ፊርማ ያለበት ቃለ ጉባኤ ከነአባሪ ማስረጃዎች ጋር
   ቀ. የሰብሳቢው ፊርማ ያለበት ሸኚ ደብዳቤ

**38. Calling a witness**

1) The Disciplinary Committee shall summon witnesses to appear before the due date.
2) Witnesses testifying against a disciplinary offense shall be summoned at the same time and testify one by one before the committee.
3) Where necessary, the plaintiff or the committee may present additional witnesses and their testimony may be heard.

**39. Hearing of witnesses**

1) In the presence of witnesses, both the defendant and the plaintiff shall be present. However, if one party is informed but not present, it does not preclude the testimony of witnesses.
2) The oral testimony of the witnesses shall be recorded.
3) The parties may request additional inquiries or cross-examination for witnesses and they can request this be recorded.

**40. The last response of the defendant charged with a disciplinary offense**

Before the disciplinary committee completes its investigation of the disciplinary offense, the defendant is given the opportunity to state his or her final opinion on the case. This shall be recorded verbatim. This can be used to justify or mitigate the level of punishment during the final decision of the committee.

**41. Recommendations**

1) As soon as the Disciplinary Committee investigates the disciplinary offense, it shall conduct the investigation, it shall submit the proceedings and action to be taken fully signed and completed to the immediate head of the Institute to which the committee is accountable.
2) The committee's recommendation should include the following:
   a. Defendant's full name, ID number, department, year of study, building and dorm number,
   b. If the defendant is a student, the student's academic performance, if he/she is an employee his/her result of performance evaluation
   c. Defendant's previous record
   d. Details of the disciplinary offense, the category of the offence, and the circumstances of the incident
   e. Defendant's response
   f. The testimonies of witnesses,
   g. Detailed recommendations
   h. Minutes signed by committee members with attached evidence
   i. Cover letter with the Chairperson's signature



Scanned with CamScanner

3) በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰ ተከሳሽ ተጣርቶ ከተከሰሰበት ጉዳይ ነጻ መሆኑ ሲረጋገጥ ይህንኑ የሚገልጽ የጽሑፍ መረጃ ይሰጠዋል፡፡

**42. የአስተዳደር ዘርፍ ምክትል ኃላፊ ውሳኔ**

የተቋሙ ም/ኃለፊ ወይም የካምፓስ ኃላፊ የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ከመረመረ በኋላ :-

1) የኮሚቴውን የውሳኔ ሐሳብ ሙሉ በሙሉ የማጽደቅ፤ ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ ሐሳብ የማሻሻል፤ ኮሚቴው ጉዳዩን እንደገና እንዲመረምር ምክንያቶችን ገልጾ የማዘዝ ሥልጣን አለው፡፡
2) በተቋሙ ም/ኃላፊ ወይም በካምፓሱ ኃላፊ የጸደቀው የዲሲፕሊን ውሳኔ ለተከሳሹ በጽሑፍ ይሰጠዋል፤
3) ከከባድ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እና ከዚያ በላይ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደበት ከሆነ ተመሳሳይ ቅጂ በትምህርትና ስልጠና ተቋሙ ግቢ ውስጥ ባሉ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ ይለጠፋል፡፡

**43. የውሳኔ አፈጻጸም**

1) የዲሲፕሊን እርምጃ ውሳኔ ከጸደቀበት ቀን አንስቶ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ተከሳሹ ከተቋሙ ግቢ የሚታገድ ከሆነ የ24 ሰዓታት ጊዜ ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም እንደ አንድ ባለጉዳይ ከውጪ እየተመላለሰ መጨረስ ያለበት ጉዳይ ካለ የሚመለከተውን አካል አስፈቅዶ መጨረስ ይችላል፡፡
2) በንዑስ አንቀጽ (ሀ) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩን ይግባኝ ብሎ ይግባኙ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ለተቋሙ የበላይ ሃላፊ ጥያቄ አቅርቦ ከተፈቀደለት በግቢ ውስጥ ሆኖ እየተማረ/እየሠራ እና አገልግሎት እያገኘ ጉዳዩን መከታተል ይችላል፡፡

**44. የዲሲፕሊን ጉዳይ ሰሚ ኮሚቴ የክስ አሰማም ሂደት (ስነ-ስርዓት)**

1) ሰብሳቢው የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ምክትሉ ኃላፊነቱን ይረከባል፡፡
2) የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ ጸሐፊው ይይዛል፡፡
3) ተከሳሹ በጽሑፍና በቃል መልስ የማቅረብ መብት አለው፡፡
4) ከፍተኛና አሳማኝ በሆነ ምክንያት ተከሳሹ በክርክሩ ሂደት መሳተፍ ያልቻለ እንደሆነ ሲታመን እስከሚችልበት ቀን ድረስ ክርክሩ እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡
5) ተከሳሹ ክሱን ለማስረዳት ከሳሽ ያቀረባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ከሳሽም ተከሳሽ ያቀረባቸውን የመከላከያ ምስክሮች የመጠየቅ መብት አለው፡፡
6) ተከሳሹ ዝም የማለት መብት አለው፡፡ ነገር ግን ዝምታው አምኖ እንደመቀበል ይቆጠራል፤

3) When a defendant charged with a disciplinary offense is found to be acquitted, he/she shall be given written information stating the same.

**42. Decision of the Administrative Deputy Head of the Institute**

After reviewing the recommendations made by the Discipline Committee, the Administrative Deputy Head of Campus, whether they are in accordance with the provisions of this Directive, shall:

1) fully approve the committee's decision; amend the committee's recommendation; or order the committee to reconsider the decisions mentioning justifiable reasons for the case.
2) The disciplinary decision approved by the Administrative Deputy Head of Campus or the Institution shall be given to the defendant in writing;
3) If a severe written warning or higher order disciplinary measure is taken against the defendant, the copy of the decision shall be posted on the notice boards on the campus of the education and training Institution.

**43. Implementing the decision of the committee**

1) Disciplinary action shall be effective from the date of approval. However, if the defendant is suspended from the premises, he/she shall be given 24 hours to clear from the campus. However, as a client, if there is an issue that needs to be settled, he/she can follow up his/her outstanding case with prior permission from Institution's Head.
2) Subject to the provisions of sub-article (a), he/she may appeal the case to the President or Head of the institution and, if permitted, may follow up the case while he/she on study or on duty in the Institute.

**44. Procedures by Disciplinary Hearing Committee**

1) The chairperson shall chair the meeting of the committee. In the absence of the Chair, the deputy shall assume responsibility.
2) The Secretary shall take the minutes of the committee.
3) The defendant has the right to respond in writing and orally.
4) If the defendant is found to have been unable to participate in the proceedings for serious and convincing reasons, the case may be adjourned until the day he/she can.
5) A defendant shall have the right to cross-examine the plaintiff's witnesses. Plaintiff also has the right to cross-examine the defendant's witnesses.
6) The defendant has the right to remain silent. But the silence is considered as acknowledgment of the case.



Scanned with CamScanner

## ክፍል አሰር
## የቅጣት አወሳሰን

### 45. ቅጣት ስለማቅለል

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ምክንያቶች ለዲስፕሊን ጥፋቶች ለሚሰጡ ቅጣቶች የቅጣት ማቅለያ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1) ጥፋተኛው ከዚህ በፊት መልካም ስነ ምግባር የነበረው መሆኑ ከመዝገብ ሲረጋገጥና ከዚህ በኋላ የመድገም ሀሳብ የሌለው እንደሆነ በመፀፀት በጽሑፍ ያቀረበ ከሆነ፣
2) ጥፋቱን የፈፀመው ከባድ አደጋ እየደረሰበት መስሎት ራሱን ለመከላከል በሚያደርገው ሙከራ ከሆነ፣
3) ጥፋቱን እንዲፈፀም የተጐጅው እጅ ካለበት፣
4) ጥፋቱን ሲፈጽም አጥፊው በከፍተኛ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጭንቀት ውስጥ ከነበረ፣
5) ጥፋተኛው የሚጠበቅበትን ሁሉ በማድረግና ጥፋቱን በማመን ከፍተኛ የመፀፀት አዝማሚያ ያንፀባረቀ እንደሆነ፣

### 46. ቅጣት ስለማከበድ

የዲሲፕን ጥፋት በፈጸመ ተከሳሽ የሚተላለፍ የቅጣት ውሳኔ ላይ ቅጣቱን ሊያከብዱ የሚችሉ ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1) ተደጋጋሚ፣ በሌሊት ወይም ጨለማን ተገን በማድረግ፣ የጦር ወይም ሌላ አደገኛ መሳሪያ በመያዝ ከሆነ፣
2) ጥፋቱን የፈፀመው ከሌሎች የወንጀለኞች ቡድን ጋር በመሆን በተለይ በመሪ ተዋናይነትና አደራጅነት ከሆነ፣
3) ጥፋቱን የፈጸመው በቡድን በመሆን ጥፋቱ የከበደና በሌላው ላይ አስበና ሆነ ብሎ ጉዳት ለማድረስ ከሆነ፣
4) ጥፋቱን የፈፀመው በማናለብኝነት፣ የተሰጠውን ወይም ያለበትን አደራ ወደ ጐን በመተው ሆነ ብሎ ለማጥፋት አስቦ ከሆነ፣
5) ጥፋቱን የፈፀመው በከፍተኛ ጥላቻ በመነሳት ወይም ሆን ብሎ አስቦበት ከሆነ፣
6) ጥፋቱን የፈፀመው ለጥል ባልተዘጋጁና ባላሰቡ ንጹሀን ወይም በተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች፣ መምህራን ወይም በአስተዳደር ሠራተኞች ላይ ከሆነ፣

### 47. የዲሲፕሊን ጥፋቱ በሪከርድነት በተያዘበት ወቅት ሲደገም

1) ቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት የዲሲፕሊን ግድፈት አነስተኛ ግድፈት ሆኖ ውሳኔው የሚያበቃበት ጊዜ ሳይደርስ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የሚገኝ የድስፕሊን ጥፋት ከተደገመ እስከ አንድ ወሰነ ትምህርት ከትምህርት ገበታ ያሳግዳል፡፡ የተደገመው ግድፈት አነስተኛ የዲሲፕሊን ጥፋት ካልሆነ ግን በአዲስ መልኩ ይታያል፡፡
2) ቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት ጥፋት ቀላል ሆኖ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የሚገኝ ጥፋት ወይም አነስተኛ ጥፋት ከተደገመ ከአንድ እስከ ሁለት ዓመት ከትምህርትና ስልጠና ገበታ ያሳግዳል፡፡ የተደገመው ጥፋት መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ከሆነ በጣም ከፍተኛ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚጣልበት ይሆናል፡፡

## Part Ten
## Penalties

### 45. Simplification of penalties

The following reasons may be considered for simplifying/lessening the penalties for disciplinary offenses.

1) If the offender has been found to have good moral in the past and regrets that he/she has no intention of repeating it in writing,
2) If he/she committed the offense in an attempt to defend him/herself thinking that he/she was in a dangerous situation;
3) If the victim has a part in the crime;
4) If the perpetrator was in a state of extreme physical and psychological distress while committing the crime;
5) if the offender has a strong tendency to regret for doing what is expected of him/her and admitting the offense;

### 46. Severe punishment

The following are some of the factors that may make the sentence of a defendant guilty of a misdemeanor worse.

1) Repeatedly carrying a weapon or other dangerous weapon, specially during night time covering up darkness,
2) He/she committed the crime in collaboration with other criminal gangs, especially as a leading actor and/or organizer;
3) If he/she commits the offense as a group and the offense is serious to intentionally harm others;
4) If he/she committed the offense in arrogance, deliberately neglecting the responsibility entrusted to him/her;
5) If he/she committed the crime out of hatred or willful intentions,
6) If the offense was committed on those innocent persons including head of the institution, teachers, students, or administrative staff who were physically and psychologically ready to fight prepared and had no intention to conflict with him/her;

### 47. When a disciplinary offense is repeated upon a recorded offense

1) If the disciplinary offense is a minor one, which is in the same category, and is repeated before the expiration of the decision, the offender shall be suspended him or her up to one semester. If the repeated error is not a minor disciplinary offense, it shall be treated anew.
2) If a previous offense, for which a decision is made, a minor and in the same category, is repeated, the offender shall be suspended for one to two years from the Institution. If the offense is moderate or severe, it shall result in a severe disciplinary action.

Ministry of Science and Higher Education, Federal Democratic Republic of Ethiopia



Scanned with CamScanner

3) ቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት ጥፋት መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ከሆነ የትኛውም ጥፋት ቢፈጽም ሙሉ በሙሉ የሚሰናበት ይሆናል፡፡

**48. ተደራራቢ የዲሲፕሊን ጥፋት ሲፈፀም የቅጣት አወሳሰን**

ተከሳሹ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከተቋሙ የሚያሳግዱ የዲሲፕሊን ግድፈቶች በአንድ ጊዜ ወይም በመጀመሪያ ለፈፀመው ጥፋት ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት ፈጽሞ ከተገኘ ለእያንዳንዱ ጥፋት ቅጣት ከተቀመጠ በኋላ የሁሉንም ቅጣት በመደመር ይወሰናል፡፡ የሁሉም ድምር ከሶስት ዓመት ከበለጠ ሙሉ በሙሉ ከተቋሙ የሚሰናበት ሆኖ አግባብ ባለው ህግም ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**49. ውሳኔን ስለማሳወቅና ተያያዥ ጉዳዮች አፈጻጸም**

1) ከምክር (ከግሳፄ) በስተቀር ማንኛውም በተከሳሽ ላይ በዲስፕሊን ጥፋት የሚወሰድ እርምጃ ለተከሳሹ በጽሑፍ ሊሰጠው ይገባል፡፡
2) በተቋሙ ውስጥ በማንኛውም ደረጃ የሚወሰድ የዲሲፕሊን ጥፋት እርምጃ ቢያንስ ለግቢ ደህንነትና ጥበቃ፣ ለሚመለከተው የትምህርት ክፍል ኃላፊ፣ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል፣ ለተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር፣ ለአስተዳደር ዘርፍ ም/ኃላፊና ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ በግልባጭ ማሳወቅ ይገባል፡፡ የተጠቀሱት አካላትም በአግባቡ አደራጅቶ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
3) ለተቋሙ ማህበረሰብ በሙሉ በግልጽ በሚታይ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ሌላው እንዲማርበት ይደረጋል።
4) ተከሳሹ ባጠፋው ጥፋት በጊዜያዊነትም ይሁን ሙሉ በሙሉ ከተቋሙ በሚታገድበት ወቅት የታገደበት ምክንያት በጽሑፍ ይገለጽለታል፡፡ በወቅቱ ተከሳሹ በተቋሙ በግቢ ውስጥ ባለመገኘቱ ወይም አድራሻው ባለመታወቁ ወይም በሌላ ምክንያት በአካል ሳይገኝ በመቅረቱ የታገደበትን ውሳኔ ለራሱ መስጠት ካልተቻለ ውሳኔው በተቋሙ ማስታወቂያ ሰሌዳ ቢያንስ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ተለጥፎ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡
5) ተከሳሹ የተከሰሰበት የዲሲፕሊን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ከተቋሙ እንዲታገድና ተማሪ ከሆነ የትምህርትና ስልጠና ማስረጃው እንዳይሰጠው ካልተወሰነበት በስተቀር እስከ ዕግዱ ያለው የትምህርትና ስልጠና ማስረጃ በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ያቋረጠ መሆኑን ከሚገልጽ ሸኚ ደብዳቤ ጋር ይሰጠዋል፡፡
6) የተከሳሹ በጊዜያዊነትም ይሁን ሙሉ በሙሉ ከተቋሙ መታገድ ከዕግዱ ጋር ያልተያያዙ መብቶችንና ግዴታዎቹን ተፈጻሚነት አያስቀርም፡፡
7) ውሳኔ ለመስጠትም ይሁን ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር፣ የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር እና የተማሪዎች ህብረት የውሣኔ መጓተት እንዳይፈጠር አፈፃፀሙን ይከታተላሉ፡፡

3) If the offense is a foregone conclusion, the offender shall be completely dismissed for any offense thereof.

**48. Determination of punishment in the event of multiple disciplinary offenses**

If the defendant is found guilty of two or more disciplinary offenses committed at the same time or sequentially, before a decision is made for the first offense committed, penalty shall be determined by adding up the total penalty for each offense. If the sum of the disciplinary action is more than three years, the offender shall be dismissed completely from the institution and shall be liable by applicable law.

**49. Informing decisions and implementation of related matters**

1) Any disciplinary action against the defendant, except for oral reprimand or advice, shall be given to the defendant in writing.
2) Disciplinary action taken at any level in the institution shall be notified in writing to the head of the security department, the relevant department, the director of student affairs, the administrative deputy head of the institution, and the head of the institution. The mentioned bodies should keep the document properly in an organized manner.
3) Post the decisions on notice boards in the campus visible to the entire community of the institution.
4) The reason for the suspension of the defendant, whether temporarily or permanently, shall be stated in writing and given to him/her. If the defendant is not present in the institution to be informed or notified of the decision due to his/her absence from the campus, or if his/her address is not known, or for other reasons, the decision shall be posted on the notice board of the institution for at least five consecutive days.
5) If the defendant is provided with a letter stating that he's dismissed from the institution, unless the disciplinary action explicitly indicates that he/she (if he/she is a student) shall not be given his/her education or training certificate, the defendant has the right to take the certificate.
6) The suspension of the defendant, temporarily or permanently, does not preclude the exercise of his rights and obligations not related to the suspension.
7) The Director of Human Resource Management, the Director of Student Services and the Student Union shall monitor the procession of decision making to ensure that no decision is late.



Scanned with CamScanner

**50. የዲሲፕሊን ጥፋት ቅጣትን በሪከርድነት ስለመያዝ**

ማንኛውም ተከሳሽ የዲሲፕሊን ጥፋት የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈበት በኋላ በግል ፋይሉ ውስጥ ገብቶ በሪከርድነት ሊያዝበት የሚችለው

1) ለአነስተኛና ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ቅጣት ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ የሚቆይ ሲሆን በተከሳሹ ማህደር ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይ ተቀምጦ ቢገኝ ዋጋ አይኖረውም::
2) ለመካከለኛ፣ ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ውሳኔ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ተከሳሹ ተማሪ ከሆነ በሰነድነት በተመራቂው ፋይል ውስጥ ሁሌም ይቀመጣል::

## ክፍል አስራ አንድ
## የይግባኝ ስነ-ሥርዓት

የይግባኝ ውሳኔ አሠጣጥ ሂደቱ ከዲሲፕሊን ጥፋት ክስ አመሠራረት እስከ ውሳኔ አፈጻጸም ድረስ ካለው ጋር ተመሳሳይ ሂደትን የሚከተል ነው::

**51. የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

የተቋሙ የበላይ ኃላፊ የተቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንዲመረምረው ያደርጋል:: አስፈላጊ ሲሆንም ሶስት አባላት ያሉት የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል::

**52. ይግባኝ የማቅረብ መብት**

1) ጥፋተኛነት የተወሰነበት ተከሳሽ ቅሬታውን (ይግባኙን) ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ እንዲቀርብለት ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ውሳኔው ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማመልከቻ የማቅረብ መብት አለው:: የይግባኝ ማመልከቻውም የሚከተሉትን መያዝ አለበት::
   ሀ. የይግባኝ አቅራቢ ስም፣ መታወቂያ ቁጥር፣ ጾታና እድሜ
   ለ. የሚሰራበት ሥራ ክፍል፣ ተማሪ ከሆነ የሚማርበት ፋካሊቲ፣ ትምህርት ክፍልና የትምህርት ዓመት
   ሐ. የቅሬታው መንስኤ
   መ. ደጋፊ ማስረጃዎች /ካሉ/
   ሠ. አመልካች የሚሻው መፍትሄ
   ረ. ቀንና ፊርማ
2) የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በወቅቱ የቀረበውን ቅሬታ አይቶ መጣራት አለበት ብሎ ሲያምን የተጻፈውን ማመልከቻ ከአስፈላጊ መረጃ ጋር ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊመራው ይችላል።
3) ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የተመራለትን ማስረጃዎች አግባብነት ካላቸው የተቋሙ ህጎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች አንፃር በመመርመር በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅጣቱን ሊያፀድቀው፣ ሊያሻሽለው ወይም ውድቅ እንዲሆን ወይም እንደገና በዲስፒሊን ኮሚቴ እንዲመረመር ወይም ለየት ያለ ቅጣት እንዲወሰን ከዚህ መመሪያ ጋር የተገናዘበ አማራጭ የውሳኔ ሃሳብ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሊያቀርብ ይችላል:: በዚህ ላይ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ይሰጣል::

**50. Recording of penalties of disciplinary offenses**

The records of penalties for any disciplinary offences committed by any defendant shall be kept in his/her personal file after a disciplinary action has been taken.

1) For minor and simple disciplinary offenses, it shall be kept and remain valid for one year from the date of imposition and shall not be valid if it is kept in the defendant's file for more than one year.
2) If the defendant is a student, the decision for moderate, high and severe disciplinary offenses shall always be documented in the graduate's file.

## Part Eleven
## Appeal Procedures

The appeals processes follow similar paths as the disciplinary action processes.

**51. Establishment of Appeals Committee**

The head of the institution shall have the institution's grievance committee investigate appeals. If necessary, the head may establish a three-member appeals committee.

**52. Right to appeal**

1) The convicted defendant shall have the right to submit a written request to the appeals committee of the Institution within five working days from the date of notification of the decision. The appeal must include the following:
   a. Appellant's name, ID number, gender and age
   b. Workplace, if a student his/her major, the department and matriculation year
   c. The root cause of the complaint
   d. Supporting evidence, if available
   e. The resolution the appellant seeks
   f. Date and signature
2) When the head of the institution determines that the complaint deserves closer investigation, he/she may refer the application to the appeals committee with the necessary detail.
3) The Appeals Committee shall, within three working days, review the available evidence in accordance with relevant laws, rules, regulations and procedures of the institution and approve, amend or revoke the sentence or have it re-examined by the disciplinary committee or decide on a different punishment. As an alternative, the Appeals Committee may, in accordance with this Directive, propose another course of action to the head of the institution. In such situations, the head of the institution will make the final decision.



Ministry of Science and Higher Education, Federal Democratic Republic of Ethiopia
Scanned with CamScanner

4) ይግባኝ የሚቀርብባቸው ጉዳዮች መካከለኛና ከዚያ በላይ ምድብ ላይ ለሚገኙ የዲሲፒሊን ጥፋቶች ላይ በተላለፈ ውሳኔ ላይ ነው::

**53. የይግባኝ መሠረቶች**

1) በዲስፒሊን ኮሚቴ ታይቶ በአስተዳደር ዘርፍ ም/ኃላፊ በጸደቀ የዲሲፒሊን እርምጃ ላይ ቅሬታ ሲኖር
2) አዲስ ማስረጃ ካልተገኘ በስተቀር ይግባኝ መሠረት የሚያደርገው የዲሲፒሊን ኮሚቴ ባሰባሰባቸው ማስረጃዎችና በውሳኔ መዝገብ ላይ ብቻ ነው:: አዲስ የከስ ጭብጥ በይግባኙ ላይ አይቀርብም::
3) የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኙን ማየት አግባብ ሆኖ ካገኘው:
   ሀ. የመጀመሪያ ክርክሩ ስነ-ስርዓቱን ጠብቆ ስለመካሄዱ፣
   ለ. የተወሰነው ውሳኔ በቂ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ
   ሐ. ቅጣቱ ተከሳሹ አጥፍቷል ለተባለው ጥፋት ተመጣጣኝ ስለመሆኑ
   መ. ተከሳሹ በዋናው ክርክር ሂደት ወቅት ሊያገኘው ያልቻለውና ውሳኔ ማስቀየር የሚችል ማስረጃ ካቀረበ ኮሚቴው የቀረበውን ማስረጃ መርምሮ በሶስት ውስጥ የውሳኔ ሐሳቡን ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር በማያያዝ ለተቋ የበላይ ኃላፊ በጽሑፍ ያቀርባል::

**54. የቅጣት አፈፃፀም**

1) በተከሳሹ ላይ የተወሰነውን ውሳኔ በማስታወቂያ ከወጣበት ሰዓት ጀምሮ ውሳኔው በጥፋተኛው ላይ ተግባራዊ ይሆናል፣
2) ተከሳሹ የይግባኝ ማመልከቻ አቅርቦ ይግባኙ አግባብ መሆኑ ከታመነበትና ተከሳሹ ሂደቱን በተቋሙ ውስጥ ወይም ሥራ ላይ ሆኖ መከታተል ከፈለገ ግቢ ውስጥ ወይም ሥራ ላይ በመቆየቱ በራሱ፣ በተቋሙ ማህበረሰብና ንብረት ላይ የሚያመጣው አደጋ አለመኖሩ ከታመነበት የይግባኝ ስርዓቱን እስኪጨርስ ግቢ ውስጥ ወይም ሥራ ላይ እንዲቆይ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሊፈቀድለት ይችላል።

**55. የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ስልጣንና ኃላፊነት**

1) በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰ ተከሳሽ ጉዳይ በውሳኔ ሂደት ላይ እያለ የተከሳሹ ግለሰብ ከተከሰሰበት የዲሲፒሊን ጥፋት ከብደት አንፃር በተቋሙ ግቢ ውስጥ መኖር ወይ ሥራ ላይ መገኘት ለእርሱና ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት መልካም አለመሆኑን በማንኛውም መንገድ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሲያውቅ ጉድዩ ተጣርቶ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ተጠርጣሪው ሰብዓዊ መብቱ በአግባቡ ተጠብቆለት፣ አስፈላጊውን አገልግሎት ከተቋሙ ማግኘት በሚችልበት መንገድ በአካባቢው ፖሊስ ቁጥጥር ስር የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል::

4) Appeals can be made only on decisions made in middle and upper division disciplinary proceedings.

**53. Legitimate appeals**

1) Cases that have been reviewed by the Disciplinary Committee and approved by the institution's deputy head
2) Unless new evidence is found, the appeal shall be based only on the evidence gathered by the Disciplinary Committee and materials on file. No new charges will be filed on appeals.
3) If the Appeals Committee finds it appropriate to review the appeal
   a. Check to see if the case has followed proper procedures.
   b. Review if the decision was based on sufficient evidence.
   c. Check whether or not the sentence is commensurate with the defendant's alleged offenses.
   d. If the defendant presents pertinent evidence that he or she was previously unable to present, the Appeals Committee can review and forward its proposed decision in writing with cover letter to the head of the institution within three days.

**54. Execution of punishment**

1) The final decision on the defendant shall be effective from the time of the notice publication.
2) If the defendant submits an appeal and the appeal is deemed appropriate and the defendant wishes to monitor the proceedings within the institution or while at work, the head of the institution may permit the defendant to remain on the premises until the end of the appeals process.

**55. Powers and responsibilities of the head of the institution**

1) In the course of the decision process of the defendant, the defendant's human rights shall be properly protected until the case is investigated and a decision is made by the head of the institution. Depending on the severity of the case, if the presence of the defendant on campus or at work can have detrimental consequences, the head of the institution has the prerogative and responsibility to consider available circumstances and determine a course of action that protects the wellbeing of the institution and campus community. Until the case is resolved, the head of the institution does have the authority and responsibility to have the defendant under police surveillance or custody, if circumstances warrant.

Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia



Scanned with CamScanner

2) በዚህ መመሪያ መሠረት ከተቋሙ ሙሉ በሙሉ ለተሰናበቱ ተከሳሽ ግለሰቦች የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ አስግብቶ ይቅርታ የማድረግ ወይም ውሳኔውን የማሻሻል ሥልጣን አለው፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ያጠፋው ንብረት ዋጋ ያለው ከሆነ ተተምኖ እንዲከፍል ማድረጉን አያስቀርም።

3) የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በዲስፐሊን ጥፋት ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ይቅርታ የሚያደርግለት ወይም ውሳኔውን የመገደብ ስልጣኑን የሚጠቀመው ተከሳሽ የቀድሞ ሪከርዱንና ከጥፋቱ ተምሮ የተፀፀተ መሆኑን ሲያረጋግጥና ይህንንም የሚገልጽ የይቅርታ ደብዳቤ በጽሑፍ ተከሳሹ ሲያቀርብና ሲታመንበት ነው።

**56. የመጨረሻ ውሳኔ**

በዲሲፐሊን ጉዳይ የተቋሙ የበላይ ሃላፊ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**ክፍል አስራ ሁለት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**57. የሰዓት ገደብና እንቅስቃሴ ሁኔታ**

1) ማንኛውም ተማሪ ከምሽት 1:00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ 12:30 ሰዓት ድረስ ከግቢ መውጣትም ሆነ ወደ ግቢ መግባት የተከለከለ ነው፡፡

2) ከተማሪ ውጭ ያሉ ሌሎች ግለሰቦች በልዩ ሁኔታ ከላይ ከተጠቀሰው ሰዓት ውጭ ወደ ግቢ መግባትና ከግቢ መውጣት ቢያስፈልግ ኃላፊነት በተሰጠው አካል ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡

3) ከመማሪያ ክፍሎች፣ ከቤተሙከራ፣ ከቤተ-መጽሐፍት በስተቀር አስገዳጅ ካልሆነ የሰው እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው ቦታዎች ላይ መሄድ ወይም መቆየት አይመከርም፡፡

**58. አፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ አቅርቦት እና አካላዊ ርቀት**

1) የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተማሪዎች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ በቀነሰ ዋጋ ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊያመቻቹ ይችላሉ፡፡

2) እንደየትምህርትና ስልጠና ተቋማቱ ርቀትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ተጨማሪ እርምጃዎችን ሊወስዱ ይችላሉ፡፡

**59. ተማሪዎች ሲመለሱ የትራንስፖርር አገልግሎት አቅርቦት**

የትምህርርትና ስልጠና ተቋማት ተማሪዎችን መልሰው ሲቀበሉ በጉዞ ወቅት የሚኖረውን ለኮቪድ-19 ተጋላጭንትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ጥንቃቄዎችን ታሳቢ ያደረገ ከፍያው በተማሪዎች የሚሸፈን የትራንስፖርት አገልግሎትን ተማሪዎች እንዲያገኙ ለማስቻል ከሚመለከታቸው የትራንስፖርት ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ሌሎች እርምጃዎችንና ድጋፎችን ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

2) The head of the institution shall have the power to pardon or amend the punishment, taking into account the circumstances of the defendant in accordance with this Directive. However, if the defendant is to compensate the institution for lost value, the defendant must still make full payment, despite the improved decision by the head of the institution.

3) The head of the institution shall grant pardons or improve the punishment following the conviction of a disciplinary offense. The head of the institution may exercise his/her discretionary powers upon verification of the defendant's previous records and only if the defendant expresses remorse and submits a letter expressing his/her regrets and the lessons learned.

**56. Final decision**

In disciplinary matters, the decision of the head of the institution shall be final.

**Part Twelve**

**Miscellaneous Provisions**

**57. Time limit and movement in the campus**

1) All students are prohibited to entering or exit the campus between the hours of 7:00pm and 6:30am.

2) Individuals other than students, must gain special permission from a relevant administrator to enter the campus outside of operation hours.

3) "Stay home/dorms if unwell" is advisable.

**58. Mask supply and physical distance**

1) Educational and training institutions may provide masks to students at reduced prices.

2) Depending on the circumstances at the education and training institution, management may implement additional measures to maintain appropriate distances.

**59. Transportation services for students' return**

Educational and training institutions may work in partnership with relevant transport agencies and other stakeholders to ensure that students receive transportation services that are covered by the students and taking precautions to reduce the risk of COV-19 during travel. Other steps may be taken as necessary.



Scanned with CamScanner

**60. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች፣ መምህራንና አስተዳደር ሠራኞችን በሚመለከት**

1) የትምህርትና ስልጠና ተቋማት የአካል ጉዳት ያለባቸውና የሌሎችን ድጋፍ የሚሹ የትምህርትና ስልጠና ማህበረሰብ አባላት ሲኖሩ እነርሱና የሚያግዙአቸው ግለሰቦች ሊያደርጉት ስለሚገባ ጥንቃቄ እንደየልዩ ፍላጎታቸው ዓይነትና መጠን ግንዛቤ መፍጠርና ስልጠና መስጠት አለባቸው፡፡
2) ልዩ የመማሪያ ክፍል፣ የቤተ መጽሐፍት፣ የምግብ አቅርቦት የሚፈልጉ ሆነው ሲገኙም አገልግሎቱን የሚያገኙበት ልዩ ሁኔታ እንዲመቻችላቸው ይመከራል፡፡
3) ምንም ዓይነት ልዩ ፍላጎት ቢኖራቸውም ከሌሎች ሰዎች ጋር ግቢ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ አካላዊ ርቀትን የመጠበቅ፣ እጅ የመታጠብ፣ አፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የመጠቀም ግዴታ አለባቸው፡፡
4) በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሆኑትን (የጤና እክል ያለባቸው እና እድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ የሆኑትን) በተመለከተ ተቋማቱ እንደሥራቸውና እንደተቋሙ ልዩ ባህሪይ አንጻር እያዩ ተጋላጭነታቸውን ሊቀንስ የሚችል እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ፡፡
5) ተማሪዎች በኮቪድ-19 ተጠርጥረው ታመው በማቆያ ወይም በለይቶ ማቆያ ወይም በማገገሚያ ማዕከላት ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ትምህርታቸውን መማር ቢፈልጉ እና ቢችሉ በቴክኖሎጂ ታግዘው መማር የሚችሉበትን አማራጮች ተቋማት የማመቻቸት ግዴታ አለባቸው፡፡

**61. የዲሲፕሊን ውሳኔና እርምጃ አወሳሰድ**

ከኮቪድ -19 በሽታ ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሶ የተገኘ ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ማህረሰብ አባል ቀደም ሲል የነበረውን የዲሲፕሊን ውሳኔና እርምጃ አወሳሰድ ሂደት ሳይጠብቅ በልዩ ሁኔታ አፋጣኝ ውሳኔ የሚሰጥበትና እርምጃ የሚወሰድበትን አሠራር ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡

**62. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረው የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ማህረሰብ የዲሲፕሊን መመሪያዎች በዚህ መመሪያ የተተኩ በመሆናቸው ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡ ሌሎች ህጎችና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**63. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ተቋም ማህረሰብ አባል ወደ ግቢ ውስጥ ሲገባም ሆነ በግቢ ውስጥ በሚያደርጋቸው እቅስቃሴዎች ሁሉ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

**64. የማስፈጸም ኃላፊነት**

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ለተቋሙ ማህበረሰብ በሙሉ የማስተዋወቅና ግንዛቤ በመፍጠር በበላይነት የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡

**65. ክትትል፣ ግምገማና ሪፖርት**

የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በተቋማቱ ግቢ ውስጥ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች አተገባበር ሂደትንና ውጤቱን የመከታተል፣ የመገምገምና በመደበኛነት ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**60. Regarding students, teachers and administrative staff with special needs**

1) For special needs or disabled students, Education and Training Institutions shall create public awareness and provide specialized training for their designated assistants.
2) It is recommended that special classrooms, libraries, cafeteria arrangements be provided to those who need them.
3) Special needs and/or disabled students are expected to maintain appropriate physical distances just the same.
4) Regarding highly exposed individuals (health problems, age over 60 years…), the institutione may take measures that decrease the risk based on nature of the insitituion and individuals work.
5) When students want and able to learn while they are in the quarantine or isolation or treatment centers, they must get technology assisted learning paltforms; which shall be arranged by the institutions.

**61. Disciplinary decision-making and action**

Any member of the Education and Training community who violates this guideline to prevent and control the spread of Covide-19 epidemic may be subject to the decisions made by the head of the institution in a particularly prompt and decisive manner, regardless of the previous disciplinary decision-making process.

**62. Laws that do not apply**

The previous Education and Training community Discipline Directives has been replaced by this Directive and will not be applicable. Other laws and practices governing discipline do not apply on matters covered by this Directive.

**63. Obligations to cooperate**

Everyone who enters the premises of the Education and Training Institution, while on the premises, is required to respect and comply with this Directive.

**64. Enforcement responsibility**

The head of the institution is responsible for introducing to the entire community, promoting and enforcing this Directive.

**65. Monitoring, evaluation and reporting**

The Education and Training Institutions are responsible for monitoring, evaluating and implementing the Directive in the premises, and for regularly reporting to the Ministry of Science and Higher Education.



Scanned with CamScanner

### 66. መመሪያውን ስለማሻሻልና ስለመሻር

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

### 66. Amending and repealing the Directive

When deemed appropriate, this Directive may be amended or revoked by the Ministry of Science and Higher Education.

### 67. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

### 67. Effective Date of the Directive

This directive is effective as of October 10, 2020.

............................................................

ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ)
የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
ሚኒስትር

............................................................

Samuel Urkato (Ph.D)
Minister, Ministry of Science and Higher Education



Scanned with CamScanner